ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂወማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና ስነ-ጹሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምርቃ መርሀ ግብር

# የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ ጋብቻ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና

በ

ሽታዬ ገዕኖሬ

ዋና አማካሪ አብይ አሰፋ(ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ አቶ ሀብታሙ እንግዳው

በተግባራዊ ስነ ልሳን በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ጥናት ዘርፍ

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት

ጥቅምት 2011 ዓ/ም

ጅማ (ኢትዮጵያ)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂወማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና ስነ-ጹሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምርቃ መርሀ ግብር

# የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ ጋብቻ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና

በ

ሽታዬ ገፅኖሬ

ዋና አማካሪ አብይ አሰፋ(ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ አቶ ሀብታሙ እንግዳው

በተግባራዊ ስነ ልሳን በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች ጥናት ዘርፍ

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥቅምት 2011 ዓ/ም

ጅማ (ኢትዮጵያ)

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------- i

አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------- ii

አበርክቶ ---------------------------------------------------------------------------- iii

ምዕራፍ አንድ ---------------------------------------------------------------------- 1

መግቢያ ------------------------------------------------------------------ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------- 1

1.2 አካባቢያዊ ዳራ ------------------------------------------------------------------ 2

1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት -------------------------------------------------------- 4

1.4 የጥናቱ አላማ ----------------------------------------------------------------------- 4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ------------------------------------------------------------------ 5

1.6 የመስክ መረጃ አሰባሰብ ሂደት -------------------------------------------------- 6

1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ---------------------------- 8

1.8 የጥናቱ ወሰን -------------------------------------------------------------------- 8

ምዕራፍ ሁለት ------------------------------------------------------------------------ 10

ክለሳ ድርሳናት ------------------------------------------------------------------- 10

2.1 የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ---------------------------------------------------------- 10

2.1.1 የባህል ምንነት ------------------------------------------------------------ 10

2.1.2 ክብረ በዓል ------------------------------------------------------------------ 11

2.1.3 የበዓል ስነ ስርዓ -------------------------------------------------------------- 12

2.1.4 ጋብቻ (ሠርግ) -------------------------------------------------------------- 12

2.1.5 የጋብቻ ምንነት ---------------------------------------------------------------- 13

2.1.6 የቋንቋ ምንነት --------------------------------------------------------------14

2.1.7 የቋንቋ አጠቃቀም ------------------------------------------------------------- 15

2.1.8 ዲስኩር ---------------------------------------------------------------------------- 17

2.2 የተዛማች ጽሁፍ ቅኝት --------------------------------------------------------- 19

2.2.1 ትኩረታቸውን በከምባታ ብሄረሰብ ላይ ያደረጉ ጥናቶች ----------------- 19

2.2.2 በርዕሰ ጉዳይ የሚዛመዱ ጥናቶች ------------------------------------------ 21

ምዕራፍ ሶስት ---------------------------------------------------------------------------- 22

3 የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ------------------------------------------------------------ 22

3.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ------------------------------------------------------ 22

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ---------------------------------------------------- 23

3.2.1 ምልከታ ------------------------------------------------------------------------ 23

3.2.2 ቃለመጠይቅ -------------------------------------------------------------------- 23

3.2.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት --------------------------------------------------- 24

3.2.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ---------------------------------------------- 25

3.3 መረጃ መተንተኛ ዘዴ -------------------------------------------------------- 25

3.4 መረጃን መተርጎምና ማጠቃለያ መስጠት -------------------------------------- 26

ምዕራፍ አራት ------------------------------------------------------------------------------ 27

4.1 ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች ስርዓትና የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና በከምባታ ብሄረሰብ

4.1.1. የጋብቻ እሳቤ በከምባታ ብሄረሰብ ------------------------------------------27

4.1.2. ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች -------------------------------------------------------30

4.1.2.1.‹‹ቆርሲሸተ›› በመተጫጨት መጋባት --------------------------------------------30

4.1.2.1.1. ጋብቻ ከልክል ---------------------------------------------------------------32

4.1.2.1.2 ‹‹ ጪቹ ጡደቁ›› ገድ የማየት ስርዓት -------------------------------------33

4.1.2.1.3 ‹‹ሀሌቹ አሲዬ›› ጥላ ስጡን ስርዓት --------------------------------------44

4.1.2.4‹‹ ሶፋ ››እና‹‹ ሰጋዩ›› የቃልኪዳን ምልክት ---------------------------------- 47

4.1.2.5‹‹ ቆት ሴራ›› ጥሎሽ ----------------------------------------------------------------50

4.1.2.6 ሴሌሞመት ዲኩት የድንግልና የመጨረሻ ገበያ --------------------------------62

4.1.2.7‹‹ ሰጋዩ መረሙ››የሰርግ ጥሪ አደራረግ ---------------------------------------------62

4.1.2.8 ‹‹ኪፋ››በማር የመመረቅ ስርዓት -----------------------------------------------------64

4.1.2.9 አጃቢዎች ወደ ሙሽራው ቤት ሲሄዱ የሚጫወቱት ጫዋታ -----------------68

4.1.2.10‹‹ ሱዕማ ፉሹ›› የሙሽሪት ስም አወጣጥ ----------------------------------------74

4.1.2.11‹‹ ጎጫ አፍ ሴራ›› በር የመያዝ ስርዓት -----------------------------------------89

4.1.2.12 ‹‹ቆራ ሂር›› ወገብ የመፍታት ስርዓት ------------------------------------------90

4.1.2.13 ‹‹በልሸተ›› የአክብሮት ጥሪ -------------------------------------------------------90

4.1.2.14‹‹ ኢሪፉተ›› ስጦታ -------------------------------------------------------------------95

4.1.2.2‹‹ ሂረቱተ›› አግባብቶ ማግባት -----------------------------------------------------97

4.1.2.2.1 ‹‹መገንተ›› የሙጥኝ------------------------------------------------------------------97

4.1.2.3 ‹‹ምዱ›› የጠለፋ ጋብቻ -----------------------------------------------------------102

4.1.2.4 ‹‹ረግተ›› የውርስ ጋብቻ -----------------------------------------------------------103

4.1.2.4.1 የውርስ ጋብቻ አፈጻጸም --------------------------------------------------------104

ምዕራፍ አምስት

5 ማጠቃለያና አስተያየት -------------------------------------------------------------110

5.1 ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------------------------110

5.2 አስተያየት --------------------------------------------------------------------------112

6 የተጠቀሱ ምንጮች ---------------------------------------------------------------113

መረጃ አቀባዮች--------------------------------------------------------------------------- 117

አባሪዎች -------------------------------------------------------------------------------118

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት አስጀምሮ ላስጨረሰኝ እግዚአብሄር ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡በማስከተል የዚህን ጥናት ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ረቂቁን ጽሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመው በማንበብ ፣ በማስተካከልና ቃላቱና ሐረጋቱ ተቃንተው መልዕክቱ ለሌሎች እንዲደርስ ላደረጉልኝና ያለማቋረጥ ገንቢ ምክራቸውን ላልነፈጉኝ አማካሪዬ ለዶክተር አብይ አሰፋ ከልብ የመነጨ የአክብሮት ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በመቀጠል ለ2ኛ ዲግሪ መርሀ ግብር ተመዝግቤ ለፍጻሜ እስክበቃ ድረስ የቤቴን ክፍተቶች ሳላስብ ቤተሰብን በመምራትና መረጃ ስሰበስብ ከጎኔ ላልተለየው ባላቤቴ አቶ ኤልያስ ሂገና ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡በተጨማሪም ከምሰጣቸው ፍቅርና እንክብካቤ ላይ ቀንሼ ለትምህቴና ለጥናት ሰፊ ጊዜ ስወስድ በትዕግስት ለጠበቁኝ ልጆቼ ውብ ዕድል ኤልያስ ፣ ሹምነህ ኤልያስና ምሁር ኤልያስን ከልብ አመሰግናሁ፡፡

ለጥናቴ ስኬታማነት መረጃን በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ የኮካታ አባላት በሙሉ ፣ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በተለይ አቶ አቦ ሂገና፣አቶ ባንዳ ዴቦ ፣አቶ ስምኦን አያኖ ፣ አቶ ተክሌ ሙጎሮ አና አቶ አቦ ለጄቦ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ፡፡ ሳላመሰግን የማላልፋቸው አቶ ካሳ ጆሬና ወልደኣብ ጆሬን እግዚአብሄር ዕድሜ ይስጥልኝ፡፡

በመጨረሻም ለ2ኛ ዲግሪ ተፈትኜ ማለፌን ለዳምቦያ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የበጀት ድጋፍ እንዲያደርግልኝ በማመልከቻ ጠይቄ ያለምንም ማመንታት በሰኣቱ የነበረዉ ካቢኔ አባላት ፈቃዳኞች ሆነውልኛልና ባለውለታዎቼ ናቸው ፤ እግዚአብሄር ይስጥልኝ፡፡ በተለይ ዋና አስተዳዳሪ የነበሩ አቶ ጌታቸው ዓለሙ ትምህርቴን እንድከታተል በጀቱ እንዲፈቀድ ከፍተኛ አስተዋጽ አድርገዋልና የከበረ ምስጋና ይድረሳቸው ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሚገኘው በከምባታ ጠምባሮ ዞን በዳምቦያ ወረዳ በተመረጡ ስድስት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማም የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ነው፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ለጥናቱ በተመረጠው ቦታ በአካል በመገኘት በምልከታ ፣ በቃለ መጠይቅ ፣ በቡድን ውይይት ነው ፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ አራት አይነት ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቶች የቋንቋ አጠቃቀም (ዲስኮርስ) ትንተና ተደርጓል፡፡

በጥናቱ ሃያ መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህ ሃያ መረጃ አቀባዮች ውስጥ አስራ አንዱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው ፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭ እና በጥልቅ የዲስኩር ትንተና (CDA) ትወራ ትንተና ተካሄዷል ፡፡

በጥናቱ እንደተገኘው አራት ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቶች መኖራቸውና ባህላዊ እሴቶቻቸውን በቋንቋ አማካኝነት የማህበረሰቡን እምነት ፣ አመለካከት ፣ ፍልስፍና ፣ ጾታዊ እይታ ፣ ማህበራዊ ደረጃ ፣ ባህል እንዴት እንደሚገልጹ በዲስኩራዊ ትንተና ተጠቁሟል ፡፡ ብሄረሰቡ እነዚህን ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቶች ትምዕርታዊ መልዕክት የቋንቋ ዉክልና ባላቸው ስርዓቶች እና ስርዓቱን ሊያጸኑ የሚችሉ ማህበራዊ የቋንቋ አገላለጽን በመጠቀም መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

እነዚህ ባህላዊ እሴቶች በአሁን ሰኣት የመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል ፡፡ ሙሉ በሙሉ ከጠፉ የማህበረሰቡ እምነት ፣ አስተሳሰብ ፣ ፍልስፍና ባጠቃላይ ማንነቱ አብሮ ስለሚጠፋ አጥንቶ ለቀጣይ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚመለከተው አካል ሁሉ ትኩረት ቢሰጠው መልካም ነው፡፡

# አበርክቶ

ለትምህርት ትልቅ ፍቅርና አክብሮት የነበረው ልጆቹን ለማስተማር ሳይደላው ነገር ግን ዛሬ ለምደርስበት ደረጃ መሰረት የጣለልኝ በ1998 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ለተለየኝ አባቴ አቶ ገዕኖሬ ኡሳሞ ፣ አግብታ ትዳሯን ሳታጣጥም የወለደቻትን አንዷት ልጇ ጨቅላነቷን ሳትጨርስ ኑሮዋን የተሻለ ለማድረግ ደፋ ቀና እያለች እየሮጠች ባለችበት ገና በለጋ ዕድሜዋ በ1996 ዓ/ም ይህንን ዓለም በሞት ለለቀቀችው እህቴ ብርትኳን ገዕኖሬ ፣ የባለቤቴ ወንድም ልጆቹን ለወግ ማዕረግ ሳያደርስ ህልሙን ምኞቱን መንገድ ላይ በትኖ በ2007 ዓ/ም ይህንን ዓለም በሞት ለተሰናበተው ለአቶ ሳሙኤል ሄገና ይህ ጥናት መታሰቢያ ይሁንልኝ ፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን ነው ፡፡ ጥናቱ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ቀርቧል ፡፡ በምዕራፍ አንድ ላይ የጥናቱን ርዕስ አስመልክቶ የምሁራን ሀሳብ እና ለጥናቱ የተመረጠው አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ ፣ ጥናቱን ለማጥናት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ፣ ጥናቱ ይዞ የተነሳው ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ ያጋጠሙ ችግሮች ፣ የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦችና የጥናቱ ወሰን የተካተተበት ነው ፡፡ ምዕራፍ ሁለት ስለ ባህልዊ ጋብቻና ስለ ቋንቋ አጠቃቀም በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ሀሳቦችና በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች የዳሰሰና ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ዝምድናና ልዩነት የሚተነትን ነው፡፡በምዕራፍ ሶስት የናሙና አመራረጥ ዘዴ ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ያካተተ ሲሆን ምዕራፍ አራት እንዲሁ በአራት ባህላዊ የጋብቻ ስርኣት ውስጥ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ፣ ከባህል ፣ ከእምነት ፣ ከጾታ ፣ ከማህበራዊ ደረጃና ፍልስፍናን የሚገለጹ ሀሳቦች ዲስኩራዊ ትንተና ይዟል፡፡

በመጨረሻዉ ምዕራፍ ማጠቃለያና የተገኙ ውጤቶችን አካቶ ቀጣይ ጥናት የሚሹ የምርምር ስራዎች ጥቆማ ቀርበዋል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ለማስፈጸም በቋንቋ አማካኝነት የፊት ለፊት ተግባቦት በሚያደርጉበት ጊዜ የሚስተዋሉትን ሁኔታዎች በጥናቱ መዳሰስና መተንተን እንዲሁም ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት የሚያስፈጽሙ አካላት የሰመረ ጋብቻ እንዲሆን የሚጫወቱት ሚና ማጥናት ፤ በቋንቋ አማካኝነት የሚገለጹ የባህል እውቀቶችን ማሳየት የጥናቱ የትኩረት ነጥቦች ናቸው፡፡

ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህል ፣ ወግ ፣ እምነት ወዘተ አለው ፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ በውስጡ ወግ ማዕረግ ፣ ክብረ በዓል ፣ ሀገረሰባዊ እምነት ፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒት፣

ባህላዊ መዝናኛዎች ሠርግ ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ ሠርግ ከተለያዩ የህይወት ዑደት ክብረ በዓላት ውስጥ አንዱ ነው Green (1997, 270) ፡፡ ይህ ክብረ በዓል ሰዎች ከብቸኝነት ወደ ጥንድነት መምጣታቸውንና ቤተሰብ መመስረታቸውን ምክንያት አድርጎ ይከወናል፡፡ ሠርግ የከምባታ ማህበረሰብ ከሚከውናቸው ታላላቅ ማህበራዊ በዓላት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማወቅ በመረጃ መስብስብ ወቅትም ይሁን በማንኛውም አጋጣሚ ለክዋኔው ፣ ለአውዱ እና ለቋንቋ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለአውዱ ትኩረት መስጠት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት የአንድን ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ በአለባበሱ ፣ በአመጋገቡ ፣ በአኗኗሩ ፣ በቤት አሰራሩ፣ በክዋኔውና በሌላው የተለየ ስለሚሆን ነው፡፡

ባህል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆነ የወል ሀብት ነው ፡፡ ይህ የወል ሀብት ማህበረሰቡ አምኖበት ተቀብሎት የሚተገብረው ነው ፡፡ ታዲያ የከምባታ ማህበረሰብም የራሱ የሆነ የእኔ የሚለው የባህል ባለቤት ነው ብሎ ከሚያከብራቸው ታላላቅ ባህላዊ ክንዋኔዎች ውስጥ የሠርግ ስነ-ስርዓት (የጋብቻ ስነ-ስርዓት ) አንዱ ነው ፡፡ ይህ ጥናትም ያተኮረው የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ላይ ነው ፡፡

## 1.2 አካባቢያዊ ዳራ

የከምባታን ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ የመጀመሪያዎቹ የብሄረሰቡ ሰባት ጉሳዎች በአካባቢዉ ትልቅና እምብርት በሆነው አምበርቾ ተራራ ላይ ይኖሩ ነበር ፡፡ እነዚህ ሰባት ጎሳዎች ኤቤጄና ፣ ኤፌጌና ፣ ሂኒራ ፣ ጠዛ ፣ ጎርማ ፣ ፉጋና ጋዴና ናቸው ፡፡ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ጎሳዎች ከአማራ ፣ ከሲዳማ ፣ ከወላይታ ፣ ከሀድያ ከጉራጌ ፣ ከኦሮሚያ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አምበርቾ ተራራና አካባቢው እንደመጡ ይነገራል ፡፡ ባጠቃላይ የከምባታ ብሄረሰብ ወደ ሶስት መቶ የሚደርሱ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመጡ ጎሳዎችን ያካተተ ነው ፡፡ የአመጣጡም ምክንያት ከአካባቢው ለምነት የተነሳ አምበርቾ በደን የተሸፈነ መሆኑ ለአራዊት መኖሪያነትና ለፍራፍሬ ለቀማ የሚመች በመሆኑ በማህበራዊና በጋብቻ ግንኙነት በፖለቲካ ሁኔታዎች ማለትም ከጦርነትና ከሌሎች ችግሮች ለመሸሽ ሲባል ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ብሄረሰቦች መቀላቀላቸው ለምሳሌ ፡-

ከሰሜን ኢትዮጵያ በድሮ ተንቀሳቃሽ መንግስታዊ አገዛዝ ወቅት የመጡ ነበሩ (ፈለቀ ብርሀኔ 2009) ፡፡

የከምባታ ጠንባሮ ዞን በደቡብ ብሄረበቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ አስራ አራት ዞኖችና አራት ልዩ ወረዳዎች አንዱ ሆኖ በሰባት ወረዳዎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ነው ፡፡ የብሄረሰቡ አፍ መፍቻ ቋንቋ ከምባትኛ ነው ፡፡ ቋንቋው ከኩሽ ቤተሰብ ይመደባል ፡፡ ከምባትኛ ከጠንባሮ ፡ ከአላብኛ ከሀድይኛ ፡ ከቀቤንኛ ፡ ከሲዳምኛ እና ከሌሎች ኩሽ ቋንቋዎች ጋራ ይዛመዳል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ከምባትኛ የንግድ ልውውጥ ቋንቋ በመሆን ያገለግላል ፡፡ ከ1995 ዓ/ም በፊት በደርግ ዘመነ መንግስት ለመሰረተ ትምህርት ማስተማሪያ መጽሀፍ በሳባ ፊደል ተጽፎ ጥቅም ላይ ውሎ ነበር ፡፡ ነገር ግን የብሄረሰቡ ምሁራንና የትምህርት ባለሙያዎች ሳይንሳዊ በሆነ አኳኃን ጥናት አካሂደው ሳባ ፊደል ገበታ በቋንቋ አገባብና አገላለጽ መርህ መሰረት የተፈለገውን ያህል ውጤታማ ባለመሆኑ ከ1985 ወዲህ የፊደል አጻጻፍ በላቲን እንዲሆን ተወስኖ አሁን ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ዱራሜ የዞኑ ዋና ከተማ ሲሆን ከአዲስ አበባ በሻሸመኔ 352 ኪ.ሜ በሆሳና በአንገጫ ደግሞ 286 ኪ.ሜ ሲሆን ከክልሉ ዋና ከተማ ከአዋሳ 125 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል ፡፡ ብሄረሰቡ በአራቱም አቅጣጫ የሚያዋስኑት የተለያዩ ወረዳዎችና ዞኖች አሉ፡፡ በምስራቅ በኩል አላባ በምዕራብ ኦሞ ወንዝ ፣ በደቡብ ሀድያና ወላይታ ዞን በሰሜን ሀድያ እንደሚያዋስነው ከዞኑ ስነ ህዝብ ቡድን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የብሄረሰቡ የህዝብ ብዛት 630.236 እንደሆነ (የህዝብና የቤቶች ቆጠራ እስታትስቲክ 1999) ይጠቁማል ፡፡

የዞኑ የቆዳ ስፋት 15.236 ካሬ ኪሎ ሜትር ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ800-3028 ሜትር ነው ፡፡ ዝቅተኛው ደግሞ ከፍተኛ የሙቀት መጠኑ እስከ 30 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ አካባቢ ነው ፡፡ አብዛኛው ህዝብ በጥግግት የሰፈረው በወይና ደጋና ደጋ አካባቢ ሲሆን ቆላው አካባቢ የተበታተነ አሰፋፈር ይታያል ፡፡ በዚህ ጥግግት ረገድ ሲታይ በዞኑ በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ከ490 ስው በላይ ሰፍሮ ይገኛል (የከምባታ ጠምባሮ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ዓ/ም ያልተገለጸ ጥራዝ) ፡፡

የከምባታ ብሄረሰብ ዋነኛ መተዳደሪያ እርሻ ነዉ፡፡ ይሄውም ካለው ህዝብ 85% በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ሲሆን ቀሪው 15% የሚሆነው ህዝብ በንግድና በሌሎች የሥራ መስኮች እንደሚተዳደር የወረዳው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት መረጃ ያሳያል፡፡ እርሻዉን የሚያከናውነው በበሬ በማረስ ሲሆን ለጓሮ አትክልት ሥራ ‹‹ክልታ›› በሚባል እጀታው እንጨት ሆኖ ጫፉ ከብረት የተሰራ መቆፈሪያ መሳሪያ በመጠቀም ይገለገልበታል፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች በመጠቀም በቆሎ ፣ ስንዴ ፣ ጤፍ ፣ ጉደሬ ፣ ድንች ፣ ቡና በርበሬ ፣ ገብስ ፣ አተር ፣ ቦሎቄ ፣ ማሽላ ፣ ወዘተ ያመርታሉ፡፡

### 1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ የሚደረግ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ለማጥናት የተመረጠበት ምክንያት አካባቢውን ፣ ብሄረሰቡን እንዲሁም ባህሉን ከማስተዋወቅ አንጻር የራሱ የሆነ የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው በማመንና ባህላዊ የጋብቻ ክዋኔውና ቃላዊ ግጥሞች ፣ ስርአቱን ለማስፈጸም የሚጠቀሙት አገላለጾች እየጠፉና እየቀነሱ በመሄዳቸው ተንትኖ ለመሰነድ በማሰብ ነው ፡፡

ሌላው ባህል ሁሌም በለውጥ ሂደት ውስጥ ስለሆነ የከምባታ ባህላዊ ጋብቻ በአሁን ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች በሃይማኖት በዘመናዊነት በየጊዜው በሚቀያየረው የአኗኗር ዘይቤ ቀጣይነቱ ላይ አደጋ እየተጋረጠበት ነው ፡፡ ስለዚህ የጋብቻውን ስርኣት ከነቋንቋ አጠቃቀሙ ተንትኖ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ነው ፡፡

### 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓትና በስነ ስርዓቱ ላይ የሚደረጉ የቋንቋ አጠቃቀሞችን መተንተን ነው ፡፡ ይህንን ዓብይት ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተለይተዋል ፡፡

1 የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን ፡፡

2 የጋብቻ ስርዓት ክወና ትዕምህርታዊ የቋንቋ ውክልና መግለጽ ናቸው ፡፡

## ዋና የምርምር ጥያቄዎች

1/ ይህ ጥናት የሚያተኩረው የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም ምን ይመስላል ?

2/ የጋብቻ ስርዓት ክወና ትምዕርታዊ የቋንቋ ውክልና እንዴት ይገለጻል ?

የሚል አበይት ጥያቄዎችን በመያዝ የሚከተሉትን ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል ፡፡

## ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች

1 የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት ማስፈጸሚያ የቋንቋ አጠቃቀም ምን ይመስላል ?

2 የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ ውክልና ያላቸው ክዋኔዎች የትኞቹ ናቸው ?

3 የክዋኔዎቹ ቋንቋ እንዴት ይገለጻል ?

4 በቀጥታ ከሚገለጸው ሀሳብ ባሻገር የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድን ?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እነሱም

- የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓትና በስርዓቱ ላይ የሚነገሩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በመተንተን ይዘትና ቅርጹን ሰንዶ ለቀጣይ ትውልድ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- ቀጣይ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እንደ መነሻ ሊያገለግላቸው ይችላል ፡፡
- የከምባታን ባህሉንና ቋንቋውን ማሳደግ ለሚፈልጉ መረጃ በመስጠት እገዛ ሊያደርግ ይችላል ፡፡
- የማህበረሰቡን የአኗኗር ስርዓትና ባህላቸውን ለፊልምና ለሙዚቃ ኢንዱስትሪ ግብአት በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይጠበቃል ፡፡

### 1.6 የመስክ መረጃ አሰባሰብ ሂደት

ማንኛውም ተመራማሪ የጥናት አካባቢ ወይም መስክ ሄዶ ጠቃሚ መረጃዎችን ሊያሰባስብ ይችላል ፡፡ ሆኖም ጥናቱ መጀመር ያለበት በቤተ መጽሀፍት በመገኘት ነው፡፡ እናም ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በቤተ መጽሀፍት ንባብ በማድረግ ተጠኚውን ቡድን በተመለከተ መጣጥፎች ይኖሩታል ወደ ተባለበት በመሄድና ተውሶ በማንበብ አጥኚዋ ወደ መስክ አመራች ፡፡ ከከምባታ ጠምባሮ ዞን ዱራሜ ቤተ መጻህፍት ፣ ከከምበታ ጠምባሮ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ፣ ከግለሰቦች ፣ ከቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ቤተ መጽሕፍት ፣ ከዳምቦያ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት ቤተ መጽህፍት መጽሀፍ በመዋስ እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ካምፓስ ርዕሱን አስመልክቶ አስቀድሞ ንባብ ተካሂዷል ፡፡

ለዋናው ጥናት የመስክ ስራ መረጃ ለማሰባሰብ ያቀደችው ከየካቲት 8/2010 ዓ/ም ጀምሮ ነው ፡፡ ወደ መስክ ከመሄዷ በፊት የከምባታ ጠምባሮ ዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ መሄድ ነበረባት ፡፡ ምክንያቱም ከወረዳው እውቅና ዉጪ ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ ገብቶ ጉዳዩን ለማጥናት መሞከር የተሳሳተ ትርጉም ያሰጣል በሚል ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ለዞኑ ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ሀላፊ የመጣችበትን ዓላማ በዝርዝር አስረዳች ፡፡ በከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት ላይ ለማጥናት መነሳቷን አድንቀው ማንኛውንም ትብብር በማድረግ እንሚተባበሯት ቃል ገብተው በአጥኚዋ ጥናት ዙሪያ የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች ማግኘት እንደሚገባት ጥቆማ ሰጧት ፡፡ ባለሙያዎቹን ይዛ መረጃዎችን እንዴትና መቼ እንደምታገኝ አማከረቻቸው ፡፡ ለጥናቱ በተመረጡ ቀበሌዎች ውስጥ የባህል እውቀት ያላቸው እነማን እንደሆኑ ጠየቀቻቸው ፡፡ እነሱም እነማንን ማናገር እንደሚገባት የየጎሳ ውክልና ተሰጥቷቸው በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ ከህብረተሰቡ የሚነሱ ማንኛውንም ግጭት የሚፈቱ ባህላዊ ዳኞች በብሄረሰቡ አጠራር ‹‹ኮካታ›› የመረጃ ምንጭ ብታደርጋቸው ውጤታማ እንደምትሆን ጠቆማ በመስጠት ተባብረዋታል፡፡

ከሁሉም በላይ አንድ ተመራማሪ ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት መስክ ሄዶ ስለሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ እና ስለአካባቢው መጠነኛ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል ፡፡ በርግጥ አጥኚዋ የሥራ አካባቢዋ በመሆኑ ስለአካባቢው አየር ንብረት ሁኔታ ደጋ ፣ ወይና ደጋ ፣ ቆላ ፣

በረሃ ፣ መሆን አለመሆን ለመለየት ችግር አልገጠማትም ፡፡ ስለአልባሳት ፣ ስለምግብ ፣ ስለተላላፊ በሽታዎች ፣ መርዛማ ነፍሳት ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ መኖር አለመኖር ቀደም ብሎ ማወቁ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጎ እንዲንቀሳቀስና መልካም ግንኙነት ለመፍጠር አስችሏታል ፡፡

መጋቢት 5/2010 ዓ/ም በባህላዊ ጋብቻ ስርዓት ጋብቻ የሚፈጽሙ ተጋቢዎች እንዳሉ በቅኝት ጥናት ወቅት ስለተረዳች ወደ ስፍራው በመሄድ የጋብቻ ስርዓቱን መመልከትና መቅረጽ መቻሏ ለጥናቷ ከፍተኛ እገዛ አድርጎላታል ፡፡

ሌላው በቃለ መጠይቅ ወቅት ቁልፍ መረጃ አቀባዩች ጋር በመሄድ መረጃዎችን መሰብሰብ ነበር ፡፡ ለዚህም ከመስፋቱ በስተቀር ለሚፈለጉ ጥያቄዎች ምላሽ ተገኝቶ በመቅረጸ ድምጽና በማስታወሻ ተይዟል ፡፡ ቃለ መጠይቆቹም ዝግጁና ኢዝግጁ ሲሆኑ ትኩረት የተደረገው የጋብቻ እሳቤ ፣ ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች ፣ ስርዓታዊ ሂደት በሂደቱ ላይ የሚነገሩ የሀሳብ ልውውጦች ምን እንደሆኑ ያጠነጠነ ነበር ፡፡ የቀረበውም ቃለመጠይቅ ሲጠናቀቅ ፍቃደኛነታቸው ተረጋግጦ ፎቶ ተነስተዋል ፡፡

በመቀጠል የተደረገው በምልከታና በቃለ መጠይቅ ወቅት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለማረጋገጥ ቡድን ተኮር ውይይት ማድረግ ነበር፡፡የቡድን ውይይት የመረጃ አሰባሰብን በተመለከተ አንደኛው ዘዴ የባህል እውቀት ያላቸው ‹‹ኮካታ›› ተሰብስበው መገኘት ለማወያየት መረጃ ለማግኘት አመቺ መንገድ ነበርና በሚሰበሰቡበት ስፍራ ሄዳ የትብብር ደብዳቤ በማሳየት አላማዋን ግልጽ አድርጋ ፈቃደኝነታቸውን ጠየቀቻቸው፡፡ እነሱም በአላማዋ ከመደሰታቸው የተነሳ ለረጅም ደቂቃ ሲመርቋት ከቆዩ በኋላ በመደበኛ ከሚሰበሰቡበት ሰኣት ውጪ የሚመቻቸውን ቀን ነግረዋት ሚያዚያ 2/2010 ቡድኑን እየመራች በማወያየት መረጃ መውሰድ ችላለች፡፡ሁለተኛ የባህል እውቀት ያላቸው ሴቶች፣የባህል ባለሙያዎች ዘጠኝ ሰው ያሳተፈ ቡድን በማደራጀት ግንቦት 8/2010 በቡድን ውይይት በመቅረጸ ድምጽና በመቅረጸ ምስል መረጃ ተሰብስቧል፡፡

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሳቦች

### 1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማጥናት ስትነሳ የሚከተሉት ችግሮች አጋጥመዋታል፡፡

- መረጃ አቀባዮች በተቀጠሩት ሰዓትና ቀን ያለመገኘት ፡፡ ጥናቱን በተፈለገ ጊዜ ለማጠናቀቅ አዳጋች ሆኖ ነበር ፡፡
- ርዕሱ ሰፊና ሊጠና የሚገባው በመሆኑ፤ ማህበረሰቡም እንዲታወቅለት ከመጓጓት ጋር ተያይዞ በቃለ መጠይቁ ከተነሳው ጥያቄ ላይ ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ ፣ አንዱ ሲነሳ ሌላውን እየመዘዘ ሲናገሩ ከውስጣቸው ነበርና ላለማቋረጥ ሲባል ይሸፈናል የተባለው ጊዜ ለመሄድ አለመቻል ፈታኝ ሆኖ ነበር ፡፡
- ባህልን ያህል ሙሉ በሙሉ ከማህበረሰቡ ጋር የሚያነካካን ጥናት በቀላል ገንዘብ ማጥናት ፡፡ ያዳግታልና ይህም በጥናቱ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡
- መረጃ አቀባዮቹም "ከእኔ በላይ ለአሳር" ማለትም ሁሉን ነገር እኔ አውቀዋለሁ ወደ ሌሎች መረጃ አቀባዮች አትሂጂ የማለትም ችግር ነበር ፡፡

**የተወሰዱ እርምጃዎችና የመፍትሔ ሀሳቦች**

- ደጋግሞ በትግዕስት ቀጠሮ በመያዝ ከመረጃ አቀባዮች ጋር ለመገናኘት ተሞክሯል ፡፡
- የገጠመውን የገንዘብ ችግርም በተለይ ለቀረፃ የሚውሉ መሳሪያዎችን ከት/ቤት በመዋስና በሚፈልጉት ሰዓት በመስጠት ችግር ለማቃለል ጥረት ተደርጓል ፡፡
- የብሔረሰቡን ባህል፤ ወግ፤ ልማድ እኔ አውቀዋለሁ ያሉትን መረጃ አቀባዮች ሀሳባቸው ሳይነቀፍ ሳይደገፍም ያለመሰልቸት በተደረገው ጥረት የሚፈለገውን መረጃ ከሌሎች መረጃ አቀባዮች ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል ፡፡
- በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ወቅት ባህላቸውን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ ቢወስድም ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል ፡፡

## 1.8 የጥናቱ ወሰን

በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከምባታ፣ ጠምባሮና ዶንጋ የተባሉ ሶስት ብሄረሰቦች ይኖራሉ፡፡ ይህ ጥናት በከምባታ ላይ ያተኮረ ሲሆን የብሄረሰቡን ባህላዊ የጋብቻ ስርዓትና በስርዓቱ ላይ

የሚደረጉ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ብቻ ይመለከታል፡፡ የከምባታ ብሄረሰብ በስድስት ወረዳና በአንድ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚኖር ሲሆን ወረዳዎቹም፡- ዳምቦያ፣ ቀዲዳ፣ ሺንሺቾ፣ ሀደሮ ዶዮገና እና በዱራሜ ከተማ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በዳምቦያ ወረዳ በተመረጡ ስድስት ቀበሌዎች ብቻ ሲሆን ቀበሌዎቹም ዳምቦያ 01 ፣ ዳምቦያ 02፣ ቃዛላ፣ ቦንጋ፣ ገርባ፣ ገረምባና አምበርቾ ናቸው ፡፡ ቀበሌዎችም የተመረጡበት ምክንያት አጥኚዋ የምትኖርበት አካባቢ ስለሆነና መረጃ ለማሰባሰብ አመቺ ስለሚሆን ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

#### 2.1.1 የባህል ምንነት

ባህል ማለት ማህበረሰቡ በጋራ ያዳበሩትን የዕውቀት ክምችት፣ አስተሳሰብ፣ ልማዳዊ ባህሪያት ሲሆን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል ይሉታል፡፡ (Raph Linton (1940) Ward (1957)) ባህል አንድ ማህበረሰብ በየጊዜው የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ በማህበራት የሚከወኑ ቁሳቁሶች እና የማህበራዊ ተራክቦዎች መግለጫ ባህሪያት ናቸው በማለት ይበይኑታል፡፡ እነዚህ ተጠቀሱ እንጂ የባህል ምንነትን አስመልክቶ በርካታ ብያኔዎች ተሰጥተዋል፡፡

ባህል የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በባህሪው ሰፊና ሁሉን አቀፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በ1982 በሜክሲኮ ከተማ በዩኔስኮ አማካኝነት በተካሄደው ጉባኤ በተደረሰበት ስምምነት መሰረት፣ ባህል የሰው ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻሉ ወይም ከሌሎች ፍጡራን ለመለየት ያበቁን ማንኛዎቹም ምሁራዊ፣ ስነ-ምግባራዊ፣ አካላዊ፣ ቴክኒካዊና ሌሎችም ስራዎች ሁሉ እንዲሁም የሰው ልጅን በመማር፣ በሞራል፣ በቴክኒክና በአዕምሮ ዕውቀት ራሱን የማሰልጠን ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ህዝብ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅባቸውን ሁኔታዎች ማለትም የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ እምነቶቹን፣ ትውፊቶችን፣ በአጠቃላይም ቁሳዊና ህሊናዊ ሀብቶቹን የሚያካትት ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነው (የኢፌደሪ የባህል ፖሊሲ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር 1990) ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ባህል ሰዋዊ የሆነና ከሰው ልጆች ህይወት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው ያመለክታል፡፡ ህዝቦች አንዱ ከሌላው የሚለዩበት የየራሳቸው የባህል እሴቶች እንዳሏቸው ያስረዳል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የዩኔስኮን የባህል ትርጉም መሰረት በማድረግ ባህል ማለት የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አንዱ ከሌላው የሚለዩበትን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነምግባራዊ፣ ኃይማኖታዊና ስነልቦናዊ ሁኔታዎችን ወይም ቋንቋቸውን ታሪክና

ስነቃሎቻቸውን፣ ቤት አሰራራቸውን፣ የማምረቻ መሳሪያዎቻቸውንና አመጋገባቸውን ልብስና አለባበሳቸውን፣ አጋጌጣቸውንና የስነውበት ግንዛቤያቸውን፣ ሃይማኖታዊና የእምነት ክንዋኔዎቻቸውን፣ ከወሊድ ከሠርግና ከሞት ጋር የተያያዙ ስርዓቶቻቸውን፣ በዝምድና በጉርብትናና በሌሎችም ግንኙነቶች ላይ የተመሰረተ መተጋገዝና መተሳሰባቸውን፣ ባህላዊ የጤና እንክብካቤ ዘዴዎቻቸውንና ሌሎችንም ሁሉ የሚያጠቃልል ነው (የኢፌዲሪ የባህል ፖሊሲ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር 1990) ፡፡

ከላይ በተገለፀው ሀሳብ መሰረት ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች ህዝቦች ሀገር ናት፡፡ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ ባህሎችና ቋንቋዎች አሏቸው፡፡ በዚህ ርዕስ ተጠኚ ቡድኖቹ የጋብቻ ስነ ስርኣት የሚፈፅሙት በብሔረሰቡ ባህል መሰረት በመሆኑና ባህሉንም ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ባህሉን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ይህ ጥናት በባህል ጥናት መስክ ስር ተካቷል፡፡ በባህል ብያኔ ስር ከሚመደቡ በርካታ ርዕስ ጉዳዮች ውስጥ የባህላዊ የሠርግ ስርዓት አንዱ ነው፡፡

### 2.2.2 ክብረ በዓል

ክብረ በአላትን የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት በየደረጃው የሚገኙና ከወትሮ ለየት የሚሉና ማህበራዊ ክስተቶችንና አጋጣሚዎችን ለማብሰር የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሕይወት መሀል ልደት፣ ክርስትና፣ ግርዛት፣ ጉርምስና ጋብቻ እንዲሁም ሞት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው ፡፡ በመሆኑም እነዚህ የሽግግር ወቅቶች ደማቅ በሆነ የበዓል ስርዓትን ያከናውናል፡፡ በክብረ በዓላትና በበዓሉ የሚፈጸሙ የተለያዩ ስርዓቶች አማካኝነት አንድ ግለሰብ ካንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው መሸጋገሩን ሲያበስር ግለሰቡ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ክብር እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ቦታ ከፍ ይላል፡፡ ለምሳሌ የጋብቻ በዓል ብንመለከት በእለቱ በሚፈጸመው በዓል አማካኝነት የማህበረሰቡን ባህል ከማሳወቅ በተጨማሪ በዚያ በዓል ማብሰሪያነት ሙሽሮቹ ከወጣትነት ሀላፊነት ወደ መቀበል ደረጃ ለውጥ መሸጋገራቸውን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ይህንን የሽግግር ወቅት ደማቅ በሆነ የበዓል ስነ ስርዓት ያከብሩታል፡፡ በክብረ በዓሉ ላይ የተለያዩ ስነ ስርዓቶች ግለሰቡ እያደረገ ያለውን ማህበራዊ ሽግግር የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው

(Martha and Marthine;2005;94) :: የከምባታ ባህላዊ ጋብቻ ስርዓትም ከባድ ሀላፊነትን የሚያስረክቡበት ስለሆነ ደማቅ በሆነ የበዓል ስነ ስርዓት ያከብሩታል፡፡ ይህንን ስርዓት ሲያስፈጽሙ ቋንቋ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለ ቋንቋ ክዋኔ ህይወት የለውም፡፡ ስለዚህ አጠኚዋ በሚከወነው ሂደት ውስጥ በቋንቋ አማካኝነት የማህበረሰቡን በጾታ፣ በዕድሜ፣ የማህበራዊ ደረጃውን፣ አመለካከቱን መመርመር ያስችላታል ፡፡

### 2.2.3 የበዓል ስነ ስርዓት

ሁለት አይነት የበዓል ስነስርዓቶች መኖራቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህም የከፍተኛ አውድ የበዓል ስነስርዓትና የዝቅተኛ አውድ የበዓል ስነስርዓት በመባል ይታወቃል፡፡ የዝቅተኛ አውድ የበዓል ስነስርዓት የምንለው ከዝግጅት አስቀድሞ የማይነገር ዕቅድና ዝግጅት የማይጠይቅ በታዳሚዎች ሆነ በከዋኝ ብዙ ጊዜ የማይሰጠው በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከወን የበዓል ስነስርዓት ነው፡፡ የከፍተኛ አውድ የበዓል ስነስርዓት የምንለው ግን አንዳች ዓላማን ለማሳካት ተብሎ በተለይ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ለየት ያሉ የሕይወት አጋጣሚዎች ለማብሰር የሚዘጋጅ አስቀድሞ ለህዝብ የሚነገርና የሚታወቅ ሰፋ ያለ ዝግጅትን የሚጠይቅ የበዓል ስነስርኣት ነው (Martha and Marthine 2005;99):: ከዚህ ሀሳብ መነሻ የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ስነስነስርዓት የከፍተኛ አውድ የበዓል ስነ ስርዓት ውስጥ ልናካትተው እንችላለን፡፡

### 2.2.4 ጋብቻ (ሠርግ)

ጋብቻ(ሠርግ) ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ መሸጋገሪያ ሲሆን የአንድ ቡድን አባል የሆነ ሰው ከወጣትነት ወደ ቤተሰብ ወደ ማስተዳደር ወይም ወደ ሀላፊነት የሚሸጋገርበት ነው፡፡ የጋብቻ ክብረ በአሉ ይህንን ሽግግር ለማብሰር የተወሰኑ ቡድኖች የሚሳተፉበት የመከወኛ ጊዜና ቦታ ያለው ግለሰቡ ያደረገውን ሽግግር በድምቀት ማብሰሪያ ነው፡፡በጋብቻ ክብረበኣል ላይ ሙሽሮቹና እድምተኞቹ የሚለብሷቸው አልባሳት ፣ጌጣጌጦች፣የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች ፣የተለያዩ ባህላዊ እቃዎች በሰርጉ ቀን የሚጨፈሩ የተለያዩ ጭፈራዎች ባጠቃላይ የሰርጉ ቀን የሚከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶች እየተከናወነ ያለውን ማህበራዊ ሽግግር የሚጠቁሙ እንዲ እንዲሁ ያለምክኒያት የሚፈጸሙ ድርጊቶች

አይደሉም (Martha and Marthine 2005;97) ፡፡ በከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ የሚከናወኑ ማንኛውም ተግባራት ከሙሽራው ሙሽሪት ልብስ አለባበስ ስርዓት ጀምሮ እስከ ጫጉላ ቤት እስኪገቡ ድረስ ያለው ክዋኔ በገለጻ (በትረካ) ፣ በዘፈን ፣ በከበሮ ወዘተ የታጀበ ነው፡፡ ይህንን በክዋኔው ስርዓት የሚባሉ የቋንቋ አጠቃቀሞች በአውዱ መሰረት ተገልጸዋል፡፡

### 2.1.5. የጋብቻ ምንነት

ሰው ለተፈጥሮ የሚገዛ ፍጡር ነዉ፡፡ በሰዎች መካከል የተቃራኒ ፆታ ስሜት በጣሙን ከፍተኛ በመሆኑ ወንድና ሴት ይህን ስሜት ለማርካትና ዘራቸውን ለማቆየት ይተሳሰራሉ፡፡ ይህ ክስተት ለእንስሳት የሚሰራ ቢሆንም እንስሳት እንደ ሰው ጎጆ አይቀልሱም፡፡ ይህ አንዱ የኑሮ መስመር የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን ጥንዶች ከነበሩበት በወጣትነትና ጎጆ ለመቀለስ አንድ አምሳል አንድ ስጋ ሆነው የሚኖሩበትና ማህበራዊ ህይወት መመስረት የጋራ ኑሮ መኖር የሚጀምሩበት ነው ፡፡

ጋብቻ ፈጣሪ ያዘዘውና ከእናትና ከአባት ፍቅር እንኳን የሚበልጥ በውስጡ አንዳች ልዩ ኃይል እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህንን ልዩ ኃይል ያለውን ጋብቻ ለመፈጸም የሚደረጉ ልዩ ክብርና ስርዓት ክዋኔ የቋንቋ አጠቃቀም እንደ ብሔረሰቡ ይለያያል፡፡ በማንኛውም ማህበርሰብ የሚፈጽሙ ጋብቻዎች ማህበራዊ ተቀባይነት ያገኑ እና ማህበረሰቡ አምኖ እየተገበረው የሚገኝ ትልቅ እሴት ነው፡፡ በሀገራችን እኩል እውቅና እና ህጋዊ ከለላ ያላቸው የጋብቻ አይነቶች አሉ፡፡

**በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ፡-**ጋብቻ በክብር ሹም መዝገብ ፊት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻን ለመፈፀም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ሁለቱንም ስምምነት አምኖበት ፍቃዳቸውን ሲቀበሏቸውና የክብር ፊርማውን አስቀምጦ ሁለቱ አንድ መሆናቸውን ሲያረጋግጥላቸው ጋብቻው ተካሄደ ይባላል፡፡

**በኃይማኖታዊ ስርዓት መሰረት የሚፈጸም፡-**በኃይማኖት ስርዓት መሰረት ተፈጸመ የሚባለው ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በኃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንዳቸው

ኃይማኖት የሚፈጸም እና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገው ስርዓት መፈፀም ነው፡፡

**ባህላዊ ስርዓት የሚፈፀም ጋብቻ፡-** የዚህ ጋብቻ አፈፃፀም ደግሞ ከብሄር ብሄር እንዲሁም ከባህል ባህል የሚለያዩ ናቸው፡፡ ጋብቻ በባህላዊ ስርዓት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሰረት የሚፈፀምእና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ስርዓት ስፈፅሙ ነው፡፡

በአጠቃላይ ( በፍታብሄር ህግ 1952፣123) ፡፡ ትዳር ወይም ጋብቻ በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ ያለና የሚኖር ትልቅእሴት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ህጋዊነቱን አምኖበትና ተረጋግጦ በወንድና በሴት መካከል የሚከናወን ዖታ ተግብር ነው በማለት አስቀምጧል፡፡ ጋብቻ የሚፈፀምበት ጊዜ ያለው የደስታ እና የብሩህ ገፅታ መገለጫ ስርዓት እንዳለው ሁሉ ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ከጋብቻ አይነቶች ውሰጥ ባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ በከምባታ ማህበረሰብ ዘንድም በተላያየ መንገድ የሚከወኑ የጋብቻ አይነቶች ያሉ ሲሆን አጥኚዋ ትኩረት የምታደርገው በባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ላይ ነው፡፡

## 2.2 የቋንቋ ምንነት

ባህል ተለዋዋጭና ቋሚ ያልሆነ የማህበረሰብ ንብረት ነው፡፡ ቋንቋም እንደ ባህል ተለዋዋጭ በመሆኑ በየጊዜው እየገነባንና እያዳበርነው የሚኖር ነው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ ማህበራዊ መገለጫዎች በጊዜ ሂደት ከተፈጥሮ አደጋና ከሰው ሰራሽ አደጋዎች ጋር ቀን በቀን ይፋለማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ በአንዱ ላይ በሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት አንዱ ቋንቋ ወይም ባህል የመበረዝ የመጥፋት ወይም በሌላ መዋጥ ዕድል ሊገጥመው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ቱባ ባህሉና ቋንቋ ቀድሞ ካልተጠና ነባሩን ባህል ለማወቅ በጣም አዳጋች ይሆናል፡፡ የማህበረሰቡ ቱባ ባህል አልታወቀም ማለት ደግሞ ማህበረሰቡ ማንነቱ አልታወቀም ማለት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ቋንቋና የባህል ክፋዮች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ሊጠኑ ይገባል (liukun 2013:1) ::

እንደሚታወቀው የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ እና መለያ ተብለው ከሚጠቀሱት ነጥቦች አንዱ እና ዋንኛው ቋንቋ ነው፡፡ በቋንቋ ውስጥ የማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ እና ስርዓቶች

አሉ፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለዉን የቆየ ትስስር፣ አብሮነት እና አንድነት ያመለክታል፡፡ እንግዲህ አንድ ቋንቋ ሲሞት /ሲጠፋ/ የማህበረሰቡ እሴቶችም አብረው ይጠፋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ማህበራዊ ቀውስ እንዲፈጠር፣ ስነ ልቦናዊ ኪሳራ እንዲደርስ፣ የእኔነት መጥፋት እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ቋንቋን ከአንድ ማህበረሰብ ባህላዊ መስተጋብር እና እሴት ነጥሎ ማየት የማይቻል ነው፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ የማህበረሰቡ ባህል መገለጫ ነውና (liukun 2013:2)፡፡

ቋንቋና ማህበረሰብ ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ቋንቋ ያለሰው መኖር አይችልም፡፡ የሰው ልጅም የየዕለት ኑሮውን የበለጠ የተሻለ እንዲሆን ከቢጤው ጋር ሃሳብ የሚለዋወጥበት ቋንቋ የግድ ያስፈልገዋል፡፡በቋንቋና በማህበረሰብ መካከል ያለውን ትስስር ስንመለከት በሁለቱ መሃከል የገላጭና ተገላጭነት ዝምድና እንረዳለን፡፡ ይህም ማለት ቋንቋ የማህበረሰብ ገላጭ ሲሆን ማህበረሰብ ደግሞ ተገላጭ ይሆናል ማለት ነው (Liukun 2013:3) ፡፡

በሌላ አባባል ደግሞ ቋንቋ የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እውቀት፣ ኪነ ጥበብን፣ ስነቃሎችን፣ ባህላዊ ዕምነቶችን፣ አፈታሪኮችን፣ ተረቶችን እንዲሁም ሰዎች በማህበር ሲኖሩ ያካበቷቸውን ችሎታዎች እና ዕውቀቶች ሁሉ መገለጫ ነው፡፡ ስለሆነም የአንድ ማህበረሰብ ቋንቋ ለአደጋ ተጋለጠ ወይም አደጋ ላይ ወደቀ ማለት እነዚህ ባህላዊ ዕውቀቶች እና ትውፊቶችም አብረው ለአደጋ ይጋለጣሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ቋንቋና የባህል ክፋዮችን ማጥናት እነዚህን ባህላዊ ዕውቀቶች ለመታደግ ይጠቅማል (Liukun 2013:4)፡፡

### 2.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም

አንድ ማህበረሰብ መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ እሴቶች ተጠብቀው ቀጣይ በሆነ መልኩ ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ ቋንቋ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ከዚህ ሌላ የማህበረሰቡ አባላት የሚፈልጓቸውን ጥሩና ክፉ የሚሏቸውን ስነ ምግባሮች እንዲለዩ ቋንቋ በመጠቀም ከማህበረሰቡ ይማራሉ፡፡ የማህበረሰቡ አባላትም በውስጣቸው መጥፎ ስነ ምግባር ሲያገኙ አባላቱን ለማስተማር ቋንቋን በመሳሪያነት ይገለገላሉ፡፡ይሄውም በምሳሌያዊ አባባሎች፣

በተረቶች፣በቃል ግጥሞች፣ ወዘተ... በመጠቀም ማህበረሰቡ ውስጥ መጥፎ ምግባር ያለውን አባል ከችግሩ እንዲመለስ ያደርጉታል፡፡ስለዚህ ቋንቋ ማህበረሰቡን የሚያገለግል ስለሆነ ማህበራዊ ይዘት ያለው ነው፡፡ቋንቋ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ ውጤትም ነው፡፡ ከላይ የተገለጸው አበባላቱን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰቡን በሚያደርጋቸው የዕለት ተዕለት ግንኙነት ግጭቶች ይፈጠራሉ Fairclaugh N.(1995)፡፡ይህ የቋንቋና ባህል ትስስር የቋንቋና ህብረተሰብንም ግንኙነት ያመለክታል፡፡ ይህን በቋንቋና ህብረተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠና የስነልሳን ዘርፍ ደግሞ ማህበራዊ ስነልሳን ይባላል፡፡ በቋንቋ አገልግሎት ላይ ያተኩራል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀምንም ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያጠናል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ማህበራዊ ልማድ አንዱ ነው፡፡የቋንቋ አገልግሎት ብዙ ነው፡፡ አጠቃቀሙም እንደዚሁ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በፆታ፣ በዕድሜ፣ በዝምድና፣ በግንኙነት፣ በቅርበትና ርቀት በማህበራዊ ደረጃ ወዘተ. የተለያዩ ናቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ የማህበረሰቡ አባላት በቋንቋቸው በተለያዩ መንገዶች እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ፡፡ሰዎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ በቋንቋ ግንኙነት ማድረጋቸው አይቀሬ ነው፡፡ሰዎች ከሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት፣ የችግራቸውን ለመረዳትና ችግሮቻቸውንም በጋራ ለመወያየት የሚፈጸሙት በቋንቋ ነው፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜም አንድም ሲግባቡ አልያም ሳይግባቡ መቅረታቸው ያለ ነው፡፡ አለመግባባትን ከመሚፈጥሩት ምክንያቶች አንዱ የቋንቋ አጠቃቀም ችግር ነው፡፡ቋንቋን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ሰዎች በአንድ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት በአዲስ እንዲቀይሩ ወይም በዛው ፀንተው እንዲቆዩ የማድረግ ሀይል እንዳለው ነው፡፡ ስለዚህም የባህሪይ ለውጥን ለማምጣት በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ በአንፃሩም ቋንቋን በአግባቡ ካልተጠቀምን ልናስተላልፍ የምንፈልገውን መልዕክትንም ለታዳሚያችን በትክክል እንዳይደርሳቸው እንቅፋት ይሆናል፡፡ስለሆነም ንግግርን ተደማጭ፣ ጽሑፉን ተነባቢ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የቋንቋ አጠቃቀም መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ቋንቋ በሰዎች አመለካከት እና ባህሪይ ላይ ተፅእኖ አለው፡፡ በቃላት አጠቃቀም ምክንያት የተናጋሪውና የታዳሚዎች ቅርበት፣ ርቀት፣ ዝምድናን የበላይነት ወይም የጓደኝነት ቦታ ያሳያል፡፡ በዚህ ጥናት ላይ የሚውለው በባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ

አጠቃቀም ሲተነተን ጥልቅ የዲስኩር ትንተና (Critical Discourse Analisis) CDA ስለሚደረግ ዲስኩርንና የዲስኩር አተናተን አስመልክቶ ምሁራን ያሉት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### 2.2.2 ዲስኩር (Discourse):-

በተገቢው አውድ ውስጥ አንድ ሙሉ መልዕክት ለማስተላለፍ የተነገረ ወይም የተፃፈ መስተጋብር (Interaction) ወይም የቋንቋ አፍልቆት (Language production) ነው፡፡ በአጭር አገላለጽ በመስተጋብራዊነት የሚቀርቡ ተግባቦታዊ ሂደት ነው Widdowson (1998) በአብዛኛው ዲስኩር የሚባለው ቃል ተዘውትሮ በጥቅም ላይ የሚውለውም ሆነ የሚታወቀው ለንግግር /ዲስኩር፣ ደሰኮረ እንዲሉ ብቻ ነበር ፡፡ነገር ግን ጥልቅ የዲስኩር ትንተና (CDA) የማህበረሰቡን ተግባቦት መተንተን ማለት ነው፡፡ጥልቅ የዲስኮርስ ትንተና /CDA/ በአንድ ንግግር ወይም በጽሑፍ የሚቀርብ ሀሳብ የአገላለጽ ዐቅም፣ ሀይል፣ አለአቻነት ወይም ግራ መጋባት በሚመለከቱ ጉዳዮች መስክ ላይ ትኩረት አድርጎ ይህንኑ መስክ የሚያጠናና የሚተነትን ነው፡፡ እነዚህ አባባሎችና አገላለፆች በተወሰኑ ማህበረሰቦች በፖለቲካዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚጠገኑባቸውና የሚዳብሩባቸውን ዘዴ መመርመር ነው፡፡ Faircloug (1993፣135) ይህንኑ ሲያብራሩ፡- የዲስኮርስ ትንተና ሀ/ አባባሎችን ለ/ ሰፋ ያሉ ማህበራዊና ባህላዊ ግንኙነቶችና ሂደቶች እነዚህ ልምዶች፣ ሁነቶች እና አባባሎች እንዴት አድርገው እንደሚመነጩ እና እውነታዊ ቅርጽን እንደሚይዙ ሀይልን በሀይል ላይ እየጨመሩ እንዴት እንደሚዳብሩ መመርመርና እነዚህ ግልጽ ያልሆኑ በራሱ በማህበረሰቡና በዲስኮርስ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን የበላይነት ጠብቆ ማቆየት ነው፡፡ በቀላሉ ለማስቀመጥ ጥልቅ የዲስኩር ትንተና /CDA/ ዋና ዓላማው በሃሳብ አገላለጽ እና በትግበራ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ማህበራዊ መዋቅሮችን፣ ለተራ ሰው ግልጽ መሆን የማይችሉትን እነዚህን ሁኔታዎች ግልጽ ማድረግ ነው በማለት van (1998)ያስረዳሉ፡፡

የስነልሳን አጥኚዎች ቋንቋን በአንድ ጊዜ ሦስትዮሽ ተግባራትን ማለትም፣ ግንዛቤያዊ፣ አመለካከታዊ እና አገላለጻዊ ተግባራትን ይመለከታል፡፡ግንዛቤያዊ ሲባል ዓለምንና በዙሪያው እየተካሄዱ ያሉትን ክስተቶች የሚገነዘብባቸው መንገዶች ሲሆኑ አመለካከታዊ

የተባለው ደግሞ ግለሰቦች እነዚህ ክስተቶች የሚሆኑባቸውን መንስኤዎች የሚመዝንባቸውና በጥያቄም የሚያዳብርባቸውና ሆኖ በጠያቂውና በአድማጩ መካከል ያሉ መስተጋብሮች ናቸው፡፡ሦስተኛውና አገላለፃዊ የተባለው ደግሞ ግለሰቡ የተገነዘባቸውንና የተረዳቸውን ክስተቶች በቃላት አማካይነት ራሱን የሚገልጽባቸው መንገዶች ናቸው Fowler (1991p7) Fairclough (1995 p25.) ፡፡

ቋንቋ "ማህበረሰባዊ ተግባር ነው" በሚለው Halliday አመለካከት ጥልቅ የዲስኩር ትንተና /CDA/ እየተከተሉ ያሉ እንደ እነ (Chouliaraki & Fairclough 1995) የስነ-ልሳን ጥናት "በስነልሳን መዋቅር እና በማህበረሰባዊ ውቅር" መከካል ሰፋ ያለ ትስስር ያለ መሆኑን ማህበራዊ ስነልሳን ጥናት ያስረግጣል፡፡እንደ Fowler (1979) እና ሌሎች አስተሳሰብ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ማህበራዊ ስነልሳን መሠረት አንደኛው በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት አቅም የሚያስረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋ የህብረተሰብ መስተጋብር ውጤት መሆኑን ይገልፃል፡፡ ሌሎች ምሁራኖች ስለ ዲስኩር ትንተና ሲናገሩ በዘመናዊው ዓለም ሕዝቡ የተዛባ እና ፍትሃዊ ያልሆኑ ነገሮችን ለማስተካከል የተለያዩ ቋንቋዎችን እንደመሳሪያነት ተጠቅመዋል በማለት (Tishar እና ሌሎች 2000) ገልፀዋል፡፡ የዲስኮርስ ትንተና አጥኚዎች ከዕለት ዕለት የዲስኮርስ ትንተና አቀራረብ እንደማህበረሰቡ ባህል የቋንቋው አጠቃቀም እንዲሁ እንደ ማህበረሰቡ የባህል ስፋት እና የፖለቲካ ሁኔታ ምንጭና አቀራረብ ይተነትናል በማለት Fairclough /2003/ ገልጸዋል፡፡

Fairclough Wodak (1971፣271-80) ጥልቅ የዲስኩር ትንተና (CDA) ሊከተላቸው የሚገባ ዋናዋና ነጥቦች በማለት እንደሚከተሉት አስቀምጠዋቸዋል፡፡ጥልቅ የዲስኩር ትንተና (CDA) የማህበረሰቡ ችግር ላይ ያተኩራል፣ እንደየደረጃቸው ቅርበት ያብራራል፣ዲስኩር ባህልና ማህበረሰቡን ይይዛል፣ ሀሳባዊ ነው፣ዲስኩር ታሪካዊ ነው፣በማህበረሰቡና በመልእክቱ መካከል በመሆን ያቆራኛል፣የዲስኩር ትንተና ማለት መግለጽና ማብራራት ማለት ነው ሌላው የማህበረሰቡ ተግባር ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተገለፁት መሠረት በዲስኮርስ ትንተና ውስጥ የሚነሱት የቋንቋ ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ የዲስኮርስ ትንተና በጥቅሉ ሲታይ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ነው፡፡ይህ ጥናትም የቋንቋ አጠቃቀሙን ሲተነትን የጋብቻውን አፈጻጸም ሂደት ውስጥ ቋንቋ እንዴት

ማህበራዊ ደረጃን፣ ፆታን፣ ቅርበትና ርቀትን፣ ባህልን፣ እምነትን በተግባቦት ሂደት እንደሚገልጽ ያሳያል፡፡

### 2.3 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

#### 2.3.1 ትኩረታቸውን በከምባታ ብሄረሰብ ላይ ያደረጉ ጥናቶች

ጸደኒያ ዳመነ በ (2001) ‹‹የከምባታ ብሄረሰብ የባህላዊ ምግብና መጠጥ አዘገጃጀት አቀራረብና አመጋገብ ስርአት›› በሚል ርዕስ ለማስተርስ ማሟያ ያጠናችው ጥናት ሲሆን ጥናቱ ትኩረት ያደረገው የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የምግብና የመጠጥ አዘገጃጀት አመጋገብ ስርአት ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ምግብና መጠጥ ከጾታና ማህበራዊ ደረጃ አንጻር ተመልክቷል፤ሌላው የምግብና የመጠጥ ስነ-ቃልና ሀገረሰባዊ እምነቶችን አገናኝቶ የሚያስረዳ ጥናት ነው፡፡

ገዛኸኝ አሰፋ በ(1999) በኢትዮጵያ ስነ ጹሁፍና ፎክሎር ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጹሁፍ ‹‹የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት›› በሚል ርዕስ ጹሁፍ ሲሆን የጥናቱ አላማ የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ያሉበትን ደረጃ መመልከት ተጹኖዎችም እስከምን ድረስ እንደደረሱ መመርመርና ትውን ጥበባቱ ምን ይዘት እንዳላቸውና ብሄረሰቡን እንዴት እንደሚገልጸቸው ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የጥናቱን አላማ ለማሳካት የተጠቀማቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅና ምልከታ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡የጥናቱ የትኩረት ነጥብ የነበሩት ሀገረሰብ ዘፈን፣ሀገረሰብ ዳንስ፣ሀገረስብ ድራማ፣የሀገረሰብ ሙዚቃ መስተጋብር ፣ሀይማኖታዊ ትወና፣የልደት ወቅት አተዋወን ፣የሰርግ ወቅት አተዋወን፣የሞት ወቅት አተዋወን ምን አይነት የአተዋወን ስልት እንዳላቸው ማሳየት ነው፡፡ስለ ከምባታ ብሄረሰብ የትመጣ (origin) የጥናት ጹሁፍ በማቅረብN.J singer (1975;1977) Braukamper(1983) ይጠቀሳሉ፡፡Braukamper የብሄረሰቡን እምነትና መሰረት ከታሪክ ጋር እያጣቀሰ በማቅረቡ singer ደግሞ የከምባታን ህዝብ ለማስተዋወቅ ያደረገው ጥረት ሁለቱ ይጠቀሳሉ በማለት(ገዛኸኝ 1999፡7) ገልጸል፡፡

ፍቃደ (1977፣1984፣2001) ያቀረባቸው መጣጥፎችና የምርምር ስራዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኞቱ በፎክሎር የተደረጉ ጥናቶች በአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም መምህራንና ተማሪዎች የቀረቡ ናቸው፡፡ብዙዎች ጽሁፎች ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ እንደሆነ መጥቀሳቸውን ገዛኸኝ አሰፋ በጥናቱ አቅርቧል፡፡ሌላው በከምባታ ዙሪያ ከተጠኑ ጥናቶች የብርሀኑ ማቴዎስ (1986) An analysis of kembatta proverbs) በኤም ኤ ዲግሪ የምርምር ስራ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ብርሃኑ በዚህ ጥናቱ የከምባታ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብና በይዘትና በቅርጻቸው ላይ ትንታኔ በማድረጉ በቀዳሚነቱ እንዲሁም በስራው ጥልቀት ይጠቀሳል፡፡ተስፋዬ ሀቢሶ በአማርኛ ቋንቋ‹‹ከምባታና ሀድያ የአስተዳደር አካባቢና የብሄረሰቡ ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች (1986) በሚል ርዕስ ባቀረበው የጥናት ወረቀት በብሄረሰቡ የቃል ታሪክ አዋቂዎች በተጓገሮች በሚሶናዊያንና በተመራማሪዎች ስለ ማህበረሰቡ ታሪክ፣አስተዳደራዊ ሁኔታዎች ለማመልከት መሞከሩ ተጠቃሽ ነው፡፡ እንዲሁም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ‹‹someRecordes of south West Ethiopia and short History of Kembatta and its people›› (1987) ያቀረበው የጥናት ወረቀትም ስለ ብሄረሰቡ ታሪክ ለማስተዋወቅ ጥረት አድርጓል፡፡

ከሁሉም ለየት ባለ ሁኔታ የቀረበው በፍሬሕይወት አድነው 1997 የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጹሁፍ ነው፡፡‹‹ከምባቶመት›› የከምባታ ፎክሎር ይዘትና ለውጥ በሚል ርዕስ ባቀረበው ጹሁፍ የከምባታ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት ክብረ በአላትና ጨዋታዎች ልማዶች ስርዓቶችና የከምባቶመት ይዞታና ለውጡን ቃኝቷል፡፡ ፍሬሕይወት በዚህ ጥናቱ ‹‹ከምባቶመት›› የማድመጥ ባህል የመጠበቅ፣ የመረጋጋት፣ያለመቸኮልና በቂ መረጃ ይዞመነሳሳት፣ስራ ወዳድነትን ይገልፃል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ ትኩረት የሰጠው ለከሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ነው፡፡ በኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ትምህርት ክፍል ለቢ ኤ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡ ጥናቶች ውስጥ በከምባትኛ ዙሪያ የተጠኑ ጽፎች ደስታ ገ/ ሚካኤል(1963) የከምባትኛ ተረትና ምሳሌዎች፣የመኮንን(1970) የከምባትኛ እብቆቅልሾች፣የደስታ ጸደቀ(1981)የከምባትኛ ስሞች በከምባታ ማህበረሰብ፣የደስታ ሎረንሶ(1982)‹‹ የከምባታ ማህበረሰብ ባለ እጆችና ስነቃላቸው ›› ተጠቃሽ ናቸው፡፡ከላይ የቀረቡ ጥናቶች በሙሉ በከምባታ ብሄረሰብ ዙሪያ የተጠኑ በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡

### 2.3.2 በርዕሰ ጉዳይ የሚዛመዱ ጥናቶች

በአርቲንግ ደጉ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ በ 1995 ዓ/ም የቀረበው ጥናት ሲሆን ርዕሱም የከምባታ ብሄረሰብ የሰርግ ስነ-ስርዓትና ግጥሞች ይዘት ትንተና የሚል ነው፡፡የጥናቱ ዋና ትኩረት የከምባታን ብሄረሰብ ማህበራዊ፣ባህላዊ አመለካከቱን ማሳየት ነው፡፡አጥኚው በመጀመሪያ በከምባታ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከናወኑ የጋብቻ አይነቶችን ካመለከተ በኃላ ከጋብቻ አይነቶች የህጋዊ ጋብቻን በመምረጥ ስርአቱንና የግጥሞቹን ይዘት በሰፊው ተንትኖ ያቀርባል፡፡በሙሽራውና በሙሽሪት ወገን የሚገጠሙ የተለያዩ ስድቦችና ሞገሳዎች ከነይዘታቸው በሰፊው ያስረዳል፡፡የግጥሞቹን የዘይቤ አጠቃቀም በተወሰኑ የዘይቤ አይነቶች ማሳያነት ይገልጻል፡፡

በቀጥታ ከጥናቷ ጋር የሚገናኘው የከምባታ ብሄረሰብ የሰርግ ስነ ስርኣት ግጥሞች ይዘት ትንተና በሚል ርዕስ የከምባታ ባህላዊ የሰርግ ስነ ስርኣት ምን እንደሚመስል ማሳየቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም በጥናቱ ተግባቦታዊ ሂደቱን የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና አለማድረጉ ከጥናቴ ይለያል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

አጥኚዋ ጥናቷን የተነተነችው አይነታዊ ዳታ መተንተኛ በመጠቀም ነው፡፡ምክንያቱም አይነታዊ ዳታ መተንተኛ ከሳይንሳዊ የምርምር ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ "ሳይንሳዊ" አካሄድ ይከተላል፡፡ እነሱም:- ለጥያቄዎች መልስ መፈለግ፣ አስቀድሞ የተዘጋጁ ስልታዊ ቅደም ተከተሎችን መከተል፣ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ቀደም ብሎ ያልተተነበየ (Unpredictable) ግኝት ማምጣት እና ከጥናቱ ክልል /መቼት/ ተሻግሮ ሊተገበር የሚችል ውጤት ማስገኘት ነው፡፡ ከአቀራረቡ አንፃርም አይነታዊ ዳታ መተንተኛ አንድን ሁኔታ ወይም ክስተት በጥልቀት በመመርመር ሂደቱን ቁጥራዊ ባልሆነ መንገድ ወይም በቃላት እና ምንባባት መልክ የሚተነትን ነው፡፡በዚህ መሰረት በጋብቻ ክስተት ላይ የሚባሉ የሀሳብ ልውውጦችን የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ቁጥራዊ ባልሆነ መንገድ በቃላት በመተንተን አጥኚዋ ይህን አይነታዊ ዳታ መተንተኛ ተጠቅማለች፡፡

### 3.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለጥናት ያመቻል ተብሎ የተመረጠው የንሞና ዘዴ አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው ፡፡ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክኒያት የመረጃ አቀባዩች ናሙና አመራረጥ የባህል መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ዕድል የማይሰጥ የንሞና ዘዴ (non probability sampling) አካል የሆነው ታላሚ ናሙና(purposive sampling) ተመራጭ ነው፡፡ይህ ጥናት ሲጠና 20 መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል ፡፡ሀያ የተመረጠበት ምክኒያት ለጥናቱ ከተመረጡ ቀበሌዎች ውስጥ በእድሜ የገፉና የባህሉ በቂ እውቀት አላቸው የተባሉ በጥቆማ የተገኙ ስለሆነ ነው ፡፡ ከዚህ ውስጥ 14 ወንዶችና ሁለት ሴቶች በእድሜ የገፉና በአካባቢው ተወልደው ለረዥም አመት በመኖር ቱባ የባህል እውቀት አላቸው የተባሉ ሲሆን ከባህል ቱሪዝም መምሪያ ከባህል ስራ ሂደት አስተባባሪ አራት ባለሙያዎች መረጃ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ከነዚህ ወጪ ለጥናቱ እገዛ የሚያደርጉ አነስ ያለ መረጃ ያቀበሉ መረጃ ሰጪዎችም ተሳትፈዋል፡፡

### 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ጥናት ማከሄድ እንደሚቻል (Goldstein 1964 ፣ፍቃደ 1991) ይገልጻሉ፡፡እነዚህ የመረጃ ምንጮች ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ከመስክ የሚገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡ካልአይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ጹሁፋዊ ሰነዶች ፣ጥናታዊ ጹፎች ፣ታሪካዊ መዛግባቶች ወዘተ... የሚያካትት ነው፡፡በጋብቻ ስርአት ላይ የሚደረግ የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ለማጥናት ተፈጥሯዊ አውድን መጠቀም የግድ ስለሆነ ከመስክ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ ዘዴዎች ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት መጠቀም ጥሩ አማራጭ ይሆናል ፡፡

#### 3.2.1 ምልከታ

ምልከታ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ በመገኘት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ይህ ዘዴ በመስክ ላይ ሁኔታዎችን በተፈጥሯዊ ግኝታቸው በማየት በመስማት ወይም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው ፡፡ በዚህ ጥናት ባህሉን ያልለቀቁ የጋብቻ ስርኣቶች ላይ በመገኘት መረጃ ተሰብስቧል፡፡በምልከታ የተሰበሰበው መረጃ በቀጥታ ስርኣቱ ሲካሄድ ሂደቱን ለምሳሌ ሽማግሌዎች በሴቷ ወላጅ ቤት በሚያደርጉት ስርኣት ላይ በመገኘት ፣ (አንጋ ሱንቃ) የማርና የቡልኮ ስጦታ ስርአት እና በዋናው የጋብቻ(የሰርግ) ስርኣት ላይ በመገኘት ከሚነገረው ንግግር ጋር ምስልና ድምጹን በመቅርጸ ድምጽና ምስል በመቅረጽ መረጃውን ለትንተና ተጠቀማለች፡፡

#### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዩች ስለተጠየቁት ጉዳይ ፣ሁኔታ፣ድርጊት ፣ አመለካከት ገለጻ በማድረግ መረጃ እንደሚሰጡ (Goldstine 1964:77) ይገልጻል፡፡ቃለመጠይቅ ስለአንድ የሚያውቋቸውን የተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

በተግባራዊ ስነልሳን ጥናት አብዛኞቹ ቃለመጠይቆች የሚካሄዱት በከፊል በተዋቀረ ቃለመጠይቅ ላይ ተመርኩዘው ነው፡፡ ይህ የቃለመጠይቅ አይነት በተዋቀረና ባልተዋቀረ ቃለመጠይቅ የሚቀርቡ መረጃዎችን ባስታራቂ መንገድ ለመቃኘት ይረዳል (ZOLTAN 2007፥123) ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ቃለመጠይቅ አይነቶች የተዋቀረና በከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ አጥኚዋ ተጠቅማለች ፡፡ ምክኒያቱም የተዋቀረ ቃለመጠይቅ በትክክል አላማ ላይ የተቀመጠውን ሊያሳካላት የሚችል ጥያቄ በማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚረዳት፣ ሁለተኛው በከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ መረጃዎችን ባስታራቂ መንገድ ማግኘት ስለሚቻል ሁለቱን የመረጃ ማሰባሰቢያ ቃለመጥይቆች፣ ባህሉን ከሚያውቁና በእደሜ ከገፉ ሽማግሌዎቾ ከባህል ቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎች፣ በበህላዊ ጋብቻ የተጣመሩ ተጋቢዎችን ባጠቃላይ 14 ሰዎች ከእያንዳንዳቸው ጋር ቃለ ምልልስ በማድረግ አጥኚዋ ለትንተና የሚሆን መረጃ ሰብስባለች፡፡

### 3.2.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ከመስክ መረጃ ለማሰባሰብ ተመራጭ ዘዴ እንደሆነና የቡድን አባላቱም ቁጥር ከ7-12 ሊደርሱ እንደሚችሉ(MIKE AND COOK:2007) ይገልጻሉ፡፡ሂደቱም በተመራማሪውና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ምልልስ የሚከናወን ነው፡፡የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለዚህ ጥናት በምልከታና በቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ያልተመለሱትን አጠኚዋ እርግጠኛ ያልሆነችባቸውን ጉዳዮች ለማጣራት ተጠቅማበታለች፡፡ይህንን ለማሳካት ዘጠኝ አባል ያለው ሁለት ቡድን በማደራጀት አንዱ ቡድን የባህል ባለሙያዎችን ያቀፈ ሁለተኛው ባህሉን የሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች የያዘ፣ እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ጊዜ እንዲሰበሰቡና እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ወይይቱ የተካሄደው ለመረጃ ሰጪዎች ማዕከል ይሆናል ተብሎ በተመረጠ በዳምቦያ 01 የኮካታ መሰብሰቢያ ቦታ ሲሆን ውይይቱ አጥኚዋ አባሉ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሀሳቡ እንዳያመራ እራሷ እየተቆጣጠረች በመምራት እንዲወያዩ አድርጋ መረጃ ሰብስባለች፡፡መረጃው በመቅረጸ ድምጽ ከተያዘ በኋላ ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ አላማን ሊያሳኩ የሚችሉ መረጃዎች ተመርጠው ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

### 3.2.4 መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

መቅረጸ ድምጽና መቅረጸ ምስል ትክክለኛ መረጃን ለመያዝ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በተለይ ለዚህ ጥናት ማለትም ባህላዊ የጋብቻው ስርኣት ከትጭጭት እስከ ድህረ ጋብቻ ድረስ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ለመተንተን ምስልን ከነ ድምጻቸው በመቅረጽ መረጃ በመያዝ አጥኚዋ ለትንተና ተጠቀማለች ፡፡

## 3.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

### የመረጃ ትንተና

በመጀመሪያ በመቅረጸ ድምጽ የተሰበሰበው መረጃ ወደ ጽሁፍ ተቀየረ፡፡ በመቀጠል መረጃዎቹን ለትንተና በሚመች መልኩ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተሰበሰቡበት መሳሪያ አይነት ተመደበ ፡፡መረጃ የማደራጀት ሂደት አራት ዋና ዋና ሂደቶች ተከትላለች፡፡ በሂደት ቅደም ተከተላቸው መሰረት መረጃዎችን ማረም (ማስተካከል ) ለተስተካከለው ወይም ለታረሙት መረጃዎች ኮድ መስጠት፣ኮድ የተደረጉትን መረጃዎች በየዘርፉና በየርዕሱ ጉዳዩቻቸው መመደብ ወይም ማቀናጀት ናቸው፡፡ ለዚህም ጥናት እነዚህን ሂደቶች ትክክለኛ የመረጃ ትንተና ለማድረግ ስለሚጠቅሙ ሂደቶችን ተከትላ አጥኚዋ መረጃዎችን አቀናጅታለች፡፡

የመረጃ ትንተናውን በተመለከተ ጥናቱ በከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት ላይ የሚደረጉ የቋንቋ አጠቃቀሞች ትንተና የሚመለከት ስለሆነ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተጠቀማለች፡፡ይህ ዘዴ ነባራዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህሪ በመለየት ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት በብሄረሰቡ የሚገለጹ ቋንቋዎችን ለመተንተንና ለመግለጽ አመቺ ዘዴ ነው፡፡በተጨማሪ የይዘት ትንተና ዘዴን ተጠቅማለች ፡፡ይህ ዘዴ በገለጻ የቀረቡ መረጃዎችን የቀረቡበት አውዳዊ ትርጓሜ ለማሳየት የሚጠቅም ዘዴ በመሆኑ በባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት የሚጠቀሙትን በቋንቋ ውስጥ ያሉ አውዳዊ ፍቺዎችን ትንተና ለማሳየት ይህ የይዘት ትናተና ዘዴ ተመራጭ ሆኗል፡፡

## 3.4 መረጃን መተርጎም እና ማጠቃለያ ማውጣት

የመጨረሻው ወሳኝ ተግባራት መረጃን መተርጎም እና ማጠቃለያ ማውጣት ናቸው:: በርግጥ የመረጃ ትርጎማው ተግባር የሚጀምረው በዚህ ደረጃ ላይ ሳይሆን መለያ በመስጠትና አጫጭር ማስታወሻዎች (Memos) በመጻፍ ተግባር ላይ ቢሆንም በዚህ ወቅት የሚከናወነው ትርጎማ ግን በዝርዝር ጎዳዮች ላይ የሚያተኩር ሳይሆን በዋና ዋና ጭብጦች ላይ የተመሰረተ ነው:: ይህ ክዋኔም ወደ ዋና የማጠቃለያ ሀሳብ እንድናመራ ይረዳናል:: እዚህ ማጠቃለያ ላይ መድረስ የሚቻለውም በተናጥል የቀረቡትን ማስታወሻዎች ቃለመጠይቃዊ ትንታኔዎቸ እና ሌሎች መረጃዎች የተወሰነ ስርዓት በማዘጋጀት አቀናጅቶ በማቅረብ እዲሁም ዋና ዋና ጭብጦችን መርጦ በማውጣት ነው::

ይሄን ተግባር በአጭሩ ለመግለጽ አጥኚዋ በመጀመሪያ የመረጃ ሽግግር አድርጋለች፡፡ ይህ ማለት በመቅረጸ ድምጽ ያተዘውን መረጃ በጽሁፍ ወይም በንባብ መልክ አሸጋግራለች፡፡በመቀጠል በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በአንድ ላይ፣ በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በአንድ ላይ፣በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙትን በአንድ ላይ በማድረግ ለመረጃዎቹ የመለያ ኮድ ሰጥታለች፡፡ የቀጣዩ ተግባር የመረጃ ትርጎማ ስራ ሲሆን የአጥኚዋ አላማ ቋንቋውን ዲስኩራዊ ትንተና በማድረግ የማህበረሰቡን ማንነት ለማሳየት ሞክራለች፡፡ ባጠቃላይ ወደ ትንተናው ሲገባ፡-

1/ የዚህ ጥናት አብይ ጭብጥ ምንድ ነው?ምንንስ ያመለክታል?

2/ የተሰበሰቡ መረጃዎች የጥናቱን ጥያቄዎች የሚመልሱ ናቸውን?

3 የጥናቱ ትወራና የተከናወኑ ተጋባራት ምን ያመለክታሉ?

4 እንዲሁም ወደ ፊት መካሄድ ስለሚኖርበት ምርምርስ ምን ማለት ይቻላል?

የሚሉትን ጥያቄዎች ታሳቢ ያደረገ ተንታኔ በማድረግ አጥኚዋ የድምዳሜ ሀሳብ ላይ ደርሳለች፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4 የጥናቱ መረጃ ትንተና

### 4.1 የጋብቻ አይነቶች ስርዓትና የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና በከምባታ ብሄረሰብ

በየትኛውም  የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ የጋብቻ ስርዓት ያለ ቢሆንም እንደ የአካባቢው ባህል የየራሳቸው ልዩ ባህሪይ እና የህብረተሰቡን አመለካከትና እምነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በከምባታ ብሄረሰብም ጋብቻ የማህበረሰቡ ማንነት ሲንጸባርቅበት ጥናቱ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ከምባታ ስለጋብቻ ያለው እሳቤ ምንድን ነው? በብሄረሰቡ ዘንድ ስንት ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች አሉ? በሰርዓቱ ክወና ወቅት የቋንቋ አጠቃቀም ምን ይመስላል? የሚሉትን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

#### 4.1.1 የጋብቻ እሳቤ በከምባታ ብሄረሰብ

የከምባታ ማህበረሰብ ስለጋብቻ ያለው እሳቤ ምን እንደሚመስል መረጃ አቀባዮቹ ተጠይቀው ሲገልጹ ጋብቻ ዘር፣ ወገን መጨመር ነው፡፡ከዚህ የተነሳ ወላጆች ለልጆቻቸው ትዳር ሲፈልጉ ሰፊና ጠንካራ ዘር ያለው ቤተሰብ የቱ ነው የሚለው ጥያቄ የመጀመሪያቸው አድርገው ያፈላልጋሉ፡፡ ጠንካራ መሆኑ የሚፈለገው በችግር ቀን ጎን ይሆነናል፣ በደስታ ቀን ደስታን ያደምቅልናል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ አንድ አባት አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ላለው ቤተሰብ ልጁን አይሰጥም፡፡ ምክንያቱም ብቸኛ ልጅ ከሆነ ማን ያውቃል ቢሞት ልጃችንን የሚወርስ ወይም አደራ የሚቀበል ሰው የሌለበት ቤት ስለሆነ ልጃችንን አንሰጥም ይላል፡፡ ስለዚህ አግቢው ወንድሞች፣ አኅቶች ሰፊ ቤተሰብ ያለው ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ ሌላው ትንሽ ዘር ያለበት ቤተሰብ ከሆነ ልጃችን አግብታም ዘራችንን ታሳንሰዋለች የሚል ስጋት ያድርባቸዋል፡፡ ስለዚህ ጋብቻ ለከምባታ መዋለድና መብዛት ነው፡፡

ይህንን ሀሳብ ስናይ ለትዳር ዋነኛ መመዘኛ ተደርጎ የተወሰደው ሰፊና ጠንካራ ዘር ነው፡፡ አንዲትን ሴት ልጅ ለጋብቻ ሲሰጡ የልጁ ዘር ሰፊ መሆን አለበት ሲሉ የአባቱ ልጆች ብዙ አኅት እና የአኅት ልጆች ብዙ አክስትና የአክስት ልጆች  በእያንዳንዱ የዘመድ ቤት በርከት ያለ ልጅ ዘሩን ተከትሎ የመውለድና የመዋለድ መጠናቸው የበዛ መሆን አለበት፡፡ይህንን ሀሳብ በሌላ ጎኑ ስናይ ባለመውለድ ችግር ውስጥ የገባ ከቤተሰብ ውስጥ

ሊኖር አይገባም፡፡ መውለድ መቻል ብቻ ሳይሆን የሚወለዱት የልጅ መጠን ማነስ የለበትም የሚል እንድምታ ያለው ነው፡፡ይህ የማህበረሰቡ አመለካከት ብዙ ቤተሰብ ያለው ዘር ተቀባይነት፣ ከበሬታ፣ተሰሚነት፣ ቦታ የሚሰጠው ነውና ለጋብቻ ተመራጭ ነው፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳው ጠንካራ ዘር መሆኑ ሌላው የተፈላጊነት መመዘኛ ሆኖ ቀርቧል፡፡ይህ ሀሳብ ኑሮውን ማሸነፍ የሚችል፣ ቤተሰቡን በአግባቡ የሚመራ፣ አቋመ ጽኑ የሆነ ለማለት ሲሆን ይህንኑ ሀሳብ በሌላ መልኩ የዘሩን ማህበረዊ ደረጃ ማየት እንችላለን፡፡ ህብረተሰቡ ውስጥ ለዘር የተሰጠ ደረጃ እንዳለና ከፍተኛ ደረጃ የተሰጠው ዘር ጠንካራ በማህበረሰቡ መስፈርት ለችግር መፍትሄ መስጠት የሚችል፣ ክፉ ነገር ቢመጣ መቋቋም መወጣት የሚችል ነው ተብሎ ከተመረጠው ዘር ጋር በጋብቻ መጣመር ጥሩ መሆኑን ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡

ሌላው …ማን ያውቃል ቢሞት ልጃችንን የሚወርስ ወይም አደራ የሚቀበል ሰው በሌለበት ቤት… የሚለው ሀሳብ ሞት ማስቆም ባይቻል ሞት ከተከሰተ ከሞት ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ ለማስቀመጥ ይመስላል፡፡ በእነሱ አስተሳሰብ በሞት ምክኒያት ለሚፈጠር ችግር መፍትሄ መስጠት ማለት ልጃቸውን በትዳር እድትጣመር የሚያደርጉት ባል ቢሞት ወንድሞቹ ወይም የቅርብ ዘመድ ካለው ሊያገባትና ሕይወቷን ሊያስቀጥልላት ያስፈልጋል ለማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የምንገነዘበው አንዲት ሴት ባል ከሞተባት የቅርብ ዘመድ ሊወርሳት ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡

ብዙ መውለድን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን ስንመለከተው ማህበረሰቡ ካለው የመሬት ጥበትና የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር ብዙ መውለድ በሁለት መንገድ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ የሰው ሀይል በራሱ ሀብት ነው፡፡ ሀብት መሆን የሚችለው ግን የተወለደው ልጅ በወጉ ማሳደግና ወደ ስራ ማሰማራት ሲቻል ነው፡፡ የሰው ልጅ በአስተሳሰብ መንጥቆ ጨረቃ ላይ መድረስ እንደቻለው የከምባታ ልጆችም በወጉ የማደግና የመማር ዕድሉን ያገኙ በበርካታ የአለም ሀገራት ሳይንቲስት፣ ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ ፓይለት ወዘተ… በመሆን እያገለገሉ እንዳሉ ሁሉ በብዙ የሀገራችን ክልሎች በደውሮ፣ በጅማና በዙሪያው ወረዳዎች፣ በከፋ፤በቦንጋ፣ በቤንች ማጂ፣ በናዝሬት፣ በወንጂ፣ በመተሀራ፣ በተለያየ የስራ መስክ

ተሰማርተው በተለይ በደርግ ዘመነ መንግስት ሰፊ የተማረ ሀይል ባልነበረበት በመምህርነት ሲያገለግሉ የነበሩ እስከአሁንም እያገለገሉ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ይህ የሰው ሀይል ለሀገር እድገት የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ማህበረሰብ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ብዙ ልጅ መውለድ በሌላ ጎኑ ስናይ ወላጆች ካላቸው ከመሬት ጥበትና የማስተማር አቅም ማነስ የተነሳ ብዙ ልጆች  ካለው የአባት መሬት በስንዝር ተቀራምተው ያችኑ በቂ ያልሆነ መሬት በማረስ ሰፈር ቀርተዋል፡፡ሰፈር አልቀርም ያለው መሬት ሊያኖረው እንደማይችል የተረዳው ቀዬውን ለቆ በተለያየ ሀገራችን ክልሎች በጥቃቅን ስራዎች ተሰማርቶ መኖር እድል ፈንታው አድርጎ ኑሮውን እየገፋ ያለ በርካታ ነው፡፡ከዚህ ጋር ሳይነሳ የማይታለፈው የስደት ጉዳይ ነው፡፡ ስደት እንደ ሀገራችን በሁሉም አካባቢ ወጣቱ ትውልድ ላይ የሚስተዋል ቢሆንም የከምባታ ብሄረሰብን ለየት የሚያደርገው ወጣቱ ብቻ ሳይሆን ትዳር መስርቶ የብዙ ልጆች አባት ከሆነ በኋላ ሚስቱንና ልጆቹን እርግፍ አድረጎ መሰደዱ ነው፡፡ የከምባታ ማህበረሰብ በስደት በተለያዩ ሀገራት እንደሚኖሩ ይነገራል፡፡በሱዳን፣ በኬኒያ፣ በአረብ ሀገራት፣ በአሜሪካ ወዘተ.... በተለይ በልዩ ሁኔታ የሚሰደዱበት ሀገር ደቡብ አፍሪካ ሲሆን ወጣቱም ሆነ ልጆቹንና ባለቤቱን እርግፍ አድርጎ የሚሰደደው አጋጣሚ ሆኖ የተሳካለት ደቡብ አፍሪካ ገብቶ ወንድሙን፣ የአጎቱን፣ የአክስቱን ልጅ ሲወስድ፣ አባት ልጁን ሲያሻግር ሕይወቴን ከዚች ገነት አላወጣትም ያለ ሚስቱንም ጠርቶ እዛው ሲሰምጥ በቂ ሀብት የያዘና መልሶ ሀገሩን የናፈቀ አፈራው ያለውን ሀብት አካብቶ ወደ ሀገሩ ይመለሳል፡፡

ይህ ስደት ያልተሳካለት ሲጸለይና ሲያጸልይ ቆይቶ ከቤት እንደወጣ መንገድ ላይ አውሬ የበላው፣ ውሀ የወሰደው፣ በኮንቴነር ተጭኖ ታፍኖ የሞተው፣ ጫካ ውስጥ ሞቶ እሬሳውን አሞራ የበላውን ቤቱ ይቁጠረው፡፡ተሳካለት ተብሎ እንኳን ደቡብ አፍሪካ ከገባ በኋላ ዘራፊ ገደለው፣ መኪና ገጭቶ ገደለው በጩቤ ተወጋ ወዘተ..... እየተባለ በአውሮፕላን እየተጫነ ወደ ሀገር ቤት የሚመጣው የእሬሳ ቁጥር ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ እንጂ ሲቀንስ አላየነውም፡፡ይህ ሀሳብ ስጠቃለል ጋብቻ ለከምባታ ትውልድ ከመተካት  ዘርን ከማስፋት ጋር የሚታይ ከመሆኑ ባሻገር በአንድ ወገን በሞት ምክንያት እንኳን ትውልድ መቀጠሉ እንዳይቋረጥ ከቅድመ ጋብቻ በፊት ጀምሮ ጥንቃቄ የሚደረግለትእና ልጅ የመውለድ ፍላጎት ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡የዚህ አስተሳሰብ ውጤት በማህበረሰቡ

ላይ አወንታዊና አሉታዊ ተጽኖ እንዳሳደረ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

## 4.2 ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች

የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት በአራት መንገድ እንደሚካሄድ መረጃ አቀባዮች እንዲህ ሲሉ በቁጥር ያስቀምጣሉ፡-

1. ‹‹ቆርሲሻ›› በመተጫጨት መጋባት
2. ‹‹ሄረንቻ›› በማግባባት ወደ ጋብቻ ዓለም መግባት
3. ‹‹ሚዱ›› ጠለፋ ናቸው፡፡
4. ‹‹ረጊታ›› የውርስ ጋብቻ

### 4.2.1 ቆርሲሻ - በመተጫጨት መጋባት

የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት አንዱ የሆነው ‹‹ቆርሲሻ›› በመተጫጨት መጋባትን አስመልክቶ መረጃ አቀባዮች ሲገልጹ ይህ የጋብቻ ዓይነት በወላጆች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ልጆቻቸው ማለትም ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም መድረሱን ካወቁ የትዳር አጋር የምትሆነውን ልጃገረድ ማፈላለግ ይጀምራሉ፡፡ የማፈላለጊያ ሂደቱ በልጁ አባት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ዘመዶች የሆኑ ሁሉ በማፈላለግ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ ከአንድ በአንዳቸው የተፈለገችው ልጅ ከተገኘች የአቶ ኤከሌን ልጅ አይቻለሁ ብሎ ያየው ሰው ጥቆማ ለልጁ አባት ይነግራል፡፡ በዚህ ሥርዓቱ ይጀመራል፡፡

ጋብቻ በወላጆች ፈቃድ ላይ እንዲመሠረት የሚደረገው ለምንድ ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው መረጃ አቀባዮቹ ሲያብራሩ፡- ልጆች ለትዳር የምትሆነው የቷ እንደሆነች ማወቅና መምረጥ አይችሉም፡፡ የሚመርጡበት የዕድሜ ክልል ላይም አይደሉም፡፡ ወላጆች ግን በትዳር ዓለም ያለፉበት ሂደት ስለሆነ ለትዳር የሚበጀውን ያውቃሉ፡፡ ሌላው ወላጆች ሲመረጡ የዘር ሐረግ እንዳይገናኝ ይጠነቀቃሉ፡፡ የልጅቷ ባህሪይ አጥንተው ወይም አስጠንተው ባለሙያ መሆን አለመሆኗን በዘመድና በጎረቤት አማካይነት መረጃ ከሰበሰቡ በኋላ ነው ለልጃቸው የምትሆነውን አጋር የሚመርጡት፡፡ ልጆች( አጊቢው) ምረጥ ተብሎ ቢፈቀድለት መልኳን ብቻ ስለወደደ ወይም ባህሪይዋ ብቻ ስለተመቸው ወደ ጋብቻ

ሊያመራ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የዘር ሐረጉ በማይፈቅድ ሁኔታ ሊሆን ይችላል፣ በዚህ ጊዜ ከባህላችን ውጪ ሆኖ ወላጆችን ሊያስቆጣ እሱም ሊጎዳ ይችላል፡፡ ብቻ የልጅ ምርጫ አንድ ነገር እጥረት ወይም እክል አያጣም፡፡ ይህንን ከባድ የትዳር ዓለም ውስጥ ለመግባት በልጆች ምርጫ ፈጽሞ የተሳካ ሊሆን አይችልም የሚል እምነት ስለነበረ ነው በወላጆች ምርጫ ትዳር የሚመሠረተው፡፡

ሌላውና ሁለተኛው ጋብቻ የሚፈጸምበት መንገድ ልጁ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ ለትዳር የምትሆነኝን አንዲት ልጅ አይቻለሁ ብሎ ለአባቱ ይነግራል፡፡ አባቱም የልጁ ምርጫ ትክክል መሆን አለመሆኑን የሚያጣሩበትና ወደ ጋብቻው አለም እንዲገባ የሚያደርጉበት ሂደትም አለ፡፡ ወላጆቹም ሆኑ ልጃቸው አይቶ የወደዳት ልጅ ለትዳር ከመጠየቁ በፊት ሁለት ሂደቶችን ማለፍ ይጠይቃል፡፡ ይሄውም ጋብቻ ከልክል ማጣራት ‹‹ቦሎቻ ከመኖ ሴራ›› እና ገድ የማየት ስርአት‹‹ ጪቼ ጡደቁ›› ናቸው ፡፡

ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ ስንመለከት ለጋብቻ ምርጫ ሰፊ ድረሻ ያላቸው ወላጆች እና የወላጅ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ ልጃቸው የትዳር አጋር መርጫለሁ ብሎ እንኳን ቢነግራቸው የምርጫውን ትክክለኛነት እንዲያጣሩለት ወላጆችን ማማከሩ የግድ መሆኑን ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ባህላዊ አስተሳሰብ በብዙ ጎኑ ጠቀሜታ ያለው ይመስላል፡፡ አንደኛው ልጆቻቸው ያልተገባ የትዳር አለም ውስጥ እንዳይቡ ለማድረግ ይረዳል፡፡የትዳር አለም እንደሚታወቀው አንዴ በመጥፎ ምዕራፍ ከተጀመረ ለማረም ቢሞከር በርካታ የስነ ልቦናና ተያያዥ ጠባሳዎችን ተቶ ያልፋል፡፡ በአሁን ሰአት እየተስተዋለ ያለው ከጋብቻ ማግስት የእንፋታ ጥያቄ በየፍርድ ቤቱ ዶሲ ይዞ የመዞር ችግር ሳያጠኑና ሳይጠናኑ በተለይ ደግሞ የወለጅና የዘመድን ጣልቃ ገብነት፣ ምክር ወደ ጎን ጥሎ ልጆች ሁሉንም ነገር እኛ እናውቃለን እኛ እንፈጽማለን ብለው የሚመሰርቱት ጋብቻ ከጥቅሙ ጉዳቱ አያመዘነ ነው፡፡ የቀረበው የወላጅ ጣልቃ ገብነት ሀሳብ ይህንን ግዙፍ የሆነ የሰው ልጅ የሚያልፈው ከባድ ምዕራፍ የተሳካ እንዲሆን ለማድረግ ያለመ ይመስላል፡፡

#### 4.2.1.1 ጋብቻ ክልክል ‹‹ቦሎቻ ከመኖ ሴራ››

በከምባታ ባህል ጋብቻ ክልክል‹‹ ቦሎቻ ከመኖ ሴረ›› ተብለው በማህበረሰቡ የተለዩ በርካታ የደም ዝምድና ቆጠራና በፍቃደኝነት ፈልገው በዝምድና መተሳሰር ናቸው፡፡ ይህንን ሥርዓት አስመልክቶ መረጃ አቀባዮች እንዲህ ሲሉ ያብራራሉ፡፡ አንድ ልጁን ለጋብቻ የተጠየቀ ቤተሰብ ሴት ልጁ ለጋብቻ ከመፍቀዱ በፊት ለጋብቻ የጠየቀውን ልጅና ቤተሰብ የሥጋ ዝምድና መኖሩን ያጣራል፡፡ ለጋብቻ የማይፈቀዱ የዘር ግንዶች የልጅቷ አባት እና እናት ጎሳዎች በሙሉ፣ ከልጁ እናት አባት ጎሳዎች ጋር ምንም ዓይነት የዘር የስጋ ግንኙነት አለመኖሩን ማጣራት የመጀመሪያ ተግባር ሲሆን ሁለተኛው ‹‹እሌ እለንሰት›› የዓይን ዝምድና ይታያል፡፡ ይህ የዝምድና ዓይነት በከምባታ ባህል ወንድ ልጅ የሚገረዘው ለአቅመ አዳም ሲደርስ ነው፡፡ ይኸውም ከ14-18 የዕድሜ ክልል ውስጥ ሲገባ ይገረዛል፡፡ በዚህ ጊዜ ግርዛቱ ሲካሄድ ዓይኑን የሚይዝለት በጣም የሚወደውና የሚቀርበው ጓደኛውን ይመርጥና ዓይኑን እንዲይዝለት ያደርጋል፡፡ ይህ በተገረዘው ልጅ ቤተሰብና ዓይኑን በያዘው ልጅ ቤተሰብ መካከል ዝምድና ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡ይህንን የዝምድና ዓይነት ሲገልጹ ዓይን መያዝ ማለት ለከምባታ እኔ አንተን በክፉ ነገር ካሰብኩህ ወይም ከነካው ዓይኔ ይጥፋ የሚል ትርጓሜ አለው ፤ የቅርብ ዘመድና ቤተሰብ ነን ማለት ነው፡፡ስለዚህ በዚህ የተሳሰረ ቤተሰብ ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡፡

ሶስተኛው ‹‹ ኡኑኒ እለንሰተ›› የጡት ዝምድና ነው፡፡ የዚህ ዝምድና ዓይነት ሁለት ሰዎች ከተዋደዱ እኔና አንተ ወይም እኔና አንቺ ዝምድና መፍጠር አለብን ይባባሉና ቃል ኪዳን ይገባባሉ፡፡ ይኸውም አንዱ የአንዱን ጡት ይጠባል፡፡ ወንድ ከወንድ ወይም ወንድ ከሴት እንዲሁም ሴት ከሴት ሊሆን ይችላል፡፡ ጡት ተጠባቡ ማለት ላለመለያየት ቃለ መኃላ ፈጸሙ ማለት ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት ቤተሰቦች መካከል ከባድ ዝምድና ተፈጥሯል ብለው ያምናሉ ፡፡ ስለዚህ ጋብቻ መፈጸም አይችሉም ፡፡ ልጃቸውን ከመዳራቸው በፊት ይህንን ዝምድና ያጣራሉ፡፡

ሌላው ጋብቻ ክልክል ማህበረሰቡ ለጎሳዎች የሰጠው ደረጃ ነው፡፡ በከምባታ ባህል ከሌሎች ጎሳዎች ጋር እንዲጋቡ የማይፈቀድላቸው ጎሳዎች አሉ፡፡ እነሱም ፉጋ፣አግዛ፣አዋዶ እና ሰጋ ናቸው፡፡እነዚህ ጎሳዎች እርስ በእርስ እንጂ ከሌላ ጎሳ ጋር እንዲጋቡ ባህሉ

አይፈቅድላቸውም፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ ልጁን ከመስጠቱ በፊት ጎሳው ከእነዚህ ጎሳዎች ውጪ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ጋብቻ ከልክል ለከምባታ የስጋ ዝምድና ብቻ አይደለም፡፡ወይም ጋብቻ ለመፈጸም የሚከለከለው በስጋ መዛመድ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከስጋ መዛመድ እኩል የዝምድና ደረጃ ያላቸው በግርዛት ምክንያትና በጡት መጠባባት የሚፈጥሩት ዝምድና ጭምር ናቸው፡፡ እዚህ ላይ የምንገነዘበው ከመዋለድ ወጪ ሰዎች ፈልገው ያለ ስጋ ንክኪ በደም የመዋሀድን ያህል ዝምድና መፍጠርና ጋብቻ እስከ አለመፍቀድ ድረስ  የሚደርስ በዝምድና የሚተሳሰር ማህበረሰብ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ሌላው ማህበረሰቡ በራሱ መመዘኛ ከጎሳዎች መርጦ በጋብቻ ከሌላው ጋር እንዳይጣመሩ የማድርግ ሂደት ነው፡፡ይህ ለማህበረሰቡ የተሰጠው ማህበራዊ ደረጃ ያሰየናል፡፡በጋብቻ መጣመር የሚገባው ጎሳና የማይገባው ጎሳ ተብሎ ተለይቷል፡፡

### 4.2.1.2 ‹‹ጪቹ ጡደቁ›› ገድ የማየት ሥርዓት

‹‹ጪቹ›› የሚለው ቃል ቀዋተኛ ፍቺ ወፍ ማለት ነው ፡፡አውዳዊ ፍቺው‹‹ጪቹ ጡደቁ›› ማለት  ገድ ማየት ማለት ነው፡፡ለዚህ ጥናት አጥኚዋ የምትጠቀመው አውዳዊ ፍቺውን ነው፡፡ገድ ማየት የራሱ የሆነ ስርዓት አለው፡፡ይህ ሥርዓት የሚፈጸምበት ዋና ዓላማ ጋብቻው ትክክለኛ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለማረጋገጥ የሚፈጸም ነው፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው ይበጃል ያሉትን በራሳቸው መመዘኛ ከመረጡ በኋላ ምርጫቸው ትክክል መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጡት ‹‹በጪቹ ጡደቂ›› ሥርዓት ነው፡፡ እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገላጻ የአጠያየቁ ሥነ-ሥርዓት የሚጠይቀዉ የወጣት ልጁ አባት ለጓደኛዉ ‹‹አንተ እገሌ ሂድና በአቶ እገሌ ቤት ያለችዉን ልጅ እይ›› ይሉታል፡፡ አስተያየቱ የራሱ የሆነ ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት የተከተለ ነዉ፡፡ ይኸዉም፡- የአግቢዉ ጓደኛ  ለልጁ አባትህ በአቶ እገሌ ቤት ያለችዉን ልጅ እዩና ‹‹ጭዕቹ ጡጅዬ›› ገድ ተመልከቱ ብለዋል ብሎ ይነግረዋል፡፡ ተመካክረዉ የመሂጃ ቀናቸዉን ይወስናሉ፡፡ ገድ የሚታይበት ቀን ሁሉም ቀናት ሳይሆኑ ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ ቅዳሜና እሁድ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ ዉጭ ሰኞ፣ እሮብና ዓርብ ለጥያቄ ወይም ገድ ለማየት ወደ ልጁቷ ቤት አይኬድም፡፡ ምክንያቱም ሰኞ ከዚህ

በፊት በጣሊያን ወረራ ጊዜ ብዙ የብሔረሰቡ ሰዎች በጦርነቱ ያለቁበትና ብዙ ደምም የፈሰሰበት ነዉ፡፡ ደግሞም ደረቅ ቀን ነዉ በሚል አይወደድም፡፡ ሌላዉ ደግሞ ሐሙስና ዓርብ ኀዶሎ ቀናት ናቸዉ ተብለዉ ስለመታመኑ የገድ መታያ ቀናት አይደሉም፡፡ የገድ እዩ ሥነ-ሥርዓት ወጣቶች በባህሉ መሠረት ቁምጣና ከላይ ጥቡቆ ለብሰዉ ካስፈለገም ስስ ነጠላ ደርበዉ ፀጉራቸዉን አበጥረዉ፣ ቆብ ድፍዉ ተቀባብተዉና ረጃጅም በትር ይዘዉ ከላይ ከተጠቀሱ ቀናት በአንዱ በረፋድ አከባቢ ወደ ልጅቷ ቤት ይሄዳሉ፡፡ የልጅቱ ወላጆች ድንገት ቤት ያሉ ከሆነ ያጣራሉ፡፡ ወላጆች ቤት እያሉ መግባት ስለሚፈራና የወላጅ ፊት ካየ ምን ዓይነት ዓይን አዉጣ (ዓይነ-ደረቅ) ነዉ ይባላል፡፡ በርግጥ ከሰዓት በኋላም ወላጆች ቤት በማይኙበት ሰዓት በማጠያየቅ ሊሄዱም ይችላሉ፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ የልጅቱ ወላጆች ቤት ካሉ ከቤት ዞር ይላሉ፡፡ አግቢዉና ጓደኛዉ ተያይዘዉ ሲሄዱ ወይም ገና ከሠፈራቸዉ እንደወጡ በመንገዳቸዉና ከፊት ለፊት የወጣዉን ሰዉ፣ እንስሳ እና እንቅፋት የመታቸዉ እንደሆነም እያስተዋሉ ይሄዳሉ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ያጋጠማቸዉ ነገር ትርጉም ይሰጠዋልና ነዉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሴት ባዶ እንስራ ተሸክማ ዉሃ ለመቅዳት ወደ ምንጭ ወይም ወደ ወንዝ ስትወርድ ካገኙዋት ጥሩ ገድ አይደለም ‹‹ጪቹ ከሜኔ አስምባ›› ይባላል፡፡ የጥሩ ነገር ተምሳሌት አይደለም፡፡ እንዲሁም ሚዳቋ ከፊት ለፊታቸዉ አቋርጣ የሄደች እንደሆነ ደረቅ ናት ተብሎ ስለሚታመን አይወደድም፡፡ሴት ልጅ አቋርጣቸው ያለፈች አንደሆን፣ በመንገድ ላይ ግራ እግራቸዉንም እንቅፋት የመታቸው ከሆነ ገዱን ይጠራጠራሉ፡፡ ‹‹ ጭዕቹኔ ደናሚባ›› የተሳካ ገድ አይደለም ይባላል፡፡በልጅቷ ቤት ሲገቡ ልጅቷ ከሌለች ፣ ቤት ዝግ ከሆነ፣ በቤት ውስጥ ታሞ የተኛ ሰው ካለ አይጥ ወይም እባብ መንገድ ላይ ያጋጠማቸው እንደሆነ፣ የቤት ጥራጊ ይዛ ስትወጣ በበር ላይ ያገኟት እንደሆነ ፣ ከቤት ዉስጥ አመድ አፍሳ ስትወጣ ካገኟዋት በመጥፎ ስለሚተረጎም ገዱ ጥሩ አይደለም ይባላል ፡፡

ከላይ የቀረቡት ገደ መጥፎ ተብለው የህብረተሰቡን እምነት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ባዶ እንስራ የተሸከመች ሴት ካገኙ ጋብቻ ምንም የሌለው ባዶ ደሀ ይሆናል የሚል እምነት ያላቸው ይመስላል፡፡ ሚዳቋን ደረቅ ናት ብለን እንወስዳለን ሲሉ ከባዶ እንስራው ጋር የሚያያይዙት ነገር አለ፡፡ ይኸውም ሚዳቋን በደረቅ ከመሰሉ ትዳር በተመሳሳይ ያጣ የነጠ

ምንም የሌለው በችግር የተሞላ የታጀበ ይሆናል የሚል ስጋት ያለው ነው፡፡ ሌላው ሴት ልጅ ያቋረጠቻቸው እንደሆነ ገደ መጥፎ አድርጎ ይወስዳሉ፡፡ በአጠቃላይ በሀገራችን ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ባህል ዘንድ እንደሚስተዋለውና እስካሁንም ያልተቀረፈው ሴት ልጅን ዝቅ አድርጎ የማየት አስተሳሰብ በከምባታ ብሄረሰብ ይኸው ሲንጸባረቅ ይታያል፡፡ በዚህ ሀሳብ ለፆታ የሰጡትን ደረጃ ማየት እንችላለን፡፡ ሴትን ጥሩ ስፍራ ላይ ካለማስቀመጥ የመነጨ እምነት ነው የመጥፎ ገድ መገለጫ ሆና የታሰበችው፡፡

ከእንቅፋት መመታት ጋር የተያያዘው ሀሳብ ስናይ እንቅፋት በየትኛውም መመዘኛ ጥሩ ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን ልዩነቱ ቀኝ እግርና ግራ እግር የሚለው ነው፡፡ ግራ ሲባል ብዙ ጊዜ የማይገባ፤ የማይመች፤ የማይሆን ተደርጎ ይወሰዳል፤ ከዚህ የተነሳ ይሆናል ለጋብቻ ግራ እግር በእንቅፋት መመታት መጥፎ ተምሳሌት ሆኖ የቀረበው፡፡በልጅቷ ቤት ሲገቡ ልጅቷ ከሌለች… የሚለው ሀሳብ አሁን ጋብቻው (ትዳሩ) ምንም የሌለው ባዶ ወይም ልጅቷ በቤት ውስጥ የሌለችው ለትዳሩ ያልተፈቀደች ስለ ሆነች ነው የሚል ዓይነት እንድምታ ያለው ነው፡፡ ህመም፣ የቤት ጥራጊ፣ አመድ፣ እባብ፣ አይጥ ስናያቸው የመጥፎ፣ የክፉ እና ቆሻሻን ነገር የሚወክሉ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ በጋብቻ እሳቤ ላይ ሲያመጡት እነዚህ ጋብቻ እንዳንመሠርት ወደ መጥፎ ትዳር እንዳንገባ ወፏ የሰጠችን ምልክት ነውና ይህ ጋብቻ የሰመረ አይሆንምና መመስረት የለበትም የሚል እምነት አላቸው፡፡ በአጠቃላይ መጥፎ ገድ ነው ብለው የሚያስቀምጡት ባዶ፣ ግራ፣ አለመኖር፣ ደረቅ፣ ህመም፣ አመድ፣ ጥራጊ፣ መርዛማነት፣ የፆታ የበታችነት ወዘተ… ጋብቻ እንዳልተፈቀደ ማሳያ ምልክቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

ከዚህ በታች ወደ ልጅቱ ቤት ሲገቡ እንደ ጥሩ ገድ፣ ‹‹ ደናሞ ጨቺ ›› የሚታዩ ምልክቶች

1ኛ እበት እየዛቀች
2ኛ ወተት እየናጠች
3ኛ ላሞችን እያላበች
4ኛ የስፌት ዕቃ እየሰፋች የገቡ እንደሆነ
5ኛ ወደ እሷ ቤት ሲሄዱ ቀኝ እግር እንቅፋት ከመታው

6ኛ ትልልቅ ሰዎች በተለይም ወንዶች ያጋጠሟቸዉ እንደሆነም

7ኛ ቡና እየቆላች ከነበረ

8ኛ ዉሃ ቀድታ ከምትመለስ ሴት ጋር የተገናኙ እንደሆነ

9ኛ እንሰት ስትፍቅ ከደረሱ

10ኛ እህል ተሸክማ ከቤት ስትወጣ ካገኗት

11ኛ ጥሩ ልብስ ለብሳ ከቤት ስትወጣ ወይም መንገድ ላይ ያገኗት እንደሆን ጋብቻ የተፈቀደና መልካም ይሆናል ተብሎ ይወሰዳል፡፡

ከላይ ገደ ጥሩ ተብለው የቀረቡትን ሀሳቦች ስንመለከት እበት እየዛቀች ፣ ላሞችን ያለበች ፣ ወተት እየናጠች፣ እህል ተሸክማ እና እንሰት እየፋቀች፣ የተገባ ከሆነ ሀብታም ናት ጥጋብ ነዉ፡፡ ጥሩ ገድ ነዉ ብለው ያምኑ ይመስላል፡፡ ሌላዉ ደግሞ የስፌት ዕቃ እየሰፋች የገቡ እንደሆነ ዝምድናችንን እየሰፋች ወይም የጠበቀ ግንኙነትን እየፈጠረች ነዉ ተብሎ ስለሚታመን ጥሩ ገድ ተብሎ ይወሰዳል፡፡

ከላይ በመጥፎ ገድ የተነሳው እንቅፋት እዚህ ቀኝ እግርን ቀይሮ በመልካም ገድ ቀርቧል፡፡ እንቅፋቱ በቀኝ እግር ሲሆን ወደጥሩ ገድነት ይቀየራል፡፡ ከላይ በመጥፎ ገድነት የተወሰደው ግራ እግር በመሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የሚወደደውና የሚጠላው የግራና የቀኝ ጉዳይ እንጂ ጉዳዩ የእንቅፋት አይደለም ማለት ይቻላል፡፡ ቀኝን ብዙ ጊዜ የጥሩ ነገር ተምሳሌት አድርጎ የመውሰድ ነገር ነው፡፡ በጥሩ ገድ ላይ የምናስተውለው በተቃራኒው ወንዶች የጥሩ ገድ ተምሳሌት ሆነው ሲቀርቡ እናያለን፡፡ ይህ በግልፅ የሚያሳየው ነገር ለሴቶች ያላቸውን ዝቅተኛ ግምትና ለወንዶች ያላቸውን ከፍተኛ ግምት ነው፡፡ በአጠቃላይ ጥሩ ገዶች የተባሉትን ስናይ የከብት ርቢ፣ቀኝ፣ሙሉ ፣እህል፣ወንድ፣ቡና፣ጥሩ ልብስ፣ ስፌት ወዘተ ናቸው ፡፡

| መጥፎ ገድ | | ጥሩ ገድ | |
|---|---|---|---|
| ባዶ እንስራ | ኢ. ስኬት | እህል | ስኬት |
| ግራ | ኢ.-ስኬት | ከብት እርባታ | ስኬት |
| ቤት አለመኖር | ኢ. ስኬት | ቀኝ | ስኬት |
| ቀበሮ | ኢ. ስኬት | ሙሉ | ስኬት |
| ህመም | ኢ. ስኬት | ወንድ | ስኬት |
| አመድ | ኢ. ስኬት | ስፌት | ስኬት |
| የቤት ጥራጊ | ኢ. ስኬት | ቡና ማፍላት | ስኬት |
| ሴት | ኢ. ስኬት | እንሰት | ስኬት |
| እባብ | ኢ. ስኬት | | |
| አይጥ | ኢ. ስኬት | | |
| የተዘጋ ቤት | ኢ. ስኬት | | |

በኢ. ስኬት ዘርፍ የተቀመጡ የመጥፎ ገድ ወክልና የተሰጣቸው ለምንድ ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ተወያይዎቹ ሲያብራሩ፡- ለጋብቻ ኢ. ስኬት ናቸው ተብለው በማህበረሰቡ ዘንድ የተፈረጁትን ተላልፎ ጋብቻ መፈጸም መጨረሻው በጋብቻው እየተሰቃዩ መኖር ወይም መሞት ነው፡፡ሞቱ የሚከሰተው ሴቷ በምትወልድበት ጊዜ ትሞታለች፡፡የባል ዕድሜ በአጭር ይቀጫል፡፡ ለምሳሌ እባብ በባህሪው መርዛማና የሰው ጠላት ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሰውም እሱን ካገኘ ጭንቅላቱን ቀጥቅጦ ይገለዋል፡፡ እባቡም አጋጣሚ ካገኘ ነድፎ ለመግደል የሚጥር ፍጡር ነው፡፡ ይህ መርዛማ ፍጡር ስለልጅቷ ጋብቻ ጉዳይ አንስተው ገዷን ለማየት ወደ ቤትዋ ሲሄዱ መንገድ ላይ ይሁን በልጅቷ ግቢ ወይም ሲመለሱ ካጋጠማቸው ጋብቻው እንደይፈጸም ወፏ ልካ ነግራናለች ማለት ነው፡፡ይህ

ገድ መጥፎ ነውና ጋብቻው አይፈጸምም፡፡አይጥንም ብንወስድ እንዲሁ የመጥፎ ገድ ተምሳሌት ነች፡፡አይጥ ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ እያሰሰች፣ እያሳደደች የምትበላ፣ የምትቆራርጥ፣ እህል፣ ልብስ፣ ምግብ፣ ወዘተ… የምታበላሽ ፍጡር ናት፡፡ስለዚህ የጥሩ ገድ ተምሳሌት ልትሆን አትችልም፡፡ሌላው የቡድን ተወያይ ስለ ቤት ጥራጊ መጥፎ ገድነት ሲያነሳ ያለቀለት ከዚህ በኋላ ጥቅም የማይሰጥ የሚጣል ተፈላጊ ያልሆነ ነገር ነው ፡፡ስለዚህ ለጋብቻ የተፈለገችው ልጅ ገድ ለማየት ወደ ቤቷ በተገባ ሰዓት የቤት ጥራጊ ስታወጣ ወይም በእጇ ይዛ ወይም እየጠረገች ከተገኘች ጋብቻ ውስጥ የሚቀላቀል ቆሻሻ አለ ተብሎ ስለሚወሰድ ጋብቻው እንደይፈጸም ይደረጋል፡፡

ሌላው በውይይቱ የተነሳው የልጅቷ እቤት አለመኖርና የተዘጋ ቤት ነው፡፡ገድ ለማየት በልጅቷ ቤት ሲኬድ በሩ ዝግ ከሆነ ልጅቷ ለጋብቻው ያልተፈቀደች ናት፡፡ምክንያቱም በሩ ዝግ ሆነ የጋብቻውም ሀሳብ ይዘጋ አይቀጥል የሚል የወፏ መልዕክት ነው፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ቤቱ ክፍት ሆኖ ነገር ግን ልጅቷ እቤት ባትኖር ለትዳሩ አለመሆኗን ለማሳወቅ ወፏ እንዳትኖር አድርጋት ነው፡፡የሚል ሀሳብ አቅርበዋል፡፡የቡድን ተወያዮች ሁሉ ምክኒያት መስጠት ያልቻሉበት የገደ መጥፎ ተምሳሌት የሆነችው ሴት ናት ሃሳብ ሰጪዎች ሴቶችን እንወዳቸዋለን ነገር ግን ገድ ለማየት በሚኬድበት ጊዜ ሴት ካቋረጠች መጥፎ ገድ ነው እንላለን የወፏ መልክት ነው የሚል ማምለጫ ምክንያት ሲያቀርቡ ተስተውለዋል፡፡

የአመድ መጥፎ ገድነት ምክንያት ሲገልጹ ብዙ መጥፎ ትርጓሜ ያለው ነው፡፡ አንዱ ምንም የሌለው ያጣ የነጣ ጋብቻን ያሳያል፡፡ በቀጥታ ስንወስደውም እሳት ነዶ ሲያበቃ የቀረው በእጅ የማይያዝ ዱቄት ሆኖ የቀረ የማይጠቅም ነገር ስለሆነ ለጋብቻ የታሰበችው ልጅ ይህንን አመድ ዝቃ ስታወጣ ከተገኘች ጋብቻው እንደዛው እንደ አመዱ ይሆናል፡፡ የሚል ሀሳብ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘው ስለ ህመም መጥፎ ገድነት ሲገልጹ ህመም አንዱ የሞት መንደርደሪያ ነው፡፡ሁለተኛው ህመም ሰው ስጋው ፣ መንፈሱ ፣ ሕይወቱ ሊታወክ ይችላል፡፡ ጋብቻው በዚህ መልክ ሊታወክ ይችላል፡፡ ስለዚህ ለጋብቻ በተፈለገቸው ልጅ ገድ ለማየት ሲገባ እቤት ውስጥ አንድም ሰው ታሞ የተኛ ካለ ጋብቻው እንዳይካሄድ ይደረጋል፡፡

ሌላው መረጃ አቀባይ ስለቀበሮ መጥፎ ገድነት ሲገልጹ ቀበሮ በተፈጥሮ ቀዥቃዣ ሁል ጊዜ የምትሮጥ  ብቻ መልካም ነገር የሌላት እንስሳ ናት፡፡ እሷ ካቋረጠች ጋብቻ የሰመረ አይሆንም፡፡ አያይዘው ስለ ግራ ነገር ሲያወሩ ግራን ለምን ጊዜም ጥሩ ገድ አድርጎ አይወሰድም፡፡ በግራ እጇ የምትበላ ፣ በግራ የምትጽፍ ፣በግራ እጇ የምትሰራ፣ እንዲሁም የልጅቷን ገድ ለማየት ወደ እሷ ቤት ሲኬድ ግራ እግር እንቅፋት ከመታ ብቻ ማንኛውም ግራ ከምባታ አይወድም፡፡ በጋብቻ ወቅት እነዚህ ይጣራሉ፡፡

ከላይ የቡድን ተወያይዎችን ሀሳብ ስናይ እምነታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ጾታዊ አስተሳሰቦችን ከሚገልጹት ቋንቋ መረዳት ይቻላል፡፡ እምነት የሚገልጹ ሀሳቦች አንዲት ወፍ አለች የገዱን ጥሩና መጥፎ መጥታ ትነግረናለች… የሚሉት አስተሳሰባቸው የወለደው በክፉ ነገር ተምሳሌትነት የወከሏቸውን ነገሮች የነገረችን ገዱን ለማየት ስንቀሳቀስ ማግባት ያለብን ከሆነ ጥሩ ገዶችን በፊታችን ታመጣለች፡፡ እንዳናገባ ከፈለገች መጥፎ ገዶችን እያመጣች የምትፈቅድልንና የምትከለክለን ወፏ ናት የሚል እምነት እናያለን፡፡ እምነት መሆኑን የምንረዳው በምንኖረው አለም ያለችው ወፍ በአካላዊ አለም በአፏ እየተናገረች ይሄ ክፉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ ነው፡፡ እያለች ጋብቻ የምፈቅድና የምትከለክል ወፍ የለችም፡፡ ነገር ግን አእምሯቸው የፈጠረው የማይታይ አለም ውስጥ ያለች አንድ መልዕክተኛ ፈጥረው እያዳመጡ የሚታዘዙላት ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ለማምለጫነት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ ምክንያቱም ለምን ጋብቻውን እምቢ አልክ ቢባል እኔ አይደለሁም፡፡ ለምን እሺ አልክ ቢባል እኔ አይደለሁም ወፏ ነች በማለት ያመልጡበታል፡፡

ከባህል አንጻር ስናይ በከምባታ ማህበረሰብ ዘንድ ስለ ቅድመ ጋብቻ ሲነሳ የገድ ጥሩና መጥፎ ጉዳይ አብሮ ይነሳል፡፡ ይህ በህብረተሰቡ ውስጥ የሰረጸ ጉዳይ ነው፡፡ባህል አድርጎታል ማለት ነው፡፡ሌላው ከቋንቋ አገላለጻቸው ውስጣዊ መልዕክት የምንረዳው ለጾታ ያላቸውን ግምት ነው፡፡ሴት ልጅን የመጥፎ ገድ ተምሳሌት አድርገው ሲስሉ በአቅም ደካማ፣ አስተሳሰቧ ዝቅ ያለ ወዘተ ብለው አስበው ስለመሆኑ ማረጋገጫው ሁሉም የመጥፎ ገድ ተምሳሌቶች ትረጉማቸውን ሲያብራሩ የሰውን ልጅ በአንድም ሆነ በሌላ የሚጎዳ እንስሳ፣ ነገር፣ ሁኔታ መግለጻቸው በሴት ላይ መጥፎ ግምት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሴት በመጥፎ የተመሰለችው ለምንድ ነው? የሚል ጥያቄ ሲቀርብላቸው ለመግለጽ አልደፈሩም፡፡ በወፏ ለማሳበብ እሷ የወሰነችው ነው ብለው ለማምለጥ ጥረት ያደረጉ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል መረጃ ተቀባይዋ ሴት ስለሆነች ስነ ልቦናዋን ለመጠበቅ ታስቦ ይሆናል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በጥሩ ገድ ተምሳሌትነት የተፈረጁ የጋብቻ ስኬት መገለጫዎች እንዴት ጥሩ ሊባሉ ቻሉ? የሚለው ጥያቄ ለቡድን ተወያዮች የቀረበ ሲሆን ተወያዮቹ ሲገልጹ፡- ለምሳሌ እህልን ብንወስድ ለሰው ልጅ ለኑሮ የሚጠቅም ነገር ነው፡፡ ስለዚህ አግቢዋ ለጋብቻ ገድ በሚታይበት ሰዓት እህል ስታበጥር ሆነ ስትፈጭ ከተገኘች ገዷ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ጋብቻዎ ምግብ የተትረፈረፈበት ስኬታማ ኑሮ ትኖራለችና ነው፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘው ከብትና የከብት ውጤቶችን ስታከናውን ከተገኘች ከብት ስታግድ፣ እበት ስትዝቅ፣ወተት ስታልብ፣ ወተት ስትንጥ ከተገኘች፣ ይህ ብቻ ሳይሆን እንሰት ስትፍቅ፣ ቆጮ ስትቆርጥ፣ ቂጣ ስትጋግር ከተገኘች እነዚህ ሁሉ የሀብታምነት ማሳያዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥሩ ገድ ተብለው ይወሰዳሉ፡፡ ስለ ቀኝ እና ስለ ሙሉ ነገር ሲገልጹ እንዲሁ የመልካም ነገር ተምሳሌት መሆን ያስረዳሉ፡፡ በተለይ ሙሉ ነገር ለከምባታ ከባድ ትርጉም አለው፡፡ ሙሉ እንስራ ውሀ፣ ሙሉ ኩባያ መጠጥ ካዩ ከቀመሱ በመልካም ነገር ይወስዳሉ፡፡ ስለዚህ ለጋብቻ የታሰበችው ልጅ በእንስራ ሙሉ ውሀ ተሸክማ ስትመጣ ከተገኘች የጥሩ ገድ ባለቤት ነችና ጋብቻው የተሳካ ነው፡፡ ሌላው የሚነሳው የጾታ ጉዳይ ነው፡፡ስለሴቶች ከላይ ተነስቷል፡፡ ወንዶች የጥሩ ገድ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ለትዳር የታሰበችው ልጃገረድ ገድ ለማየት በሚኬድበት ጊዜ የትኛውንም ስፌት ስትሰፋ ከተገኘች በሁለት መልኩ ትርጓሜ ይሰጠዋል፡፡ አንዱ ባለሙያነቷ ሁለተኛው ዘመድ የምታቀራርብ የምታገናኝ የፍቅር ሰው ነች ተብሎ ስለሚታመን እንደ ጥሩ ገድ ይወሰዳል፡፡

ከላይ የቀረበው የተወያዩች አስተያየት ከእምነት፣ ከባህልና ከጾታዊ አመለካከት አንጻር ስናይ እምነቱ ከላይ በመጥፎ ገድ የተነሳው እምነት በዚህም ላይ ተመሳሳይ ነው፡፡ ባህሉ ማህበረሰቡ አምኖበት ለጥሩ ገድ ተምሳሌት ባስቀመጣቸው ህጎች ይመራበታል፡፡ከጾታ አንጻር በመጥፎ ገድ የተነሳው የሴቶች ጉዳይ በጥሩ ገድ በወንዶች ላይ መነሳቱ በትክክል ለጾታ ያላቸውን ከፍተኛና ዝቅተኛ ግምት ማረጋገጫ ነው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ገዶች ለማጣራት ወደ ልጅቱ ቤት ሲገቡ አግቢዉ ቀደም ብሎ ይገባል፡፡ ሲወጡም በኋላ የሚወጣዉ አግቢዉ ነዉ፡፡ ይህ ልጅቷን ለማየት እሷም እንደመሸኘት እያለች ለመተያየት እንዲመች የሚደረግ ባህላዊ ቅደም ተከተል ነዉ፡፡ በገድ የመተያያ ወቅት ላይ አግቢዉ የማትፈልገዉ የናቀችው ከሆነ የምታሳያቸዉ ምልክቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

1ኛ ጓደኛዉና አግቢዉ እንደገቡ መቀመጫ ቦታቸዉን ከያዙ በኋላ የቤቱን ወለል ትጠርጋለች፡፡ ያ ማለት አቧራ አቦነነች ስለሚባል መጥላቷን መግለጫ ነዉ፡፡

2ኛ ጋያ ባህላዊ ማጫሻ ስጭን ብለዉ ሲጠይቋት በጋያዉ አናት ላይ ደረቅ ኩበት ወይም በርበሬ ጨምራ ትሰጣለች ፡፡ ይህም ማለት ጋያዉን ሳብ ሳብ ሲያደረግ በርበሬዉ ያስነጠሰዋል፤ ካልሆነም ያስለዋል፡፡ በዚህም የማን ሳላም ነዉ ቤታችንን በጉንፋን አታበላሽ ዉጣልን ማለት ትጀምራለች፡፡

3ኛ ሳይጠማዉም ዉሃ ስጭኝ ይላታል ፡፡ ውሃዉም ብዙ ካለማመጠች በኋለ ንጽህና በጎደለዉ ዕቃ ትሰጣለች ፡፡ ዉሃዉን ስታቀብል ፊቷን ለማየት እጇን ዞር ዞር እያደረገ ያስቸግራታል፡፡ ላለማየት ስትል ዉሃዉንም ይዛ ትመላለሳለች፡፡

ሌለዉ ደግሞ የመዉደዷ ምልክቶች ፡-

1ኛ/ ስትጠራ አቤት! ብላ ጥሩ ምላሽ ትሰጣለች፡፡

2ኛ/ ጋያ ስትጠየቅ ጥሩ የተቀመመ ትምባሆ ጨምራ ትሰጣለች፡፡

3ኛ/ ዉሃ ስትሰጥም ተረጋግታ በጥሩ አና በንጹህ ዕቃ ትሰጣለች፡፡ እየተሽኮረመመች ለማየት ለእርሱ ሲጭዉ ለእርሱም ሲጭዉ ብትባልም ሳትበሳጭ ታስተናግዳለች፡፡

የገድ መተያየት ስነስርዓት ወይም በመንገድም ሆነ በልጅቱ ቤተሰብ በቤታቸዉ ያጋጠማቸዉን ሁሉ የልጁ ጓደኛ ‹‹ጃላ›› ለአባትየዉ ይህን ይህን አየን ብሎ አንድ በአንድ

ይነግራቸዋል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰዉ የመጥፎ ገድ ተምሳሌት ከሆነ ሌላ ቦታ ተልኮ እንደገና እንዲተያዩ ይደረጋል፡፡ የጥሩ ገድ ከሆነ ደግሞ የልጁ አባት ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ሁለት ሽማግሌ ‹‹ጭዕቹ ጡንዴም››ገድ አይተናል፡፡ ልጃችሁን ለልጃችን እንዲሉ ይላካሉ፡፡ ሁለት ሽማግሌዎች ልጅህን ለልጄ መልዕክት ይዘው ወደ ልጅቷ ቤት ሲገቡእቤት ገብተው ከተቀመጡ በኋላ የሚሉት፡-

አደቤ አና ጡማ ጡማ ሆሴንታ

የልጁ አባት ሰላም ሰላም ደህና ዋላችሁ

ሚኒ መኑ ጡማ ጡመንከ ሆንሴም

የቤት ሰው ደህና ሰላም ውለናል

እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በኋላ ጥቂት ደቂቃ ቁጭ ካሉ በኋላ ይቆሙና ሀሳብ ማንሳት

የሚጀምሩት የልጁ አባት ናቸው ፡፡

አደቤ አና ጭዕቹ ከሚኔ አስቴኤ

የልጁ አባት ወፏ እዚህ ቤት ሰጥታኛለች

አደቤ አና ከ ምኔን ቀለማም

የልጁ አባት ከዚህ ቤተሰብ ጋር መዋለድ እንፈልጋለን፡፡

ሜሴሌ አና ሀቃቃም --- ቦኪን ኤረማም ለሙ ሂዜቱ አስዬኤ

የልጅቷ አባት ህልሜን አያለሁ ከዘመዶቼም ጋር እመካከራለሁ ሁለት ሳምንት ስጡኝ --

ሽማግሌዎቹም የአባትዋን ሀሳብ ተቀብለው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

የሁለቱን ቤተሰብ የሀሳብ ልውውጥ ስንመለከት የልጅቷ አባት ከሰላምታ ልውውጣቸው በኋላ ያቀረቡት ሀሳብ ‹‹ጪቹት ከ ሚኔን አስቴ ›› ወፏ ከዚህ ቤት ሰው ሰጥታናለች፡፡

ሲሉ ወፏን መስለው የሚያዳምጡ አእምሯቸው የፈጠረው አንድ መልዕክተኛ አድርገው ያስቀመጡትና ይህ መልዕክተኛ መጥቶ ልጃችሁ ከእኛ ቤተሰብ ጋር ጋብቻ እንድትፈጽም አረጋግጦልናል፡፡ ለዚህ ነው የመጣነው፡፡ ወፏ ከፈቀደችልን ደግሞ ከዚህ ቤተሰብ ጋር መቀላቀል ዝምድና ማፍራት መዋለድ እንፈልጋለን፡፡ የሚል ሀሳብ ማስተላለፋቸው ነው፡፡ የልጅቷ አባት ሲመልሱ ‹‹ሀቃቃም ቦኪን ኤረማም›› ህልሜን አያለሁ፤ ከዘመዶቼ ጋር እመካከራለሁ፡፡ የሚል ምላሽ ሲሰጡ መልሳቸው ወፏ ላንተ ከዚህ ቤት ጋር እንድትዋለድ ከነገረችህ ለእኔም ትነግረኛለችና እኔም የእሷን መልዕክት እጠብቃለሁ፡፡ ለማለት ነው ፡፡ ህልሜን ልጠብቅ ሲሉ ለጥሩና ለመጥፎ ገድ ያስቀመጡት መመዘኛ ብቻ ሳይሆን ወፏ መልዕክቷን የምትገልጸው በህልምም መጥታ እንደምትናገር እምነት እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡ ምን አልባትም ህልሙ በአካል በጥሩና በመጥፎ የተመሰሉ ነገሮች በመኝታ ወቅት በአጭሩ ሊነገራቸው ይችል ይሆናል፡፡ ወፏ የምትናገረው በሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ በአካልም በህልም መልዕክት መስጠት ትችላለች የሚል እምነት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘው የገለጹት ‹‹ከዘመዶቼ ጋር እማከራለሁ›› ይህንን ሀሳብ ስናይ ወላጅ ብቻውን ውሳኔ እንደማይሰጥ ዘመዶችም ሀሳቡ ተነግሯቸው በእነሱም በህልም ወይም አካላዊ ገድ ማየ ዘዴዎቻቸው እንዲያረጋግጡላቸው ለማድረግ ያሰቡ እና የዘመድ ተሳትፎም እንደሚታከልበት መረዳት እንችላለን፡፡

የልጅቷ አባት የሁለት ሳምንት ቀጠሮ የወሰዱት ምን ምን ሊያደርጉበት ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው መረጃ አቀባዮች ሲገልጹ፡- ልጆቻቸው የሚወስደውን ሰው ወይም የወደፊት የልጃቸውን የትዳር አጋር መሆን አለመሆኑን ገዱን አይተው ያጣራሉ፡፡ ባህሪውን፣ የሥራውን ሁኔታ፣ ጠንካራ ሠራተኛ ነው፤ አይደለም፣ የሚለውን ሰው ልከው እና በጎረቤታቸው አማካኝነት ያረጋግጣሉ፡፡ ሌላው የህልም ጉዳይ በዛ በሁለት ሳምንት ውስጥ የልጅቷ አባት ወይም የቅርብ ዘመዶች ህልም ይጠብቃሉ፡፡ የበቆሎ እሸት ያፈራ፣ ወይም ማንኛውም ሰብል አፍርቶ ካዩ ገዱ ጥሩ ነው ልጃችንን እንሰጣለን ይላሉ፡፡ ነገር ግን ልብስ አጥቦ ውጪ ተስጥቶ ካዩ ይህ ጋብቻ ጥሩ አይደለም፡፡ ልብስ ውጪ ማስጣት ከሞት ጋር ያያይዙታል፡፡ ልጃችን ልትሞት ስለምትችል ወላጅ ዘመዶች  አንሰጥም ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ሁለት ሳምንቱ የልጃቸውን ገድ የሚያዩበት ጊዜ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ከጋብቻ በፊት ወላጆች የሚያደርጉትን ከፍተኛ ጥንቃቄ ነው፡፡ በባህሉ መሠረት ገድ ካልፈቀደላቸው በስተቀር ልጃቸውን ለትዳር አይሰጡም፡፡ ገድ ጥሩም ሆነ መጥፎ ተብሎ የተወሰነው ህብረተሰቡ አምኖ በመጥፎና በጥሩ በፈረጃቸው ነገሮች ይመራበታል፡፡ ይተዳደርበታል፡፡ መጥፎ ብሎ የፈረጃቸው ነገሮች በጋብቻው መካከል እንዳይገባ ቅድመ ጋብቻ ትግል ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ለጋብቻ ስኬታማነት ምልክት ናቸው ብሎ ያስቀምጣቸው ነገሮች ብቻ ቆጥሮ ሲያገኝ ጋብቻው እንዲፈጸም ይፈቀድለታል፡፡ በአጠቃላይ በጋብቻው ሂደት የወላጆች ብቻ ሳይሆን የወላጅ ዘመዶችም ጣልቃ-ገብነታቸው ሰፊ ነው፡፡ ጋብቻ በህብረተሰቡ ዘንድ ከባድ አድርገው የሚያዩትና ጠለቅ አድርገው የሚያስቡበት መሆኑን ያሳያል፡፡

ሌላው ምንም እንኳን የልጁ አባት ወፏ ገዱ ጥሩ መሆኑን ነግራኛለች ብለው የጋብቻ ጥያቄ ይዘው ቢቀርቡም የልጅቷ አባት እንደገና ስለልጃቸው ወፏ የምትነግራቸውን ገደ ጥሩ ይሁን መጥፎ መስማት ማየትና ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ለዚህ ነው ሁለት ሳምንት እንዲሰጣቸው የጠየቁት፡፡ ሁለት ሳምንት በተለምዶው ገድ የማያ በቂ የጊዜ ገደብ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል ለጋብቻ ምርጫ የወላጆችና የወላጅ ዘመዶች ጣልቃ ገብነት ሰፊ እንደሆነ አይተናል፡፡እዚህም ላይ የምናስታውለው የወላጅና የወላጅ ቤተሰብ ጣልቃ ገብነት የትዳር አጋር የምትሆነውን በመፈለግ ላይ አያበቃም፡፡የልጅቷ ቤተሰብም የልጁ ቤተሰብም ገድ በማየቱ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

የልጅቷ አባት በሁለት ሳምንት ቆይታቸው የልጃቸውን ገድ አጣርተው ገዱ ጥሩ ከሆነ በቀጠሮ ቀን ወንበር ውጪ ግቢ ውስጥ ጥላ ሥር አስቀምጠው ይጠብቋቸዋል፡፡ ገዱ ጥሩ ካልሆነ ጥላ ሥር ወንበሩን አያስቀምጡም፡፡ የልጁ አባት ወንበር ውጪ ከሌለ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን አረጋግጦ ይመለሳል፡፡ ካለ ግን ይቀመጡበታል፡፡

### 4.2.1.3 ‹‹ሀሌቹ ኣስየ›› የጥላ ስጡኝ ሥነ-ሥርዓት

በከምባታ ቤረሰብ ጥላ ስጡን ‹‹ሀሌቹ ኣስዬ›› የራሱ የሆነ ባህላዊ አካሄድ እና ስነ-ስርዓት

አለዉ፡፡ በዚህ ጊዜ መልዕክት ወይም አስተያየት አመላላሽ በሁለቱም ቤተሰብ እዉቅና ያለዉ ሰዉ ይፈለጋል፡፡ ይህ የመሃል ሰዉ ጋብቻ ስነ-ስርዓት በተሳካ ሁኔታ እንዲያልቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የተለያዩ ግጭቶች እንዳይነሱ የምክር እና የጥንቃቄ ሥራዎችንም ይሰራል፡፡ በቀጣይ ሥነ-ሥርዓቶች ሁሉ አብሮ ይሆናል፡፡ ይህ ሰዉ የልጁ አባት ለልጅቷ አባት በዚህ ቀን ሽማግሌ ይመጣል ብሎ ይልካል፡፡ የልጁም አባት ከራሳቸው ጋር ሶስት ባህሉን የሚያዉቁና ተሰሚነት ያላቸዉን ሽማግሌዎች ይዞ ይሄዳል፡፡ የልጅቱም ቤተሰብ መጠነኛ መስተንግዶ በማዘጋጀትና ዉጭ በራፍ ላይ ጥላ ሥር መቀመጫ አዘጋጅተዉና የተወሰኑ የቤተሰብ ሰዎችን በመያዝ ይጠብቃል፡፡ ልክ ግቢዉን ሲገቡ የሚቀመጡበት ወንበር በጥላ ስር ካለ ጥላ ተሰጥቷል ማለት ነዉ፡፡ ተቃዉሞ ካለ ወንበር ወይም መቀመጫ ዉጭ አያስቀምጡም፡፡ የመጀመሪያዉን ግቢ እንደገቡ በረጅም ድምጽ ጤና ይስጥልን? ‹‹ጡማ ጡማ ጡማ ገልቴንታ›› ይላሉ፡፡ የመሃል ሰዉ ብቅ በማለት ጤና ይስጥልን? ‹‹ጡማ ዋልዬ›› ይምጡ ብሎ በጥላ ላይ ወደ ተቀመጠላቸዉ መቀመጫ ያመራል፡፡ ወፏ በህልምም ይሁን በእውን ልጃቸውን መስጠት እንዳለባቸው በጥሩ ገድ ከነገረቻቸው በኋል የልጁ አባት ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር ሄዶ በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ ይቀመጣል፡፡ ኮፍያና ዱላቸውን ካስቀመጡበት ከልጅቷ ቤተሰብ የመኃል ሰው ወስዶ ወደ ቤት ያስገባል፡፡ በዚህ ጊዜ እቤት እንዲገቡ እንደተፈቀድላቸው ይረዱና ወደ ቤት ይገባሉ፡፡የልጁ አባት ከአንድ ሽማግሌ ጋር ይቆሙና ፡-

| | |
|---|---|
| የልጁ አባት | አንገተ |
| | የከበረ ሠላምታ አቀርባለሁ |
| የመሀል ሰው | አንጋተ |
| | እኛም የከበረ ሠላምታ ሰጥተናል፡፡ |
| የልጁ አባት | ሀሌቹ አስዬኔ |
| | ጥላ ስጡን |

የመሀል ሰው ኡሩታ አሴንክዕኔ

ደጄን ሰጥቻችኋለሁ ይላሉ፡፡

ከምልልሱ የምንረዳው ከሰላምታው ስንጀምር ‹‹አንገት›› የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ፡፡ ይህ የሰላምታ አይነት ለሁሉም ሰው የሚሰጥ ሰላምታ አይደለም ለንጉስ ቤተሰብ በብሄረሰቡ ከፍተኛ ጎሳ ለተባሉ ሰዎች እና ከማህበረሰቡ ውስጥ የከበረ አስተሳሰብ በሳል ሀሳብ ያለው የሚወደድ ሰው ከሆነ ብቻ ይህ የሰላምታ አይነት ይቀርባል፡፡ ስለዚህ ሽማግሌዎቹ ለቤተሰቡ ያላቸውን አክብሮት ያቀረቡበት ሰላምታ ነው፡፡የቤቱም ሰዎች ሲመልሱ እኛም የከበረ ሰላምታ ሰጥተናል በማለት አክብሮታቸውን በአክብሮት መልሰዋል፡፡ ‹‹ሀሌቹ አስዬ›› ወይም ጥላ ስጡኝ የሚለው አረፍተ ነገር የያዘው ሀሳብ ለጠይቅኩህ የልጃችን መጋባት፣ መዋለድ ዝምድና መፍጠር ተዋልደን እንድንኖር ይገፔ የመጣሁትን ሀሳብ እንድንወያይበት ፍቃደኝነትህን ግለጽልኝ ለማለት ፈልጎ በቀጥታ ከመናገር ወይም ሀሳቡን በግላጭ ከመግለጽ ብለው የተጠቀሙት አረፍተ ነገር ነው፡፡ ምላሹም እንዲህ ‹‹ኡሩታ አሴንኬ›› ደጅ ሰጠሁክ ብሎ ሲመልስ የጠየቃችሁትን የጋብቻ ጥያቄ የእንዛመድ እንዋለድ እንቀላቀል ጥያቄ ጉዳይ ለመነጋገር ፍቃደኛ ነኝ ለማለት ፈልገው ነው፡፡

ደጅ መስጠትና መቀበል የሚለው ሀሳብ እንድምታው ለሰርጉ ለመወያየት ፍቃደኛነትን መጠየቅና መቀበልን ይያዝ እንጂ በሁለቱም ቤተሰብ ዘንድ ከዚህ በኋላ የሚነሳ የተቃውሞ ሀሳብ የሚኖር አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ከባዱና በጥንቃቄ ማየት የሚፈልጉት ደረጃ አልፈዋል፡፡ ጥሩ ልጅ የመምረጥና ገድ የማየት ስርዓቱ ላይ ልጃቸውን ለዚህ ቤተሰብ መስጠትና መቀበል እንዳለባቸው ለሁለቱም ቤተሰብ ወፏ በህልምም በእውንም ነግራቸዋለች፡፡ ስለዚህ የሁለቱም ቤተሰብ ፍቃደኛ መሆናቸውን ልባቸው ወስኖታል፡፡ በዚህ ቀን ቤተሰቡ ያዘጋጀውን ማንኛውንም መስተንግዶ ተጋብዘው ሲያበቁ‹‹ የሶፋ ዘለላ ዮሻ›› ለልጅቷ የቃል ኪዳን ምልክት በእጅና በአንገቷ ላይ የማድረግ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምበት ቀነ ቀጠሮ ተይዞ ይለያያሉ፡፡ የቀኑ ቀጠሮ የልጅቷ ቤተሰቦች በሚመቻቸው ቀን የጊዜ እርዝመት ይወሰናል፡፡

#### 4.2.1.4 ‹‹ሶፋ (ዘለላ)፣ ሰጋዩት› የቃል-ኪዳን ምልክት

ሶፋ (ዘለላ) ምንድነው? ሥርዓቱስ እንዴት ይካሄዳል?

አቶ አቦ ሄገና 05/08/2010 ዓ.ም ሲመልሱ ሶፋ(ስጋዩት) የቃልኪዳን ምልክት ነው፡፡ የሚዘጋጀው በተፈተለ ክር ሲሆን ክሩ የተለያየ ዓይነት ዶቃ ይታሰርበታል፡፡ አራት አምስት ስድስት ሰባት ስምንት ተንጠልጣይ ያለው በአንገት የሚጠለቅ ተደርጎ የሚሠራ ነው፡፡ የተንጠልጠዩ ቁጥር የሚወሰነው በባል ሀብት መጠን ነው ፡፡ ባለ አራት አምስት ዘለላ ከሆነ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያለው ነው ማለት ነው፡፡ ስድስትና ሰባት መካከለኛ ስምንት ዘለላ ሀብታም መሆኑን ማሳያ ነው ፡፡ ይህ ከተዘጋጀ በኋላ የልጅቷ እጮኛና ቤተሰቡ በልጅቷ ቤት በቀጠሮ ቀን እንዲገኙ ይደርጋል፡፡ የመጀመሪያው የሚደረገው ለሥርዓቱ የተጠመቀ ጠላ ወይም ሌላ መጠጥ ሊሆን ይችላል ሁለቱም አንድ ላይ እንዲቀመጡ ይደረግና የተጠመቀውን የጠላ እንስራ አጠገባቸው ያስቀምጡና ፊት ለፊታቸው መሬት ላይ ያፈሳሉ፡፡ ይህ ‹ሴሉ ጮቢሱ›ይባላል መጠጥ ማፍሰስ ማለት ነው ፡፡የሚያፈሰው ሰው‹‹ ሜጡ ኢኪዩ … ሜጡ ኢኪዩ›› እያለ ይመርቃቸዋል ምርቃቱ አንድ ሁኑ አንድ ያድርጋችሁ ማለት ነው፡፡

‹‹ሴሉ ጮጵሱ›› መጠጥ ማንጠባጠብ ቃለ ማህላ ማስፈጸሚያ አንዱ ክፍል ነው ፡፡ የማፍሰሱ መልዕክት ጋብቻዬን ባፈርስ እንደፈሰሰው መጠጥ ደሜን ያፍስሰው ሕይወቴ ማንነቴ እንደዚህ ፈሳሽ ያድርገው የሚል ቃል ኪዳን የያዘ ነው፡፡ ጠላውን የሚያፈሰው ሰው ይህንን ቃለ ማህላ አስፈጽሚል ማለት ነው፡፡ ተጋቢዎቹም መልክቱን ስለሚያውቁ በልባቸው እንጂ የሚያስቡት በቃላቸው የሚናገሩት ነገር የለም፡፡

ሁለተኛው ቃለማህላ ማስፈጸሚያው ሶፋውን በአንገት ላይ የማጥለቅ ስርዓት ነው፡፡ይህንን ስርዓት የሚፈጽመው አግቢው እራሱ ነው፡፡ ቤተ ዘመድ በተገኘበት በልጅቷ አንገት ውስጥ ያጠልቃል፡፡ በሚያጠልቅበት ሰዓት ሽማግሌዎች ‹‹ሜጡ ኢኬ ሜጡ ኢኬ›› እንድ ሁኑ እንድ ያድርጋችሁ ብለው ይመርቋቸዋል፡፡ይህ ምርቃት አንገት ላይ እጅ ላይ ያደረግሽው የመተጫጨት ምልክት ቢሆንም ከጌጥነት ባሻገር

ለእንድነታችሁ ምክንያት ይሁን አይነት መልዕክት የያዘ ነው፡፡

ሶስተኛው ቃለ ማህላ ማስፈጸሚያ አንድ ጥቁር በግ ያርዱና የበጉን ደም አምጥተው በግምባራቸው ላይ ይቀባሉ፡፡ ይህንን የሚቀባው ሰው ‹‹ኪቲም ሻሙ ኪቲም ሻሙ›› ይላል፡፡ ይህ የመሰዋት ደም ላለመለያየታችሁ ምክንያት ይሁን፡፡ አንድ ያደረጋችሁ፡፡ ትዳራችሁን ያጽና፡፡ ምንም ነገር አይለያችሁ ማለት ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን ሥርዓት ስንመለከት ሦስት ዓይነት የተግባር ማሳሪያ ምልክት ሲያደርጉላቸው እናያለን፡፡ በእነዚህ ሥርዓት ውስጥ እጩ ተጋቢዎች አንድም የሚገቡት ቃል-ኪዳን የለም ነገር ግን በሁሉም ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው አንድ ዓረፍተ ነገር ነው ሲናገር የምናየው እሱም አንድ ሁኑ ‹‹ሜጡ ኢኬ›› ሶፋ በአንገት ላይ የማጥለቅ ሥርዓቱም ደም በግምባራቸው የመቀባት ሥርዓትም ተመሳሳይ መልዕክት የያዘ ነው፡፡የጥቁር በግ ማረድ ለከምባታ አንድ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡የበጉ ጥቁር ቀለም መመረጡ ለአንድ ሰው ትልቅ ሀላፊነት ማሸከም ወይም መስጠት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡የሚፈሰው ቀይ ደም ደግሞ ቃለ-መኻላ ማስፈጸሚያ ወይም ቃል-ማስገቢያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ የጥቁር በግ ወይም በሬ አንድን ሰው አንድን ነገር በሚስጥር እንዲይዝ ከተፈለገ ይህንን ጥቁር በግ ወይም በሬ በቁሙ በጥርሳቸው እኩል ይነክሳሉ፡፡ይህንን ተግባር የፈጸሙ ሰዎች በሚስጥር እንያዝ የተባባሉትን ነገር በምንም ታዓምር እስኪሞቱ ያንን እንዳይነገር የተባለውን ሚስጥር ለማንም አይናገሩም፡፡

ይህም ‹‹ገምበላ ገዕሜ፡፡›› ጥቁር ነክሷል ይባላል፡፡ በጋብቻ ቃል ማስገቢያ ተደርጎ ደሙን በግምባራቸው ላይ ቀብተው አንድ ያድርጋችሁ የሚሉት በዚህ ደም የታሠረ ማንኛውም ትዳር አይፈርስም የሚል እምነት አላቸው፡፡ እስከ አሁን ድረስም በከምባታ ዘንድ ጋብቻ ተቻችሎ መኖር ባህልነቱን ቀጥሏል፡፡

ከላይ የቃል ኪዳን አሰጣጥ ስርዓቱን ስናይ ሶስቱም አይነት ስርዓት የቋንቋ ውክልና ያላቸው ትምዕርታዊ መልዕክቶች ናቸው፡፡ በአንገት የሚጠልቀው የቃል ኪዳን ምልክት የተንጠልጣዩ ቁጥር የአገቢውን የሀብት መጠን ይገልጻል፡፡ይህንን የአንገት ጌጥ እጩ

አግቢው በሚያጠልቅበት ጊዜ ሙሽራዋም እድምተኛውም ያለውን የሀብት መጠን ይረዱታል፡፡ እዚህ ጋር የምንረዳው የእጩ አግቢው የሀብት መጠን በሚንጠለጠለው ተንጠልጣይ መጠን ተወክሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህንን መረዳት የሚያቅተው ምን አልባት ባህሉን የማያውቅ እድምተኛ ካለ ብቻ ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሁሉ ግን የትምዕርቱን መልዕክት ይረዳዋል፡፡

ሁለተኛው ግልጽነትን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ዘመን የሚታየው አንዲትን ልጅ ለማግባት ያለውንና የሌለውን የሀብት መጠን እየጠራ ልጅቷ እቤት ከመጣች በኋላ የተነገራትና የተሰበከችው የሀብት መጠን የተለያየ ይሆናል፡፡ ይህ ግን ያለውን የሀብት መጠን ቁልጭ አድርጎ ባህሉ በሚፈቅድለት የመንገሪያ መንገድ ተናግሯል፡፡

ሶስተኛው የምንረዳው ነጥብ ማህበራዊ ደረጃውን ነው፡፡ ሀብታምና ድሀ ወይም ሀብት ያለውና የሌለው በጋብቻው የቃልኪዳን ስርዓት ላይ በተንጠልጣይ መጠን እንዲለይ ተደርጓል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቃልኪዳን ማስገቢያ ‹‹ሴሉ ጮቢሱ›› መጠጥ የማፍሰስ ስርዓት ነው፡፡ይህ ስርዓት ከህይወት ጋር አያይዘው የሚያስገቧቸው መህላ ይመስላል፡፡ ምክኒያቱም መጠጡን በፊታቸው የሚያፈሰው ሰው አንድ ሁኑ ይህ የፈሰሰው መጠጥ ላለመለያየታችሁ ምክኒያት ይሁን የዚህን መልክት ሲገልጹ አንተን ወይም አንቺን ብከዳሽ እንደዚህ ፈሳሽ ደሜ ይፍሰስ ሲሉ ካንተ ወይም ካንቺ ለመለየት ካሰብኩ ቀጥሎ ሌላ የምኖረው ሕይወት አይኖረኝም፣ መሞት ነው የሚገባኝ፣ ብለው ሕይወታቸውን አስይዘው ቃል የሚገቡት ስርዓት ነው፡፡መራቂውም ለዚህ ይሆናል ከመሞት መኖር ይሻላቹሃልና ይህ የሚፈሰው መጠጥ ላለመለያየታችሁ ሀይልና አቅም ይስጣችሁ፣ ያላቸው፡፡

ሶስተኛው የቃልኪዳን ማስገቢያ ጥቁር በግ አርደው በሁለቱም ተጋቢዎች ግንባር ላይ መቀባት ነው፡፡የበጉ መልክ ጥቁር እንዲሆን የተፈለገው ለምንድ ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ወደ ትዳር መግባት ከባድ ሀላፊነት መሸከም ነው፡፡ልጁ የመውለድ፣ የማሳደግ፣ በባህሪ ተቻችሎ የመኖር፣ የተለያዩ ማህበራዊ ተግባራትን መፈጸም ወዘተ ይህንን ሀላፊነት ሁለት ተጋቢዎች አውቀው መግባት አለባቸው፡፡ ይህንን ለማሳየት ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ

ሀሳብ የምንረዳው የጋብቻ አለምን በትልቅ ሀላፊነት ስሜት መጀመር እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው፡፡ጋብቻ ትልቅ ክብርና ክብደት የሚሰጠው ነው፡፡ሳይታሰብበት ዘው ተብሎ የሚገባበት አይደለም የሚል አንደም አለው፡፡

ሌላ መረጃ አቀባዮች ያነሱት ሀሳብ ጥቁር ነገር ለከምባታ ለጋብቻ ቃል ማስገቢያ ብቻ አይደለም፡፡ አንድን ነገር በሚስጥር ለመያዝ የፈለጉ ሰዎች በጥቁር ነገር ይማማላሉ፡፡ በጥቁር ነገር የተማማለ ማንኛውም ሰው እስኪሞት ድረስ ሚስጥሩ ሚስጥርነቱ እስኪያበቃ ወይም ሰዎቹ አሰኪሞቱ ድረስ ያንን ሚስጥር አይናገሩም ብለዋል፡፡ ይህንን ሀሳብ ከጋብቻ ቃል መገባባት ጋር ስናገናኘው ከጋብቻው ሞት እስኪለየን ድረስ አንለያይም የሚል መልዕክት ያዘለ ነው፡፡

የቃል ኪዳን ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ቤተሰብ ያዘጋጀው ግብዣ አብልቶ እጅ የመሳም ‹‹አንግ ሱንቃ›› ቀን ይያዝና በዕለቱ ፕሮግራም ያልቃል፡፡ይዘዉ የሚመጡትን ስጦታ ወይም ጥሎሽ ከተነገረ በኋላ ይለያያሉ፡፡

### 4.2.1.5. ‹‹ቆታ አንግ ሱንቃ›› ጥሎሽ

‹‹አንግ ሱንቃ›› እጅ መሳም ማለት ነው፡፡ይህ ሥርዓት የልጁ አባት የልጅቷን ቤተሰብ ጉልበታቸውን በሥጦታ የሚስሙበት ሥርዓት ነው፡፡ የዚህን ሥርዓት ሂደት አቶ አቦ ሄገና 08/08/2010 ዓ.ም ሲገልጹ

> ይህ ቀን የማር ቀን ‹‹መለብ በርሃ›› ተብሎ ይታወቃል፡፡ ማር በባህሉ ከፍኛ ቦታ የሚሰጠዉ ነዉ፡፡ ማሩን ይዘዉ በተወሰነላቸዉ ቀን ከሽማግሌዎቹ ጋር ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ቀን የአባትና የእናት እጅም ስለሚሳም ለምለም ሣር ‹‹ሀሩፈ›› የተባዉን ልዩ ሣር ይይዛሉ፡፡ ማር የያዘዉ ሚዜ ወይም ሌላ የተሸከመዉ ወጣት ልክ ሽማግሌዎቹ እንዲገቡ ፈጠን ብሎ በምሶሶ አጠገብ የታሰረበትን የእንስራዉን አፍ ከፍቶ ያስቀምጣል፡፡
>
> ማሩን ስጦታዉን እንድናቀርብ ይፈቀድልን ብለዉ የልጁ አባት ከአንድ ሽማግሌ ጋር

ጋቢ አደግድገዉ ይቆማሉ፡፡ ሲፈቀድላቸዉም ከወላጆቹ ፊት ለፊት በተዘጋጀዉ መሶብ ላይ የገንዘብ ስጦታውን ያስቀምጣሉ፡፡ የማሩም ሆነ ለልጁቷ አባት የሚሰጠው የገንዘብ ስጦታ መጠን እንደ አግቢው የሀብት መጠን ይወሰናል፡፡ ሀብታም ከሆነ እስከ አስር ሺ ደሀ ከሆነ እስከ አምስት መቶ ብር በተዘጋጀው ቦታ ላይ ያስቀምጣል ፡፡ የመሃል ሰዉ የቀረበዉን ስጦታ ቆጥሮና በዓይነት ከሆነም በመለየት ለተቀመጡት ሽማግዎች ይናገራል፡፡ የልጅቱም አባት ምንም ዓይነት ምላሽ አይሰጥም፡፡ ሌላ ሽማግሌዎች ከተቀመጡት ጋር በመመካከር ይበቃናል ካልሆነም ያንሳል የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ ያንሳል የተባለ ከሆነ እሺ ያላችሁትን ሁሉ እናሟላለን ይላሉ፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ የማር ስጦታ ትርጉም ዝምድናችን ጣፋጭ ይሁን ትዳራቸዉ እንደ ማር ይጣፈጥ ማለት ነው ፡፡ማሩ በምሶሶ ስር የሚቀመጠው በከምባታ ባህል ምሶሶ የአባት የክብር ቦታ ነው ፡፡ማሩም የከበረ መሆኑን ለማሳወቅ ምሶሶ ስር ይቀመጣል፡፡ሲሉ ሌሎች መረጃ አቀባዮች የማሩና የምሶሶውን ውክልና ይናገራሉ ፡፡

እዚህ ላይ የምንገነዘበው ስጦታዎች ያላቸውን ተምሳሌትነትና ውክልና ሲሆን የስጦታው መጠን ደሀና ሀብታምን የሚለይ ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳይ ነው፡፡

በመጨረሻ የምርቃት ስርኣት ይካሄዳል፡፡ ምርቃቱን እንዲመርቁ ለልጁ አባት ወይም አያት ወይም ለቅርብ ዘመድ ይሰጣል፡፡አቶ ስምኦን አያኖ ሲመርቁ (ምልከታ ሚያዝያ 1/2010) ፡፡

**‹‹ማሳት›› ምርቃት**

| **የመገኛ ቋንቋ** | **የአማርኛ አቻ ፍቺ** |
|---|---|
| ባዱኔ ጡማ ኢሁ | ሐገራችን ሠላም ይሁን |
| አያኑሴ መኩን | የልጅቷ ገድ ለእኛ የተመቸ ይሁን |
| አያኑሴ ኢለሚ መኩ | ገዱ ለዘመዶች ይመች |
| አያኑሴ ሆሪንካ መኩ - | ገዱ ለሁሉም ይመች |

| | |
|---|---|
| አደቤ አያኑሁ ኔሳ መኩ | የልጄ ገድም ለእኛ የተመቸ ይሁን |
| ኢ.ተት ደደንቱን | የሁለቱም ቤተሰብ ፍቅር የተገመደ ይሁን |
| ለሙንኩስ ማሳአንቱን | ሁለቱም ይባረኩ |
| ላሙንኩሳ ኢ.ለሙ አቢ.ሱን | ሁለቱም ዘመድ ያክብሩ |
| ኢ.ልቱን ሥርቱን - | ይውለዱ ይክበዱ( ይብዙ) |
| ሆለመራ ኤቤ መገኑ ማሳኡሳ | ብዙ ነገር አምጠተዋል እግዚአብሄር ይባርካቸው |
| ኢ.ለሚ.ን ደቀሚ. ዋልቴሀሃ | ዛሬ ከእኛ ጋር ለመገናኘት መጥተዋል ይህ |
| | ግንኙነት ለዘላለም ይደግ፣ይቀጥዶሊ.ሆሪኢ.ሁን |
| አኒ.ሀ አማሃ አያኑ ኦሶ መኩ | የእናትና የአባት ገድ ለእናንተ የተመቸ ይሁን |
| ቲ ኢ.ለንሰት ጎንድ ጎጌሳ ኢ.ሁን | ይህ ዝምድና እንደ ጉንዳን ክምር ይብዛ |
| ቲ ኢ.ለንሰት ሀንቀጸንቴኢ.ተ እኩን | ዝምድናችን ይሁን የተሳሰረ ይሁን |
| ኤሳች ፈኦ መገኑ ዊንሹ | ከእኔ የቀረውን ምርቃት እግ/ር ይሙላው |

የምርቀቱን ሀሰብ ስንመለከት የአንድ ሰው ገድ ጥሩ መሆን ለሁሉም ነገር መሰረት አድርጎ ማየት አለ፡፡ ይህ የምያሰየው የሁለቱም ተጋቢ.ዎች ገድ ጥሩ እንዲሆንላቸው መመኘት ብቻ ሳይሆን የወላጆች የራሳቸውም ገድ ለልጆቹ የተመቸ እንዲሆን የተሳካ የተስተካከለ የዘመድ ግንኙነትና ትስስር እንዲኖር ይህ ከሆነ ደግሞ ፍቅር፣ መተሳሰብ እንደሚ.ኖር እምነታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡ ‹‹ቲ ኢ.ለንሰት ወደሪገ ደደንቲር ኢ.ሁን›› ይህ ዝምድና እንደ ገመድ የተገመደ ይሁን የሚ.ለው ምርቃት በሁለቱ ዘመዶች መካከል እንዲፈጠር የሚ.ፈልጉት ፈጽሞ የማይለያይ፣ በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ልብ ተሳስቦ ተዋህዶ እንዲኖር መፈለጋቸውንና መመኘታቸውን የሚ.ገልጽ ነው፡፡

‹‹ቲ ኢለንሰት ሀንቀጳንቴኢተ ኢኩን›› ይህ ዝምድና የተሳሰረ ይሁን ይህም ምርቃት የላይኛውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ በፍቅር በየትኛውም ጉዳይ ልዩነት ሳይፈጠር ተከባብሮ ተረዳድቶ እንደ አንድ ሰውና እንደ አንድ ቤተሰብ ተግባብቶ የመኖር ፍላጎትና ምኞታቸውን ገልጻዋል፡፡

ሌላው ሁሌም በምርቃት ሰዓት የማይታጣው ሀሳብ ‹‹ኢልቱን ስርቱን›› - ይውለዱ ይብዙ የሚለው ምርቃት ሲሆን ልጅ ለመውለድ ያላቸውን ትልቅ ግምትና ፍላጎት የሚያሳይ ነው፡፡ ጋብቻ ለከምባታ ዘር መጨመር ነው የሚለውን ከመነሻ የተነሳውን እሳቤ ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ሀሳብ ነው፡፡ በመጨረሻ -ኢሳች ፋኦ መገኑ ዊንሹን - ከእኔ የቀረውን ምርቃት እግዚአብሄር ይሙላው፡፡ እኔ መመረቅ የሚገባኝ ለእናንተ፣ ለዘመድ ሁሉ አስፈላጊ የሆነ ነገር በእኔ አዕምሮ ያልመጣ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያደርግላቹን ነገር እሱ መርቆ ይፈጽምላችሁ ብለው የእሳቸው ምርቃት ሙሉ መስሎ ስላልተሰማቸው መራቂው የምርቃቱን ሂደት ዝግ ላለማድረግ ሲፈልጉ ክፍቱን ቦታ አምላክ እሱ ይሙላው፡፡ ብለው ለእግዚአብሔር ሲሰጡ ይታያሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ዋናዉ የሠርግ ዝግጅት እየደረሠ በመሆኑ የሠርግ መወሰኛ ቀን እንዲያዝ በመሃል ሰዉ የእናትና የአባትን በባህሉ መሠረት ወጋቸዉን እንጨርሳለን ብሎ ቀነ-ቀጠሮ እንዲያዝ ይላካል፡፡ በተያዘዉም ቀን ለአባት ትልቅ ቡሉኮ (ኦኮና) ለእና መቀነት (ጠጠባ) እና ጥብቆ፣ የልጅቷ ሙሉ ልብስ፣ የልጅቷን ገንዘብ፣ ለአገቶቿ ገንዘብ፣ ለአያቶቿ ለእናቷ እናት ቀሚስ፣ ነጠላ፣ ለአናቷ አባት ጋቢ፣ ለአባትዋ አባትና እናት በተመሳሳይ ቀሚስና ጋቢ፣ ለልጅቿ ወንድም ገንዘብ ፣ለልጅቷ እህት ገንዘብ ይሰጣል፡፡ እነዚህን ስጦዎች እጃቸዉን እየሳሙ በተቀመጡበት በታፋቸዉ ወይም እጃቸዉን በዘረጉበት ያስቀምጣል፡፡ ከስጦታው በኋላ የምርቃት ስነ ስርዓት ይካሄዳል፡፡

| መገኛ ቋንቋ | አማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ዘኩሴ በጅጉ | መጨረሽዋ ደስታ ይሁን |
| ዘግሽግ ዘርፋሚተ ኢህ | እንደ ዝግባ ቅርንጫፍ ሁኚ |
| ኦዴቾገ ጠጳምተ ኢህ | እንደ ሾላ ስር ስደጂ |

ሰሜ ቤዜገ በተኢ.                    እንደ ሰማይ ኮከብ ብዢ

መገኑ ማሰኡሂ                    ፈጣሪ ይባርክሽ

ይህ ምርቃት አንድን መልካም ሀሳብ አጠናክሮ በአነጻጻሪ ዘይቤ የተገልጸ ነው፡፡ ‹‹ዘኩሴ በጅጉ›› መጨረሻዋ ደስታ ይሁን፡፡ የሚለው ሀሳብ ማግኘትና ማጣት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚፈራረቅ ነው፡፡ አግኝቶ ከሚያጣ ሰው አጥቶ የሚያገኝ ካገኘ በኋላ እስከ መጨረሻው ማግኘቱ የሚጸናለት ሰው ሁኚ እኛ ዛሬ ባንቺ ምክኒያት ተደስተናል፡፡ይህ ደስታ ባንቺ ሕይወት እስከ መጨረሻ ይሁን ለማለት ነው፡፡

‹‹ዘጊሺግ ዘርፋሚት ኢሀ›› እንደ ዝግባ ቅርንጫፍ ተትረፍረፊ ያንቺ ዘሮች እርስ በእርስ እየተዋለደ እጅግ በጣም ይብዛ አንቺ እንደ ግንድ ሆነሽ ለሚበዙ ለሚዋለዱ ልጆች መነሻ ያድርግሽ፡፡የልጅ ልጆችሽን እያየሽ ረዥም አመት ኑሪ ቶሎ አትሙቺ አትጥፊ ነው፡፡

‹‹ኦዴቺግ ጠባሚት ኢሀ›› እንደ ሾላ ስር ስደጂ ከገባሽበት ቤተሰብ ፈጽሞ የሚነካሽ የሚነቀንቅሽ ነገር አይኑር፡፡ በዘመዶችሽ ልብ ዘልቀሽ ጊቢ ዘልቀሽ እንድትገቢ የሚያደርገሽን ባህሪና ማንነት ይስጥሽ፡፡ለማለት ፈልገው ነው፡፡

‹‹ሰሜ ቤዘግ በተይ›› እንደ ሰማይ ኮዋክብት ብዢ ይህ አረፍተ ነገር የላይኛውን ሀሳብ የሚደግፍ ነው፡፡ዘሮችሽ ከቁጥር በላይ ይሁን ማንም ሊቆጥር የሚሳነው ያህል ዘር ይኑርሽ ዘሯ እንዲበዛ በመመኘት የቀረበ ምርቃት ነው፡፡በመጨረሻ የፈጣሪ ባርኮት ለዚህ ሁሉ ነገር መፈጸም የእሱ እጅ ይጨመርበት፡፡

ይህንን ሀሳብ ሲጠቃለል የትዳር ሕይወታቸው በደስታ የተሞላ መልካም መልካም ነገር የሚያጋጥመው እንዲሆን ሁለተኛውና በከምባታ ብሄረሰብ ትኩረት የሚሰጠው የመብዛትና የመዋለድ ጉዳይ ነው፡፡በብዙ እጥፍ ዘሮቻችንን አትረፍርፊልን ለማለት ነው፡፡ሌላው የባህሪና የጥሩ ሰው የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ሚስት የባል ዘመዶቿን እንድታከብር ይፈልጋል፡፡ፈጽማ በመፍራትና በመታዘዝ ባህሉ የሚጠይቃትን አክብራ እንድትኖር የመፈለግ መልዕክት ነው፡፡በመጨረሻ የፈጣሪ ባርኮት በመመኘት ምርቃታቸውን ጨርሰዋል፡፡

ምርቃቱ እንዳለቀ ቤተሰብ ያዘጋጀውን ግብዣ ካስተናገዱ በኋላ የሠርግ ቀን ሁለቱም ቤተሰብ በመመካከር ይወስናሉ፡፡ ለጥር ሚካኤል ወይም ገብርኤል ካሆነም ሌላዉን ታቦት ጠርተዉ በቀጣዩ እሁድ ወይም ማክሰኞ በማለት ይይዛሉ፡፡

ለሠርጓ ሁለት ሳምንት ሲቀረው በአግቢው በር የሚጫወቱት ጫወታ አለ ፡፡ይህንን ጫወታ የሚጫወቱት ወንዶች ለብቻ ሴቶች ለብቻ በረድፍ ቶመው ነው፡፡ ጫዋታውን እየተቀባበሉ ወንዶች ለሚሉት ሴቶች መልስ እየሰጡ ይጫወታሉ፡፡ ከግጥሞቹ መካካል ፡-

| የመገኛ ቋንቋ | የአማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ዋልቤ ዋልቤ አማዬ ዋልቤ | ነይ ነይ እናቴ |
| ደናሜ ዋልቤ ዋልቤ | ቆንጆዬ ነይ ነይ |
| ጬቁሉሰ አጉዳንቲት ዋልቤ | አንቂ ጌጥ የምትመስዪ ነይ ነይ |
| ጪአ ወማ አጉዳንቲት ዋልቤ ዋልቤ | የወፍ ንጉስ የምትመስዪ ነይ ነይ |
| ኦዶሞርቹ አጉዳዋቲት ዋልቤ ዋልቤ | ደስ የሚል ወፍ የምትመስዪ ነይ ነይ |
| ዚሽ ወማ አጉዳንቲት ዋልቤ ዋልቤ | የንብ ንግስት የምትመስዪ ነይ ነይ |
| ሰጄ ከምባት ቤቱት ዋልቤ ዋልቤ | ንጹህ የከምባታ ልጅ ነይ ነይ |
| ወጋሚት ዋልቤ ዋልቤ | ወግ የምታውቂ ነይ ነይ |
| ኢሊተሱማት ዋልቤ ዋልቤ | ዓይነኩሏ ነይ ነይ |

ከላይ የቀረቡትን የዘፈን ስንኞች ስንመለከት የየራሳቸው እምቅ ሀሳብ የያዙ ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ስንኝ ነይ ነይ እናቴ ሲል ነገ እናቱን የምትተካ ከጋብቻ በኋላ የምትንከባከቢኝ ብታመም ቢከፋኝ ቢደላኝ በደስታም በሀዘንም አጠገቤ የምትሆኚው ከዚህ

በኋላ አንቺ ነሽ እናቴ በማለት ከእሷ ጋር ለመኖር ያለውን ፍላጎት በመግለጽ እንድትመጣለት በመጓጓት ስሜት ነይ ነይ ይላታል፡፡ቆንጅዬ ነይ ነይ ፣ እንቁ ጌጥ ነይ ነይ የሚሉ ሁለት ስንኞች ቁንጅናዋን ፣ ውበቷን የምታምር መሆንዋን መልኳን የሚያሞግሱና እንቁ ጌጥ… ሲል ውበቴ ደም ግባቴ ካንቺ ጋር ከሆንኩ አምራለሁ የሚል መልዕክት የያዙ ስንኞች ናቸው፡፡ የወፍ ንጉስ የምትመሲዪ ሲል ግርማ ሞገስ ያለሽ፣ አይን የምትስቢ መልክና ቁመና አሟልቶ የሰጠሽ የሴቶች ሁሉ የበላይ የምታኮሪ ነሽ ስለዚህ ነይልኝ እያላት ነው፡፡

‹‹ንጽሁ የከምባታ ልጅ ነይ ነይ›› ይህ ስንኝ ከሚወደድ፣ ከሚፈለግ፣ከንጉስ ጎሳ የተወለድሽ በከምባታ ውስጥ ሆኖ የሚናቅ ጎሳዎች ውስጥ ያልተፈጠርሽ በረዥም ዘር ቆጠራ እንኳን የሚነካካሽ መጥፎ ዘር የሌለሽ የሚል ይዘት ያለው ሀሳብ ነው፡፡ ወግ  የምታውቂ …. ሲል አለባበስሽ ፣ ባህሪሽ ፣ አነጋገርሽ ፣ አኗኗርሽ ሁሉ የከምባታን ባህልና ወግ የጠበቀ ነው፡፡ የከምባታ ባህል ጠንቅቀሽ አውቀሽ በወጉ የኖርሽ ነሽ እና አንቺ ለእኔ ትመቺኛለሽና ነይ ነይ ‹‹ አይነ-ኩሏ … ››አይንሽ ያምራል ኩል ተኩሎ ወበት እንዳለው አይነት አይን ያለሽ ነሽ በማለት የአይኗን ውበት በተፈጥሮ የሚያምር መሆኑን እያደነቀ የምትመጣበትን ቀን ይናፍቃል፡፡ የግጥሙን ሀሳብ ጠቅላላ ይዘት ስንመለከት የልጅቷን የመልኳን ውበት ፣ ግርማ ሞገስ ፣ የከበረ ጎሳ ልጅ መሆኗን የከምባታን ባህልና ወግ ጠንቅቃ የምታውቅ መሆንዋን የሚያስረዱ ስንኞች ናቸው ፡፡ በዚህ ውስጥ መገንዘብ የምንችለው አንድ ወንድ ለማግባት የአካባቢውን ባህል መላበስ የጎሳ ምርጫና ውበት መመዘኛዎች እንደሆኑ እንገነዘባለ፡፡

**ወንዶችና ሴቶች እየተቀባበሉ የሚጫወቱት የሠርግ ጨዋታ**

**የጫዋታው ስም‹‹ አበሞ›› ይባላል**

| **ጎኑ** | **መሰላከት** |
|---|---|
| ሂሎ ለሙ ለመላ ሶኬቤ | ሂሎ ለሙ ለመላክ አጵት መር |
| ለመቀ ኦኮና ሶኬቤ | ለመቀ ኦኮናክ አጵት መር |

| | |
|---|---|
| ቦዮ ሱሉሙተ ሶኬቤ | ቦዮ ሱሉሙክ  አጽት መር |
| ሶፋ ዮሻ ሶኬቤ | ሶፋ ዩሻክ አጽት  መር |
| ቦክሴ ቡጥመት ፎልቴቤ | ቦኮንተኔ ቡጥመት ዮበቤ |
| አባ ሂለሞ አፍ ዋልታረ ጡንዳምቤ | ቦኮንተኔ ቡጢመት  ዩበቤ |
| ገረሴ ዌሴች ከማንሴ | ፊሶ ፊሶ ምነኖ |
| ጌዩሴ ሚኒች ከማንሴ | ፊሴሬካ መጠኖ |
| ጎተራ ሂቻች ፉሽናንሴ | ገሲ,ሙንኩስ ሀዋንቾ |
| ሶናንሴ | ገሎ ቲሚ ያረኖ |

## የአማርኛ አቻ ፍቺ

| ወንዶች | ሴቶች |
|---|---|
| ጥሎሽ ሰባት እጥፍ ልኮላታል | ሰባት እጥፍ ስጦታህን ይዘህ ሂድ |
| ደርብ ቡሉኮ ልኮላታል | ድርብ ቡሉኮህን ይዘህ ሂድ |
| ወይፈንና ጊደር ልኮላታል | ወይፈን ጊደርህን ይዘህ ሂድ |
| የአንገትና የእጅ ጌጥ ልኮላታል | የአንገትና የእጅ ጌጥህን ይዘህ ሂድ |
| የዘመዶቿን ድህነት ተወጥታለች | በቤተሰቧ ድህነት የለም |
| ይዛ የምትመጣውን ነገር እናያለን | በቤተሰቧ ድህነት የለም |
| ለጋ እንሰት ከመፋቅ እናወጣታለን | ቤትህ ትንሽ እና ጠባብ ነው |

ከትንቧ ጎጆ ኑሮ እንገላግላታለን

ከጎተራ ቤት ኑሮ እናወጣታለን

እንቀልባታለን

ጥሩ ጎመን እንኳን በጓሮህ የሌለህ

ከልጅነትህ ጀምሮ ጎስቋላ

ላደረ ቆጮ እንኳን የምታለቅስ

ከላይ የቀረበውን የስንኝ አገላለጽ ስናይ የወንዶቹ ሀሳብ አግቢውን ከፍ ከፍ አድርጎ የልጅቷንና የቤተሰቧን ድህነት የገለጸ ይመስላል፡፡ ‹‹ጥሎሽ ሰባት እጥፍ ልኮላታል›› ለቤተሰቦቿ የተላከው እያንዳንዱ ስጦታ በባህሉ ሊላክ ከሚገባው ብዙ እጥፍ መሆኑን እየገለጹ በስም ዝርዝር ያነሳሉ፡፡ የተላኩትም ነገሮች በጥራትም በብዛትም የተሻለ ነው ፡፡ ድርብ ቡሉኮ፣ ወይፈን፣ ጊደር፣ ጌጣጌጥ በጥሎሽ ጊዜ የተሰጠው ገንዘብ ቤተሰቦችሽን ከድህነት ሊያወጣ የሚችል ያህል ነው፡፡ ይህ ሀሳብ አግቢውን ለማሞገስ ፣ ብቁ መሆኑን ፣ ሀብታም መሆኑን በሌላ በኩል ልጅቷንና ቤተሰቦቿን ምንም የሌላቸው ከደህነት እያወጣቸው እንዳለ ወደፊትም እንደሚያወጣቸው ለማስረዳት ነው፡፡ ሴቶቹ የወንዶቹን አጸፋ የመለሱ ይመስላል፡፡ የሰጠውን ስጦታ እየዘረዘሩ ይዘህ ሂድ አንተ እንደምትለው በእኛ ቤተሰብ ድህነት የለም እንደውም ያንተን ድህነት እንንገርህ ቤትህ ትንሽና ጠባብ ነው፡፡ በጓሮህ የሚበላ የተተከለ ነገር እንኳን የለም፡፡ የሚበላ ነገር እንኳን ያላመቻቸህ ሰነፍ ነህ፡፡ ጓሮህ ባዶ ነው፡፡ እንዲያውም ከስር መሰረትህ ዘርህም ጎሳህም ከመነሻ በታሪክ የሚታወቀው በድህነትና በችግር ነው፡፡ ተጠፍጥፎ ላደረ ቆጮ እንኳን እንዳይነኩብህ የምትሰስት መስጠት የማትወድ ነህ፣ እናውቅሃለን፣ እያሉ ለተነሳባቸው ወቀሳ የሚሆን ምላሽ ሲሰጡ እናያለን፡፡

ከላይ የተገለጸው ሀሳብ ሁለት አላማ ያለው ይመስላል፡፡ አንደኛው የሚያዳምጣቸውን የታዳሚያቸውን ጆሮ ለመሳብ በግጥሙ ውስጥ የሁለቱንም ተጋቢዎች ማንነት አድማጩ እያሰበ ዳኝነት መስጠት እንዲችል ለማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው በቅኔ አደራደራቸው ሰው እንዲዝናና፣ እንዲስቅ፣ ደስ እንዲሰኝ ከአሁን አሁን ምን ይላሉ እያለ አድማጭ ካጠገባቸው እንዳይርቅ በጉጉት እንዲሰማቸው ለማድረግ ሲሉ ነው፡፡

በዚህ ውስጥ የማህበረሰቡን የቋንቋ አገላለጽ ማየት ይቻላል፡፡ ይኸዉም በማንቋሸሽ ውስጥ

ማሞካሸትን፣ በጥላቻ ውስጥ መውደድን፣ በስድብ ውስጥ ሙገሳን፣ በድህነት ውስጥ ሀብትን፣ በመጥፎ ቃል ጥሩ ነገርን የመግለጽ ችሎታን መረዳት ይቻላል፡፡

**ጎኑ**

ጉልቤን ሸዕላ ሆጋታቤ
ጉልባን ጉልቢሴ ጦፊፌታ
ሱሉሙት ጡርሲንሰን ቡሪን አንሽናንሴ
ሂልንሳንሴ ዋልቱን ዋልቱኒ
ግዳኒገ ባንዳሜ
ግድግድገ ሸዕላሜ
ጊራ ቆጢገ ጥታሜ
ቂንጣ ቆሪጤ በደሜ
ሎበተ ሎሎሴ በደሜ
ሸንኮ አዜን ሸዊ ፊጅያን
ሀሰን ሆሳንት ኢ በደሜ
ዱብ አዜን ዱብ ፊጂያን
ሀሰን ሆሳንት ኢ በደሜ

**ሜሴላካት**

ቡላ ቡሪን ሌኤታቤ
ቡታካ ቆጭቆን ሌኤታቤ
አደቤ መዕላላ ሮሳበቤ
አመኔ ቤቱት

**የአማርኛ አቻ ፍቺ**

**ወንዶች**

በጉልበቷ እበት የምትዝቅ ናት
ከባድ ስራ ጉልበቷን የጨረሳት ናት

**ሴቶች**

ቡላ በቅቤ በልታ ያደገች ነች
የበግ የጠቦቶችን ስጋ በልታ ያደገች ናት

ጊደር እንድታልብ እናደርጋታለን

ትምጣ በቅቤ እናጥባታለን

እናንደላቅቃታለን ትምጣ ትምጣ

እንደ ዝንጅሮ ቂጥ መላጣ

እንደ ግድግዳ በእበት የቆሸሸሸ

እሳት አጠገብ እንዳለ ቆጥ ጥላሸታም

የቂጣ ቁራሽ በአንዴ የምትውጥ

የቂጣ ጥፍጥፍ የምትልስ

ሰንበሊጥ ውስጥ ተደብቁብሽ ስትፈልጊኝ ትውያለሽ አጅሬ

እንሰት ውስጥ ተደብቄ ስትፈልጊኝ ትውያለሽ  አጅሬ

የልጇን ክሽንክሽ ምግብ አትለምድም

የእናቴ ልጅ

የመጀመሪያው ስንኝ ልጅቷ ቤት በነበረች ጊዜ በጣም ተጎሳቁላ ከባድና አስቸጋሪ ስራዎችን እንደምትሰራ እና ይህ መከራዋ እኔን ያገባች ቀን ያበቃል፡፡ በእኔ ቤት ድሎት፣ ምቾት አለ፡፡ ‹‹ጊደር እንድታልብ እናደርጋታለን›› ይህ አባባል በእኔ ቤት የሚበላው ነገር ሁሉ ቅቤ ያልነከው ወይም ቅቤ የማይጨመርበት ምግብ የለም፡፡ እስከሚሰለችሽ ድረስ በቅቤ ትበያለሽ ነይ አይነት መልዕክት ያለው ነው፡፡

ከአምስተኛው ስንኝ በኋላ ያለው ስንኝ መልኳንም፣ ኑሮዋንም የመጣችበትን የኖረችበትን ኑሮ የማጥቆ፣ የማበላሸት አይነት ይመስላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከድህነቷ የተነሳ ሆዳምና ስግብግብ እንደሆነች አንድ ጥፍጥፍ ቆሎ አራት ጊዜ ብቻ ትጎርሰዋለች፡፡ ቂጣ በምላሷ የምትልስ ነች፡፡ ደግሞ እኔ እውቃታለው ከፊቷ ዞር ስልባት አጠገቧ እያለሁ እየፈለገችኝ የምትውል ናት፡፡ እንሰት ውስጥ ኮባ ከልሎኝ ብቆም አንኳን ሀገሩን ሁሉ እያሰሰች የምትውል ናት እኔን ትፈልገኛለች፤ ትወደኛለች፤ አውቃለሁ፡፡ እያሉ ወንዶቹ ሲያቀነቅኑ ሴቶቹ እነሱ የሚሉት ነገር ሁሉ እሷን የማይመለከታት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ቡላ በቅቤ በልታ ያደገች ናት›› ይሄ የምትሉት ቆሎ እንኳን መዋጥ መላስ ቀርቶ ቆሎ በአፏ

አትነካም ቡላ ከቆጮ ተጣርቶ የሚወጣው የውስጠኛው ክፍል ተሰርቶላት በቅቤ የምትበላ ናት፡፡ የበግ ጠቦቶችን ስጋ እየበበላች ያደገች እንጂ የእሱን ቤት ምናምንቴ ምግብ አትለምድም የሚል መልዕክት ያዘለ ነዉ፡፡

| ጎኑ | ሜሴላከት |
|---|---|
| ቴ ሜሲሌ ደናሜ | ሀሴንቲ ሚሀቲ አስናምበኣ |
| ኢራሜ ኢንጋሜ | ተ ወርቃታ አስናምበኣ |
| ሰጄ ቤቱት ወጋሜ | ተ ሉባምታ አስናምባ |
| ቦሎቹ ኢሌ ዋል ኦሮናም ዋል ኦሮናም | ኢራምታ አስናምበአ |
| ቆቱ መሪቤ ቆድቢ ወጊቢ | ኢንጋምታ አስናምበኣ |
| አማቢ አናቢ ቦክቢ መሬቤ | አስናምበኣ አስናምበኣ አስናምበኣ |
| ቴ ሜሲሌ ዋልቤ ዋልቤ | |

**ትርጉም**

| ወንዶች | ሴቶች |
|---|---|
| አንቺ ልጅ ቆንጆ | የፈለካት ለምንድነው አንሰጥም |
| ባለጌጣጌጥ | ይህቺን ወርቅ አንሰጥም |
| ንጽሁ የከምባታ ልጅ ወግ ያለሽ | ይህቺን ባለሙያ አንሰጥም |
| ሠርጋችን ደርሷል ነይ እንሂድ | ይህቺን ባለጌጣጌጥ አንሰጥም |
| ጥሎሽ ሂዶልሻል | አንሰጥም አንስጥም አንሰጥም |
| የየድርሻው የወጉ | |
| የእናት የአባት የዘመዱ | |
| አንቺ ልጅ ነይ ባክሽ ነይ ባክሽ ነይ | |

ከለይ የተገለጸውን የጋብቻ ባህል ጭፈራ ግጥም የእያንዳንዱ ስንኝ ሀሳብ ወንዶቹ ሙሽራዋን የሚያሞግስ በጌጣጌጥ የተዋበች የተፈጥሮ ውበት ያላት፡፡ ከጥሩ ጎሳ የተወለደሽ፤ ባህልና ወግ የምታውቂ እኔም የሚገባሽን ባህሉን ወጉን ጨርሻለሁና አሁን የቀረሽ አንቺ ነሽና ነይልኝ ብሎ ለማግኘት በመናፈቅ ስሜት እንድትመጣለት ይናፍቃል፡፡ ሴቶቹም በበኩላቸው ይህቺን የመሰለች ልጅ አንሰጥም የምታጓጓ፣ የምታምር፣ ቆንጆ ባለጌጥ፣ አንሰጥም አንሰጥም ይላሉ፡፡ ሴቶችም ላለመስጠት ፈልገው ሳይሆን የእሷን ውበትና ዝና ለመግለጽ እንጂ መሄዷን ልባቸው ያውቀዋል፡፡

#### 4.2.1.6 ‹ሴሌሞመ ድኩተ› የድንግልና የመጨረሻ ገበያ

ሴሌሞመ ድኩት፡ የድንግልናዋ የመጨረሻ ገበያ ለሠርጓ አንድ ሳምንት ሲቀረው የመጨረሻ ገበያ ትሄዳለች፡፡ ሀቡቢሳ (ያልበሰለ ቅቤ) ፀጉሯ ላይ ይርከፈክፍና ከብዙ ጓደኞች ጋር ገበያ ትሄዳለች፡፡ አወጣጧ አፍሮ ፀጉር አድርገው ቅቤ ያርከፈክፋሉ፡፡ ይህ በከምባትኛ ‹‹ዲንቢጭ›› ይባላል፡፡ ከብዙ ጓደኞቿ ጋር በመሆን የመጨረሻዋን ገበያ የምትወጣበት ቀን ነው፡፡ ጓደኞቿ ክብ ይሠሩና መሓል አድርገዋት እየጨፈሩ ነው ይዘዋት ይሄዳሉ፡፡ አንገቷ ላይ ‹‹ሶፋ›› የአንገት ጌጥ እጅዋ ላይ ሰጋዮ የእጅ አምባር ስለምታደርግ የሚያያት ሁሉ የታጨች መሆኗን ያውቃል፡፡

የዚህ ስርዓት አላማ የእናትዋን ቤት ገበያ መላላክ ዛሬ ያበቃል፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የራስዋን ቤት የኑሮ ገበያ የምትጀምርበት ቀን ነው ለማለት ነው፡፡

#### 4.2.1.7 ሰጋዩተ መረሙ (የሠርግ ጥሪ አደራረግ)

ሁለት ሳምንት ሲቀራት ሠርጓን ለዘመድ በሙሉ ዞራ ‹‹ከን በሬን ኢሃ ቦሎቸ›› በዚህ ቀን ሠርጌ ነው፡፡ እያለች ከአንድ ጓደኛዋ ጋር በመሆን በእያንዳንዱ ቤት እየዞረች የሠርጓን ቀን ትነግራለች፡፡ ይህ ሁለት ዓላማ አለው አንደኛው ከዚህ በፊት ለሠርግ፣ ለግርዛት፣ ለሌሎች ጉዳዮች የሰጠችው ስጦታ ካለ እንዲመልሱላት መንገር ነው፡፡ ሁለተኛው እንዲመልስላት የተጠራው ዘመድ ገንዘብ ወይንም ዕቃ ይዞላት በተጠራው ቀን ይመጣል፡፡ ለአዲሱ ጎጆ ቤቷ የሚያስፈልጋትን ዕቃዎች ሁሉ ዘመዶቿ እየተመካከሩ ይገዙላታል፡፡ አክስት እኔ ሰፌድ አዘጋጃለሁ ካለች ሌላዋ ደግሞ ሳህን ትሪ አዘጋጃለሁ፣ አጎት አንዱን ዕቃ

አዘጋጃለሁ ይላል፡፡ ጓደኞቿም እንዲሁ ይመካከራሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉት አንዱን ዕቃ ብቻ ብዙ ሰው ገዝተና ሌላዉ ዕቃ ሳይገዛ እንዳይቀር ለማድረግና የሚያስፈልጋት ዕቃ ሁሉ ማግኘት እንድትችል ነው፡፡

አንዳንድ ሠርግ አዘጋጅ ሴቶች እራሳቸው የእቃዎቹን ስም ዝርዝር ያዘጋጁና ለዘመዶች ይከፋፍላሉ፡፡ አንተ ይሄንን ግዛልኝ፣ አንተ ደግሞ ሌላዉን አሰራልኝ፣ አንቺ ይህንን ግዢልኝ አንቺ ሰፌድ እያለች የሠርጓን ቀን ስትነግር ከሰውዬው የምትፈልገውን ስጦታ ጭምር ነግራ ትመለሳለች፡፡ በነገረችው እለት ሁሉም ሰው የታዘዘውን ስጦታ ይዞ ያቀርባል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ስጦታን ሲሰጥ የስጦታውን ስም እየጠራ እድምተኛው እልል

እያለ እያየ ያስቀምጣል፡፡

**ሙሽሪት ከጓደኛዋ ጋር እየዞረች የሠርግ ጥሪ ስታደርስ**

**የሚሰጣት ባህላዊ እቃዎች፡-**

| መገኛ ቋንቋ | ትርጉም | መገኛ ቋንቋ | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| ደጉዲተ | ሰፌድ | ሌማተ | መሶብ |
| ሜሜተ | ወንፊት | ቡዲ ሞቁተ | የቀንድ ማንኪያ |
| ቁና | የምርት ማፈሻ | ሁፉተ | የጸጉር ማበጠሪያ |
| ወጭተ | ሎሎ | በርጩመ | ወንበር |
| ኢትልተ | ቁርበት | ጠጠበ | መቀነት |
| ባሬትተ | ፖፖ | ቡራቱተ | የተፈጨ ዱቄት በቅቤ |
| ሺሎ ቡና | የተነጠረ ቅቤ | ኤንዴቤሩ | ጅባ |
| ቦርካኑ | ትራስ | ገበታ | ገበታ |
| ቡቺ ኦዳተ | ሸክላ ሲኒ፣ኩባያ | ሶሮ | እርቦ |

የእናትና የአባት ስጦታ የዚያን ቀን ለብቻ የሚሰጥ ነው፡፡ አባት የሚሰጠው ስጦታ ጌጌያ ይባላል፡፡ ይኸውም አንዲት ጊደር እና አንድ ወይፈን ይሆናል፡፡ ይህንን የሚሰጥበት

ምክንያት ከብት አርብተው ወተት እየጠጡ እንዲኖሩና የከብት ባለቤት እንዲሆኑ በማሰብ ነው፡፡ እናት ከቤት ውስጥ ቁሳቁስ እና በሙሽራነት ጊዜዋ የምትጠቀምበት በጥሩ ሁኔታ የተነጠረ ቅቤ ታዘጋጃለች፡፡ ሌላው ለልጁ እናት የምታዘጋጀው ስጦታ ነው፡፡ ለባሏ እናትም ለልጇ የሰጠችውን ዕቃ ጥንድ ጥንድ እያደረገች የማዘጋጀት ግዴታ አለባት፡፡ ሰፌድ ካዘጋጀች አንዱ ለባሏ እናት አንዱን ለሙሽሪት እያደረገች እያንዳንዱን ስጦታ በዚህ መልክ ታዘጋጃለች፡፡ በሠርጓ ዕለት ስትሄድ ስጦታወቿ በሙሉ አብረው ከእሷ ጋር ይሄዳሉ፡፡

### 4.2.1.8. ‹‹ ኪፋ›› ግብዣ

በቆርሲሻ የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ሀብታሞች ብቻ የሚፈጽሙት ስርኣት ነው፡፡ ሀብታም ሰዎች ያላቸዉን ይዞታ፣ የሀብት፣ የዘር ክብርንና ዝናን በመንተራስ የሚዘጋጅ ነዉ፡፡ የልጅቷ ሰርግ እንደ ነገ ሲሆን ዛሬ የልጅቷ ቤተሰብ ሰፊ ድግስ ይደግስና አግቢው አጃቢዎችን ይዟቸው እንዲመጣ ያደርጉና እያበሉና እያጠጡ የሚያሳድሩበት ስርኣት ነው፡፡ (ስፍላ) ከነ ሙሽራዉ ባህላዊ ጭፈራቸዉን እየጨፈሩ ለአዳር ወደ ሙሽሪት ወላጆች ቤት ሄደዉ እየበሉና እየጠጡ አድረዉ በሁለተኛ ቀን በርካታ ስጦታዎችን (ጌጊያ) ማትለም ወይፈን፣ ግደር፣ ፈረስ ከነ ሙሉ ዕቃዉ፣ የቤት ዉስጥ ሙሉ ቁሳቁስ ተሰጥቷቸው እንዲመለሱ የሚደረግበት ስርኣት ነዉ፡፡ ለኪፋ ቆርሲሻ ሠርግ ለአጃቢነት የሚመረጥ ሰዉ ከየቤተ ዘመዱ ጠንካራና ግርማ ሞገስ ያለዉ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛዉ በሙሽራይቱ ቤተሰብ ላይ የተሰበሰበዉ ዘመድ አዝማድ ለእንዲህ ዓይነት ሰዉ ነዉ ወይ? ልጅቱ የተሰጠችዉ (የሚትዳረዉ) ስለሚባል ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ምክንያት ደግሞ በድንገት ሁለት የተለያዩ ሙሽሮች በመንገድ የተገናኙ እንደሆነ በመጠጥ በተጋጋለ ሁኔታ ያሉ ከመሆናቸዉ የተነሳ ሙሽራይቱን እንቀማ ይባባሉና አንድ ሁለት አንድ ሁለት ስለሚሉ ይጣላሉ፡፡ የከረረ ድብድብም ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ ያንን ሁሉ ለመመከት የሚችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

ከአጃቢዎቹ (ከ"ስፍላዉ") መሃል ስድስት ሰዎች ተመርጠዉ ‹‹ቁቡታ››ሽማግሌዎች ተብለዉ ይሄዳሉ፡፡ ከእነዚህ ስድስት ሰዎች ሁለቱ ሴቶች መሆን አለባቸዉ፡፤ ሁለቱ ሴቶች ልጅቷ ሞኝ ብትሆን የሚመክሯት፣ ሙያ በደንብ ያልተለማመደች ከሆነች ሙያ የሚያስተምሯት

እና ለባለቤቷ ምቹ ሴት እንድትሆን በአጠቃላይ ስለትዳር ምንነትና እንዴት የከምባታ ሴት የትዳር ሕይወቷን መምራት እንዳለባት የሚያስተምሯትና ቀናዉን መንገድ የሚያሳዩአት ናቸዉ፡፡ ልጅቱ እነዚህንና ሌሎች ነገሮችንም ባለማወቅ የምታስቸግር ከሆነች ባለቤቷ ለወላጆቿ ከመንገሩ በፊት ለሴቶቹ እንዲመክሯት ይነግራቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሴቶች በትዳር ዉስጥ ስለሚከሰቱ ነገሮች በግልጽ ይነግሯታል፡፡ ከወንዶቹ ሁለቱ ደግሞ የተለያየ ኃላፊነት መሃላ ገብተዉ የሚቀበሉ ናቸዉ፡፡ እነሱም "እሌቢሃ እንቆቢሃ" የዓይንና የጥርስ ኋላፊነት የሚወስዱ ናቸው፡፡ በትዳር ዓለም ዉስጥ በተለያዩ ክስተቶች መጋጨት ወይም በትንንሽ ጥላቻዎች መቃቃር አይቀርም፡፡ በመሆኑም እነዚህን የመሳሰሉ ችግር የሚቀርፉ ናቸዉ፡፡ ባልና ሚስት ሲጋጩ በድንገት ዱላ አንስቶ ሲመታት ጥርሷን እንዳያወልቅ እና ዓይኗን አጥፍቶ አካል ጉዳተኛ እንዳያደርጋት ለጥንቃቄ ተብሎ ወንድዬዉን እንዲመከሩ ኋላፊነት የሚወስዱበት ነዉ፡፡

ሁለተኛዉ ደግሞ "ሐማምቢሃ" የእሸት የተባዉ ጎረቤት በጊዜ ዘርቶ እርሷ የሌሎችን እሼት እንዳትከጅል የአዝመራ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘራና አስፈላጊዉን ሁሉ እንዲያሟላላት ችግሮች ካሉ የምትነግራቸዉ ናቸዉ፡፡ እንዲሁም በቤተሰብ ዉስጥ ባለቤቷ የማይመቻት ከሆነ ለወላጆቹ ለመንገር ስለምትፈራ ያላትን የዉስጧን ብሶት ሆነ እንዲመቻችላት የምትፈልገዉን ሁሉ የምትነግራቸዉ ለእነዚህ ለዓይን፣ ለጥርስና ለእሸት ሃላፊነት ለወሰዱት ሰዎች ነዉ፡፡

ከላይ የተነሳውን ሀሳብ ስንመለከት ሀብትና ዝናን ለማሳየት ተብሎ በሚደገስ ድግስ ላይ አግቢው ይዞ መመጣት የሚገባው ሰው…ጠነካራና ግርማ ሞገስ ያለው … ሲሉ ማንነቱን ለማሳየት ከፍተኛ ድግስ የደገሰዉ የልጅቷ ቤተሰብ አግቢው ኮስመን ያለ ሰው ይዞ ቢመጣ ቤተሰቡ ሊያፍር ነው፡፡ ምክኒያቱም እንዴት ሀብታም ሆኖ ለደሀ ቤት ልጁን ሰጠ ተብሎ ስለሚወቀስ ነው፡፡ ስለዚህ አግቢው ይዟቸው የሚመጣው ሰዎች ወፈር፣ ረዘም ያሉ በዘርም ቢሆን ታዋቂ መሆን አለባቸው ለማለት ነው፡፡ ..ለእንዲህ አይነት ሰው ነው ወይ….የሚለው አባባል ይህንኑ ሀሳብ  የሚያጠናክር ነው፡፡

ሌላው የተነሳው ነጥብ ለሶስት አይነት ወገኖች ሶስት አይነት ሀላፊት ሲሰጡ እናያለን፡፡ ከሴት ወገን ሙያ የምታስተመር፣ ከወንድ ወገን አንዱ ጥላቻ ቢፈጠር አስታራቂ፣ ሌላው

የእርሻ ስራ እንዳይደክም ተቆጣጠሮ ችግር የሚፈታ ተብሎ የቅርብ ሰዎች ተመርጠው በሰው ፊት የትዳር ዘመናቸው ሰላማዊና የተሳካ እንዲሆን የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የልጅቷ ቤተሰብ አደራ ጭምር ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሀሳብ የኑሮ መሰረት ሰላምና ተስማምቶ መኖር፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሚሆን ሀብት ማሟላትና ሴት ልጅ ባለሙያ ሆና መገኘት ነው የሚል አምነት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ሴት ልጅ የምትሸከመው በርካታ ኃላፊነት እንዳላት ሁሉ ይህንን ኃላፊነት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣት ባለሙያ ሆና መገኘት ይኖርባታል፡፡ ስለዚህም ይሆናል አስቀድመው ክፍተት ቢኖር ሊደፍን የሚችል ሰው ያዘጋጁት፡፡ መሰረታዊ የትዳር ሕይወትን ለመግፋት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ተለይተው ጋብቻው ችግር እንዳይገጥመው ለማድረግ ይመስላል፡፡

የእሸት ኃላፊ ባል (በእርሻ ስራው ቢደክም፣ ቤተሰቡን ማስተዳደር ቢያቅተዉ የሚበላ ቢታጣ የእሸት ኃላፊ የለውም ወይ? ይባላል፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው እጁን አጣጥፎ መቀመጥ የለበትም፡፡ ኑሮን ለማቅናት የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከመምከር ጀምሮ እስከ አብሮ መስራት ድረስ የሚደርስ መስዋትነት መክፈል ይጠበቅበታል፡፡

ጥላቻ ቢፈጠር ተብሎ ኃላፊነት የሚወስድ ሰው ይህንኑ የሰላማቸውን ጉዳይ በአንክሮ መከታተልና ችግር ቢፈጠር ችግሩን የመፍታት ሀላፊነት ተጥሎበታል፡፡

በአጠቃላይ ይህንን ለሶስት ወገኖች ኃላፊነት የመስጠት ትርጉም ሲፈታ ጋብቻው እክል እንዲያጋጥመው በተሳካ መንገድ እንዲቀጥል ለማድረግ ነው፡፡

የቆርሲሻ ጋብቻ ዓይነት በቤተሰብ ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከፍተኛ ክብርና ቦታም የሚሰጠዉ ነዉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ዘመድ አዝማድ እና ወዳጅ ሁሉ ተሰብስቦ የሚደሰት በመሆኑ ኤገሌ ልጁን ወይም ልጅቱን እንዴት ዳረ የሚሉ ነገሮች ስለሚነሱ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ የሚደገስ ሥርግ ነዉ፡፡ የተጋቢዎች ቤተሰብ የተመጣጠነ መሆኑ መጀመሪያዉኑ የሚታወቅ ስለሆነ የፉክክር ሁኔታም ስለሚኖር ላቅ ያለና የደመቀ ዝግጅት ይሆናል፡፡

ቆርሲሻ በዕለቱ አጃቢዎች "ስፍላዉ" ሚዜዎቹ ጋር ሄደዉ ሙሽሪቱን ይዘዉ የሚመጡበት

ሁኔታም አለ፡፡ እንድህ ባለዉ የቆርሲሻ ሠርግ አግቢዉ ከአጃቢዎች ጋር አብሮ አይሄድም፡፡ የልጅቱ ቤተሰብ ለሚጠይቀዉ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡትና አስፈላጊዉን ሁሉ ጠብቀዉ ኃላፊነት የሚወስዱት ከሁሉም አጃቢዎቹ በበለጠ በመጀመሪያ ‹‹ቂቦ›› የተባሉት ስድስቱ ሰዎችና ሚዜዉ ይሆናሉ፡፡

በሠርጉ ዕለት ጧት በሙሽራይቱ ቤት ኮሶ የመጠጣት ፕሮግራም ይከናወናል፡፡ ኮሶ የምትጠጣበት ምክኒያት ሙሽሪት በሠርጓ ማግስት እስከ ሶስት አራት ቀን ድረስ ወደ ሽንት ቤት እንዳትሄድ ኮሶው ሆድዋን ያጥበውና ያደርቀዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ከመጠጣቷ በፊት ከሚዜ ጋር ሙሉ ተቀድቶ ሌሎች የወንድና የሴት ጓደኞችዋ ከኋላም አጅበዉ ይቆማሉ፡፡ ሴት ሚዜዋ የሽልማት "እሪፎ" ሥነ-ሥርዓት ለመጠየቅ ስለምትፈራ ከቤተዘመድ አንድ ወጣት እሱም ሙሉ ይይዝና ከአባት ጀምሮ ሁሉን የቅርብ የሆነዉን ቤተዘመድ የአባት ወገንን እና የእናት ወገንን "እርፉተ አስዬ" እያለ ይጠይቃል፡፡ ይህን ሰጥተናል ሲሉም ‹‹መጋኑ እሱ በራቹ›› ይላሉ፡፡ በመቀጠልም ባህላዊ ምርቃት ይመርቃል፡፡ ትዉለድ ትክበድ ‹‹እልቱ ስርቱ›› እግዚአብሔር የአባቶቻችን አምላክ ያስፋት በማለት ሽማግዎቹ ይመርቋታል፡፡ ይህ ምርቃት ቀደም ሲል የነበሩ አባቶቻችን በዝተው ተዋልደው እኛ ለዚህ በቅተናል፡፡ እነሱን ያበዛ ያሰፋ አምላክ አንቺንም እንድትዋለጂ እንድትከብጂ እንድትከብሪ ያድርግሽ ለማለት ነው፡፡

የምርቃቱ ሥነ-ሥርዓት እንዳለቀ የኮሶ አጠጣጥ ይቀጥላል፡፡ በእናት ወይም በአክስት ተደቁሶ የተዘጋጀዉን ኮሶ ከቦርዴ ጋር በደንብ ከበጠበጡና ካዋሃዱ በኃላ መጀመሪያ ለ "እሪፎ" (ለሽልማት) የያዙትን ሙሉ ከሚዜዋ ጋር ይቀምሳሉ፡፡ አቀማመሱ ሚዜ ለሙሽራዋ ሲሆን ሙሽራዋ ለሚዜዋ ነዉ፡፡ ይህ የከምባታ ባህል ሙሉ ያድርገን ህብረታችን አንድ ነዉ፡፡ በማንኛዉም ሁኔታ አንካካድም ተወዳጅተናል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ቅምሻ ከባድ ቃለ-መሃላ እንደ ሆነ ስለሚቆጠር የመከባበርና አንዱ አንዱን የመጠበቁ ነገር እጅግ የጠበቀ ነዉ፡

**ሙሽሪት ኮሶ እንድትጠጣ የማደፋፈሪያ ጭፈራ**

***መገኛ ቋንቋ*** ***አማርኛ አቻ ፍቺ***

| | |
|---|---|
| ጪሞ ሸባ ሸባ | ገዱ ይመችሽ |
| ጪሞ ሁርቦ ሁርቦ | የሆድሽን ውስጥ ያንጻ |
| አት ደናሚታ | አንቺ ቆንጆ ልጅ ነሽ |
| አባ ሚኔን ቀለንቴንትተ | ከከበረ ቤተሰብ የተወለድሽ |
| ኒ ቤቱት ወጋሚታ | በወጉ የምትዳሪ |

የተሰበሰቡ ወጣቶች እንደሁኔታዉ ሌሎችም የማደፋፈሪያ የሚሆን ባህላዊ ዘፈን ‹‹ጬሞ ሻባሻባ›› ‹‹ጬም ሁርቡ ሁርቡ›› እያሉ ቁንጅናዋን፣ አስተዳደጓንና የቤተሰቧ ክብርና ዝና እያነሱና እያሞጋገሱ ይጨፍራሉ፡፡ አጨፋፈሩ አንድ ወይም ሁሉም ጎሮምሶች ተሸክመዋት እየዘለሉና እያዘለሏት ክብ በመስራት የሚጨፈር ነዉ፡፡የሚሸከምዋት ለሁለት አላማ ነው፡፡ አንዱ አላማ ልክ ህጻን ልጅ ወተት ተግቶ ሲነሳ እንዲያገሳ እንዲስማማው ተብሎ ጀርባው እየተደለቀ እንደሚያዋህዱለት ኮሶ እንዲስማማት ለማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ክብርና ዝናዋን እየነገሯት የመራራ የኮሶ ጣዕም እንድትረሳው ለማድረግ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ሙሽራይቱ ኮሶ እስኪያሽራት ድረስ የቤተዘመድ ወጣቶች የሰፈር ጓደኞችዋ አብረዉ በመሆን ያጫዉቷታል፡፡ ጓደኞችዋንም በሚዜዎችዋ አማካይነት ከተዘጋጀዉ ድግስ በመጋበዝ ታስደስታቸዋለች፡፡ እንዲህ እየተባለ እየተጠጣና እየተጨፈረ የአጃቢዎች መምጫ ይጠበቃል፡፡

### 4.2.1.9. አጃቢዎች ሙሽራዋን ይዘው ሲሄዱ የሚዘፍኑት ዘፈን

| **መገኛ ቋንቋ** | **አማርኛ አቻ ፍቺ** |
|---|---|
| ሜሲሌታ ኢዬላ | ልጅቷን እንኩ ተቀበሉ |
| ኢዬላ አቅዬ | እንኩ እንኩ ተቀበሉ |
| ባጃምታ ኢዬላ አቅዬ | ወጣቷን እንኩ ተቀበሉ |
| ደናምታ ኢዬላ አቅዬ | ቆንጂን እንኩ ተቀበሉ |
| ደናምታ ሎካሴ ኢዬላ አቅዬ | ቆንጆ እግሯን ተቀበሉ |

| | |
|---|---|
| አባ አበሞ ዮቤ | አበሞ የተባለ ጫወታ አለን |
| ኀባንተሴ ዮቤ | የአንገት ወዝዋዜ የቀረ አለ |
| ወም ምኒ አለቾት | የንጉስ ቤት ጫዋታ |
| ከንንቀጣንዶ | ይሄን ያህል ነው ወይ |
| አበም አባሞ ዮቤ | አበሞ አበሞ ጫወታ አለን |
| ያመዞንተሴ ዮቤ | የወገቧ እስክስታ ይቀረዋል |
| አለጽቴንበቤ | አልተጫወታቸሁላትም |
| ኢሴን ኩሌኖ | ለእሷ የሚነገርላት |
| ከንንቀጣንዶ | ይህ ብቻ ነው ወይ |

ከላይ ያሉትን ስንኞች ስንመለከት መልዕክታቸው የልጁ ዘመዶችና ቤተሰቦች አንድ መልካም ነገር ይዞ እንደመጣ ሰው አደራ እንደሚሰጥ እንኩ እንስጣችሁ ውሰዱ ዓይነት መልዕክት ያለው ሲሆን ‹‹ ደናምተ  ሎከሴ እየለ አቅዬ›› ቆንጆ እግሯን እንኩ ተቀበሉ ይዘን የመጣንላችሁ ገድ ያላት ኮቴ እርጥብ እሷ ቤታችሁ ስትገባ ቤታችሁ በብዙ ጥሩ ነገር ይቀየራል፡፡ ይህንን መለካም ዕድል ነው ይዘን የመጣነው እንኩ ስለዚህ በ‹‹አበሞ›› ጫወታ አድምቀን እንጫወት፣ ጨፋሪዎች በዚህ ልክ አይደለም መወዛወዝ ያለብን አንገት በደንብ አልተወዛወዘም፤ የንጉስ ልጅ ጨዋታ እንዲህ ብቻ ነው ወይ? የሚገባትን ያህል አልተጫውንም፤ የወገብ እስክስታ እንዲህ ነው ወይ? እሷን አይመጥናትም ጠብ እርግፍ ማለት አለብን ስለዚህ ለእርሷ የሚገባትን ዓይነት እስክስታ፣ ውዝዋዜ፣ ጭፈራ ማድረግ ይገባናል፡፡ ለእሷስ የሚገባው ግጥም ቅኔ ይህ ብቻ ነው ወይ? እያሉ የልጅቷን ጥሩነት ፣ ውበት፣ የትልቅ ሰው ልጅ መሆኗን በግጥም እየገለጹ እያሞጋገሷት ሲሄዱ እናስተውላለን፡፡

ከቀኑ 10-11ሰዓት ባለዉ ጊዜ ሙሽሪቷን የሚወስዱ የወንድ ሚዜና የተወሰኑ የቤተሰብ ሽማግሌዎች ወደ ሙሽሪት ቤት ሲገቡ ሌሎች አጃቢዎች ግን ዉጭ ይጠብቃሉ ፡፡ አጃቢዎች ልጅቷን ለመውሰድ በመጡ ሰዓት ቤተሰቡ ያቀረበላቸውን ምግብ እየበሉ ቀልድ ቢጤ ስድብ ይሰዳደባሉ፡፡ ከሚሏቸው ስድቦች መካከል አቶ አቦ ለጅቦ እንዲህ ያስታውሳሉ ፡-

## የልጅቷ አጃቢዎች ሙሽራውን ሲነቅፉ

| መገኛ ቋንቋ | የአማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ሚሴሌ ቦኩ | የልጅቷ ቤተሰቦች |
| አት መርቿኒ | አንተ ምንድነህ? |
| ሀበንካኒ | ምን ያህል ነህ? |
| ኒ ቤቱት ወርቀተቤ | የእኛ ልጅ ወርቅ ናት |
| ኒ አመ ቤቱት አንጋተ የኖታቤ | የእኛ ልጅ እኮ የከበረ ቤተሰብ ልጅ ናት |
| እቾተ ሀቂንን ቁርጨአአኖቤ | ምግብን ከነነፍሱ የሚዉጥ |
| ምኔንተስ ዱቡምቧቤ | በቤቱ ጠግቦ የሚበላ ምግብ የሌለዉ |
| እሴአን ቦኩ ዱበላሻቤ | የአባቷ ቤተሰብ ሀብታም ነው |
| መ ቡቸ ቆቼቤ | ደግሞ የሰጠህው ምን ጥሎሽ ነው |

ከላይ የተገለፀውን ስድብ ቢጤ ቀልድ ስናይ፡ የሁለቱም ወገኖች እራሳቸውን ሲክቡ አንዱ አንዱን የማጥላላትና ሌላውን ዝቅ አድርጎ የእኛ ቤተሰብ ይበልጣል አይነት ስነ ልቦንን ሲነኩ እናስታውላለን፡፡

‹‹አትስ መርቿን›› አንተ ምንድነህ? የሚለው ሀሳብ እራስህን ትልቅ ለማስመሰል ያደረከው ጥረት እንጂ እኛ እናውቅሃለን፡ ከማንም አትበልጥም ይልቁንም የእኛ ዘር ከአንተ ዘር ይበልጣል ዓይነት መልዕክት ያለው ነው፡፡

ይህንኑ የሚያረጋግጥልን ሀሳብ ‹‹ ሀበንካን›› አንተ ምን ያህል ነህ? ሲሉ የእሱን ክብደት ከሀብቱ ከገንዘቡ ካለው ነገር ጋር ለማገናኘት ሲፈልጉ ነው ፡፡ የኑሮህ መጠን እናውቀው የለም፤ ያለህ ነገር በጣም ትንሽ ነው፡፡ ድንበርህን ለማስፋት አትሞክር ለማለት ፈልገው ነው ፡፡ከዚህ ጋር አያይዘው እሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ነገር ከነሱ በኃላ የልጃቸውን በዘር በሀብት ትልቅ መሆኗን ለመግለጽ ጥረት ሲያደርጉ በቀልዱ ውስጥ ይስተዋላል፡፡

‹‹ ኒ ቤቱት ወርቀተቤ›› የእኛ ልጅ ወርቅ የሆነች ናት…፡፡ መልኳ ቆንጆ ነው፡፡ ባህሪዩዋጥሩ ነው፣ ባለሙያ ናት፣ የሚወጣት ነገር የለም በዘርም ቢሆን አንቱ የተባለ የተከበረቤተሰብ ልጅ ናት፡፡ ‹‹ ኒ አመ ቤቱት አንጋተ ዬኖተ ቤቱ›› የኛ ልጅ የተከበረ ቤተሰብያላት ልጅ ነች የሚለው ሀሳብ ይህንን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምግብ አቅርበውላቸው አበላላቸውን እያዩ የዲሃ ልጅ አበላል ነው ያለህ ምግቡን ከነምናምኑ እየዋጥከው ነው ቤትህ ጠግበህ በልተህ እንደማታውቅ የምግቡ አያያዝህና አጎራረስህ ያሳያል፡፡ በአጭሩ ደሃ ነህ እያሉ ይነግሩታል፡፡

‹‹መ ቡቸ ቆቼቤ›› ምን ታህል ጥሎሽ ሰጥቷል፡፡ ይህም ሀሳብ የሚያሳየው በዚህ ድህነቱ ምን ስጦታ ሰጥቶ ነው ያገባት የማይረባ ነገር ሰጥቷል እያሉ በተለየ መንገድ ድህነቱን እያስረዱት እና እያረጋገጡለት ነው፡፡ የልጁ አጃቢዎችም የመለሱለትን መልስ ልጅቷ ችግረኛነቷን፣ ድህነቷን፣ በእሱ ቤት መጥታ እንደምታራግፍ ይነግሯታል፤ ያስረዷታል፡፡ የሁለቱም ቀልድ መሰል ስድብ እኔ ትልቅ ነኝ፣ አንተ ትንሽ ነህ፣ እኔ በዘርም በሀብትም ትልቅ ነኝ አንቺ ግን ትንሽ ትንሽ ነሽ እየተባባሉ ሥነ-ልቦናን የመስለብ ሥራ እየሠሩ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ስነ ልቦናው በማህበረሰቡ ውስጥ ለጋብቻ ተፈላጊ ባህሪና ማንነት ምን እንደሆነ ያሳየናል፡፡የተመረጠ ጥሩ ደረጃና ክብር የተሰጠው ጎሳ አግኝቶ በጋብቻ መጣመር እድለኛ መሆን ነው ለማለት እንጂ ድህነትና ትልቅነትን፣ ትንሽነትን ለመስበክ አይደለም፡፡

**የሙሽራው አጃቢዎች ከሙሽሪት አጃቢዎች ጋር ሲነቃቀፉ**

| <u>መገኛ ቋንቋ</u> | <u>የአማርኛ ትርጉም</u> |
|---|---|
| ቲ ሀዊ ቴኢት | ይህች የተቸገረች |
| ሀወክ ኒ ምኔን ግግሸቅተንት | ችግርሽን እኛ ቤት ታራግፊያለሽ |
| ቡጥመክ ኒ ምኔን ጦጵታንት | ድህነትሽን እኛ ቤት ትጨርሺያለሽ |

የልጁ አጃቢዎችም የመለሱለትን መልስ ስናይ ልጅቷ ችግረኛነቷን፣ ድህነቷን በእሱ ቤት መጥታ እንደምታራግፍ ይነግሯታል፤ ያስረዷታል፡፡ የሁለቱም ቀልድ መሰል ስድብ እኔ

ትልቅ ነኝ፣ አንተ ትንሽ ነህ፣ እኔ በዘርም በሀብትም ትልቅ  ነኝ አንቺ ግን ትንሽ ትንሽ ነሽ እየተባባሉ ይመስላል ነገር ግን ከላይኛው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ሥነ-ልቦናዊ መልዕክት ያዘለ ነው፡፡

**ሙሽራዋን ከመስጠታቸው በፊት የሚደረግ ስርኣት**

**ኢንቆቢት፣ ኢሌቢት፣ሀማሞቢ - የጥርስና የዓይንና የእሽት ሀላፊነት አሰጣጥ ስርኣት**

ከላይ የጥርስ፣ የአይንና የእሽት ሀላፊነት የሚወስዱ በሀብታሞች ቤት የሚደረገውን ስርዓት ተመልክተናል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች በመደበኛነት የሚፈጽሙት ስርዓት በመጠኑ የሚለይ ስለሆነ ከዚህ በታች እንደሚከተለው እናያለን፡፡

ሀላፊነት ለመውሰድ ተመርጠው የሄዱ ስድስት ሰዎች ይቆማሉ፡፡ በቆሙበት ከልጅቷ ቤተሰብ ጥያቄውን ካቀረቡት ሰዎች አንዱ‹‹ ዊማ ጉቢቱን አስዬ››፡- ይላሉ ሙሉ ይቅመሱ ስጡዋቸው ማለት ነው ፡፡በቆሙበት ለሥርጉ ከተጠመቀው መጠጥ ሙሉ ‹‹ጨንቆ›› መጠጥ እንዲቀምሱ ይደረጋሉ፡፡ ሙሉ ነገር መቅመስ በከምታ ባህል ‹‹ዊማ ጉቡ›› ሙሉ መቅመስ የራሱ የሆነ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በሠርግ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የተለያዩ ባህላዊ ኃላፊነቶች ለምሳሌ፡- ዳኝነት፣ ለጎሳ ለቤተሰብ፣ ለግለሰብ ወዘተ… ኃላፊነት ሲሰጥ ሙሉ ያስቀምሳሉ፡፡ የቀመሰው ሰው ሙሉ ኃላፊነት እንደወሰደ ሰዎችን እንደማይክድ አምኗል ማለት ነው፡፡ ያንን ኃላፊነት ባለ በሌለ አቅም ለመውጣት ይጥራል እንጂ በፍጹም ችላ አይልም በሠርግ ስርዓት ይኸው ይደረጋል፡፡

**ከልጅቷ ወገን የመጡ ሽማግሌዎችና ልጁ (አግቢው) ያዘጋጀው ሰዎች ምልልስ፡፡**

| | |
|---|---|
| ኑባቡ | ኢንቆብ ኢሌቢ ሀማሞቢ አዬት›› |
| ሽማግሌ | የጥርሷን የዓይኗ ኃላፊነት የሚወስደው ማን ነው? |
| ሰዉት | - ቆመው ‹‹ነአታ›› |
| አማቾች | - እኛነን |

ጉባቡ ‹‹ዊማ ጉቢቱን አስዬ››

ሽማግሌ ሙሉ ቀምሰዉ ስጧቸው

ሰዉት - ኢንቆሴ ኢሌሴ ገጉሴ ቆርጺቱን

አማች - ሙሽራዋን ጠርተው

- ጥርሷንና አይኗን እራሷ ትጠብቅ ይላሉ፡፡

እንዲቀመጡ ያዟቸውና በዚሁ ሀሳብ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

የምልልሱን አገላለጽ ስናይ ኢንቆቢት ኢሌቢት አዬት፤ የጥርሷን የዓይኗንና የእሽት ኃላፊነት የሚወስደው ማን ነው? ብለው መጠየቃቸው የልጅቷን አደራና ኃላፊነት የሚቀበል፣ ቢጣሉ የሚያስታርቅ፣ ልጅቷ ብትሞኝ የሚመክራት፣ ብታጠፋየሚቆጣት፣ ወደ ክፉ መንገድ እንዳትሄድ የሚያደርጋት ሰው ያስፈልጋታል ማለታቸው ነው፡፡ ሰው ሆኖ ፍጽም የለም ሙሽራዋ በጋብቻ አለም ስትኖር ልታጠፋ ልታበላሽ ትችላለች በዚህ ጊዜ ጥላቻ በመካከላቸው ቢፈጠር እንኳን የመኃል ሰው ገብቶ ትዳራቸውን ሊያቀና ያስፈልጋል፡፡ ሰው አብሮ ሲኖር ጥላቻ ይኖራልና ጥላቻ ካለ ደግሞ አስታራቂና የመኃል ሰው ስለሚያስፈልግ እነዚህን የመኃል ሰዎች በጋብቻው ቀን ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ የሠርጉ አድምተኛ ባሉበት አቁመው ኃላፊነት ይሰጧቸዋል፡፡ ኃላፊነቱን ተቀባዮች ጥላቻ ተፈጥሮ አይኗ እንዳይጠፋ ጥርሷ እንዳይወልቅ ጋብቻ እንዳይፈርስ የቅርብ ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው አውቀው ሀላፊነቱን የሚረከቡ ሰዎች መሆናቸውን ቀደም ሲል አንስቻለሁ ፡፡ ኃላፊነት ለመቀበል የቆሙት የመለሱት የምላሽ ስናይ ‹‹ኢንቆሴ ኢሊሴ ገጉሴ ቆረጽቱን›› ዓይንሽንና ጥርስሽን አንቺው ጠብቂ ሲሉ ይደመጣሉሰ፡፡ ይህ አባባል ወደ ጥላቻ ከሚመራ ነገር መጀመሪያ አንቺው ተቆጠቢ የስድብ ቃላት፣ ባልን የሚያስቆጣ ነገር እንዳትሠራና ክፉ ነገር እንዳትናገር ባልዋን አክብራ ወይም ለትዳሯ ተጠንቅቃ ከኖረች ባል ሊመታት ወይም ሊደበድባት አይችልም፡፡ ትዳሯ ጤናማ ሆኖ በፍቅር መኖር እንዲችል ለጥሩ ትዳር ወሳኝ ድርሻ እንዳላት መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ መክረዋት አልፈዋል፡፡

በሠርጓ ቀን ስም ይወጣላታል፡፡ የስም አወጣጥ ሥርዓት ላይ የሚሳተፉ ወይም ስሟ ሊሆን የሚገባው ይህ ነው ብለው አስተያየት የሚጠየቁት ከአጃቢዎች ውስጥ ጥቆማ እንዲሠጡ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ሁለት ከሽማግሌዎች የስሟን ስያሜ እንዲሠጡ ይጠየቃሉ በመጨረሻም

የልጁ እናት ስሟን እንድታወጣ ዕድል ይሰጣታል፡፡ ተራ በተራ ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው አካል ከእያንዳንዱ ጥቆማ ሰጪ ስሙን ያሰባስብና የልጁ እናት ያወጣችውን ስም ያጸድቃል፡፡ አጃቢዎችንና ሽማግሌዎች የስም ጥቆማ እንዲሰጡየሚደረጉት ለተሳትፎ እንጂ ተቀባይነትን የሚያገኘው የልጁ እናት ያወጡት ስም ነው፡፡ ምን አልባት ከተጠቆመው ስም ውስጥ በአጋጣሚ እናት ልታወጣ ካዘጋጀችው ስም ውስጥ አጃቢዎች ወይም ሽማገሌዎች ከጠቆሙ እናት ሊስማሙበት ይችላሉ፡፡ያም ሆነ ይህ ስም የሚያወጡት ልጅቷ በምታገባበት ዓመት ወይም ወር አልያም ቀን ውስጥ የተከሰተ ወይም የሆነ የተደረገ ነገርን በማስተዋል የልጅቷን ስም ከዛ ጋር በማገናኘት እንደሚያወጡ ኤቶ ደሊሶ ወልዴ እና ሌሎች መረጃ አቀባዩች በቡድን ውይይት ወቅት፡፡ ለሙሽሪት ከሚሰጡ ስሞች ከእነ ምክኒያታቸው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡

ለሙሽሪት ከሚሰጡ ስሞች መካከል ጥቂቱን አስታውሰው የአወጣጣቸውን ምክኒያት ያረዳሉ፡-

#### 4.2.1.10 ‹‹ሱዕማ ፉሹ-›› ለሙሽሪት የሚሰየም ስም

| የከምባትኛ ስም | ሥነ-ልሣን | የአማርና አቻ ፍቺ |
|---|---|---|
| 1. ኑራሜ | ንኡርኣሜ | ባለ ስኬት |
| 2. ኢተሜ | ኢትምኤ | ባለ ፍቅር |
| 3. ኬዕሚሴ | ኬኤምኢስኤ | ባለ ሰው አክባሪ |
| 4. አጫሜ | አጭኣምኤ | ባለ ትርፍ |
| 5. ጫፋሜ | ጫአፋአምኤ | እርጥበት |
| 6. ደምበሌ | ድአምብልኤ | የተንበሸበሸች |
| 7. አረሴ | አርአስኤ | - |

| | | |
|---|---|---|
| 8. አወኔ | አውንኤ | ተከታይ |
| 9. ዱታሜ | ድኡትአምኤ | - |
| 10. አያኔ | አይአንኤ | ጥሩ ገዳም |
| 11. ሉደጌ | ልኡድአግኤ | የመጀመሪያዬ |
| 12. ጫኪሴ | ጭአኪስኤ | ብርሃኔ |
| 13. ጫሚሴ | ጭአምኢስኤ | ድብርት አንሺ |
| 14. አሹሬ | አሾኡርኤ | - |
| 15. ሉባሜ | ልኡብአምኤ | ባለ ሙያ |
| 16. አሻሜ | አሽአምኤ | - |
| 17. ሎጃሜ | ልኡጅአምኤ | ጤዛ |
| 18. ኪበሜ | ክኢብአምኤ | ክብነሽ |
| 19. ሸሙቴ | ሽአምአትኤ | - |
| 20. ካጢሴ | ክአጥኢሴኤ | አረጋጊ አመቻች |
| 21. መናሜ | ምአንአምኤ | ባለ ብዙ ሰው |
| 22. ኢተሜ | ኢትአምኤ | ፍቅር |
| 23. ማሳሜ | ምአስአምኤ | በረከት ይላሉ |
| 24. ቦየቴ | ከአየትኤ | ለጋ |
| 25. አያኔ | አይአንኤ | ገድ ያለሽ |
| 26. ሂባሜ | ህኢብኣምኤ | ሞገስ ያለሽ |
| 27. ሎምባሜ | ልአምብኣምኤ | ባለ ክብር |
| 28. አሞሴ | አምኦስኤ | የእናቴ ልጅ |
| 29. አሹሬ | አሹኡርኤ | - |
| 30. ሪባቴ | ርኢብአትኤ | ተተኪ |
| 31. ጩፉሜ | ጭኡፍአምኤ | ባለምንጭ |
| 32. ሂሊሴ | ህኤልኢስኤ | ባለ ምቾት |
| 33.ዘራሬ | ዝአርአርኤ | አበባዬ |

| | | |
|---|---|---|
| 34. አርፍጩ | አርፍጭኤ | - |
| 35. ቦልጠኔ | ብኦልጥአንኤ | ኩራቴ |
| 36. ፊታሜ | ፍኢ.ትኣምኤ | ባለ ፍካት |
| 37. ዘርፋሜ | ዝአርፍአምኤ | ዘርፌ |
| 38. ሲጊሴ | ስኢ.ግኢ.ስኤ | አቀዝቃዥ |
| 39. ሰብርሴ | ሰአብርስኤ | አጸናኝ |
| 40. ሂለሜ | ህኤልኸምኤ | የተመቸሽ |

ከላይ የተጠቀሱትን ሰሞች ስናይ የሁሉም ይዘታቸው የሚያመሳስላቸው ነገር አለ፡፡ ይኸውም፡- የመጨረሻ ድምጻቸው የሁሉም በ “’ኤ” ሲያልቅ እናያለን፡፡ የዚህ ድምጽ ትርጉም “ባለ” ማለት ነው፡፡ ባለ ስንል ለምሳሌ በአማርኛ ባለ ብዙ ወርቅ፣ ባለ ብዙ ሀብት፣ ባለ ጥሩ ጸባይ፣ ባለ ትልቅ ዘር እንደሚበለው ዓይነት ትርጉም ያለው ነው፡፡ በቀጥታ ድምጽን ከቃሉ ጋር አያይዞ ባለ ጨምሮ ለመተርጎም ግን አስቸጋሪ ስለሆነ የስሙን ትርጉም ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ጠቅለል አድርገን ስናይ ስያሜ የሚሠጠው በወቅቱ ከተፈጠረው ነገር ወይም ሁኔታ ሊሆን ይችላል እናት ያስተዋሉትና በልባቸው የሞላውን ባለ እዚህ ነሽ የሚል ስያሜ ይሰጧታል፡፡

ወ/ሮ ኑራሜ አራሮ እና ሌሎች የቡድ አባላት ከስያሜዎቹ ውስጥ አስያየሙ እንዴት እንደሆነ ተጠይቀው ሲያብራሩ፡-

‹‹**ኑራሜ**›› **ባለ ስኬት** ማለት ሲሆን የልጁ እናት በዓመቱ ያሰቡት ወይም ያቀዱት የተመኙት ነገር መከናወን ሲያገኝ ይህ ስያሜ ይሰጣሉ፡፡

‹‹**ኢ.ተሜ**›› **ባለ ፍቅር** በጥላቻ የቆየ ቤተሰብ ስለ እሷ ጋብቻ ሲል ከታረቀ ሠላም ከወረደ

አንድ ሆኖ የእነዚህን የጋብቻ ሥርዓት ለማሳካት እየተረባረበ ሲያዩ ወይም ልጃቸው የባህሪይ ችግር የነበረበት ወደ ጥሩ የቀየረና ሠላማዊ ጸባይ ካመጣ ይህን የታዘቡ እናት ኢ.ተሜ ብለው ስም ያወጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ባህሪይ ሸጋ፣ ተግባቢ፣ ሁሉንም የምታቅፍ፣

ሁሌ ደስተኛ፣ የማትከፋ፣ ሰውን የማታስከፋ እንደሆነች ሲረዱ ከዚህ ባህሪዋ የተነሳ ሁሉም ዘመድ ፣ ጎሮቤት፣ ጓደኛ የሚወዳት አይነት ሴት መሆኗን ለመግለጽ የሚወጣ ስም ነው፡፡

‹‹**ኬዕሚሴ**›› **ሰው አክባሪ** አብራቸው ስትኖር ከዘመድ ጋር ስትቀላቀል ቤተሰብ፣ አባትናእናት፣ ጎረቤት ዘመድን በሙሉ እንድታከብር ሲፈለጉ መጀመሪያውኑ ስሟን ኬሚሴ ሰውአክባሪ ብለው ያወጡላታል ወይም ወላጆቿን እጅግ በጣም የምትወድና የምታከብር መሆኗን መረጃ ከደረሳቸው ይህንን ባህሪዋን እንድትቀጥል በሚል የሚሰጣት ስም ነው፡፡

‹‹**አጫሜ**›› **ባለ ትርፍ** ማለት ሲሆን ይህን ስያሜ የሚሰጣት የኑሮው የሠርጓ ስኬትና መትረፍረፍን ሲያዩ የሚያወጡት ስያሜ ነው፡፡

‹‹**ጫፋሜ**›› **እርጥበት** የጨፋሜ የስም አሰያየም በምታገባበት ሰሞንና በሠርጓ እለት ከባድ ዝናብ ከጣለ ይህ ስያሜ ይሰጣታል፡፡ ዝናብ ደግሞ ለሁሉም ሀብት እድገት መሠረት ነው የሚል እምነት ስላላቸው ኑሯዋ እንደዚህ መሬት እርጥብ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

‹‹**ደምበሌ**›› **የተምበሸበሸች** የተለያዩ ነገሮች በተለያየ መንገድ ለቤተሰቡ ሲጨመር ሲበዛ ወይም አዳዲስ እና ብዙ ጥሩ ነገር እቤት ውስጥ በተጨመረ ወቅት ያገባች ከሆነ ይህ ስያሜ ይሰጣታል፡፡

‹‹**አወኔ**›› **ተከታይ** ማለት ሲሆን በዕድሜ ያረጁ ከሆነ ተከታይ ምትክ እንደሆነች ሲሰማቸው የሚያወጡት ስያሜ ሲሆን በተጨማሪ በእሳቸው ሙያ የኑሮ ዘይቤ ማንኛውን ተግባር ተምራ የእሳቸው ዓይነት ኑሮ መምራት መፈለጋቸውን ለመግለጽ ሲፈልጉ የሚሰይሙት ነው፡፡

‹‹**አያኔ**›› **ገዳም** በሷ ሠርግ ምክንያት ብቻ የመጣ መልካም ነገር ወይም እሷን ልጃቸው ለማግባት ከተስማማ ወዲህ የሆነ አዲስ ያገኙት ነገር ካለ የእሷ ገድ ያመጣው ነገር ነው ብለው ለመግለጽ ሲፈልጉ አያኔ ይላሉ፡፡

‹‹**ሉደጌ**›› **መጀመሪያዬ (መሠረት)**ለመጀመሪያ ልጃቸው የመጣችውን ሙሽራ ወይም ሌላ የተዳረ ሳይኖር ሲቀር ከዚህ ቢፊት ወግ ማዕረግ ሳያዩ ቆይተው መጀመሪያ በቤታቸው የጋብቻ በኩራቸውን የመጣቸው ሙሽራ ሉደጌ ያሏታል፡፡

‹‹**ጫክሴ››ብርሃኔ** በተለያየ መንገድ ተቸግራው የቆዩ በማጣት ወይም ባለመዳር በሕይወታቸው እንዲሆንላቸው የሚፈልጉት ነገር ካላቸው ወይም ሳይሆንላቸው የቀረ ነገር

እስከ ዛሬ ያልተሳከ ከጋብቻው በኃለ ክፍተቶች ሁሉ ይደፍናሉ ምኞቴ ሁሉ ይሳካል የሚል እምነት ሲኖራቸው በዚህ ስያሜ ሙሽሪት እንድትጠራ ያደርጋሉ፡፡

‹‹**ጫሚሴ›› ድብርት ነሺ** ይህ ስያሜ ለሙሽሪት የሚሰጠው የልጁ ቤተሰብ የልጆች እጥረት ኖሮባቸው ልጆቻቸው ሁሉ በትዳር በስራ በሞት ለሆን ይችላል ተለይተዋቸው ቤቱ ጭር ብሎ የሚኖሩ ከሆነ እሷ መጥታ ይህንን ድብርት ትቀንስልናለች ብለው ሲያስቡ ይህንን ስም ይሰጣሉ፡፡

‹‹**ሉባሜ›› ባለሙያ** ሙሽሪት ወደ እነሱ ቤት ከመምጣቷ በፊት የሰሙትን የሙሽሪት የሙያ ዝና በጥልፍ፣ ዳንቴል በመስራት፣ ቤት በማጽዳት፣ የምግብ አሰራሯን ሁሉ ባለሙያ ነች የሚለውን ስሟን ሰጥተው ይህንን ሙያዋን እዚህ እንድትቀጥልላቸው መመኘታቸውን ለመግለጽ ይህንን ስም ይሰይሚታል፡፡

‹‹**ሎጃሜ›› ለምለም** ይህ ስም ከብዙ ጥሩ ነገር ጋር ያገናኙታል፡፡ከዝናብ፣ ከሀብት፣ ስርጓ ሲታሰብ የተሳካ ነገር በሰርጓ ልጃቸው ያገኘው አዳዲስ ሀብት ሲኖር ሁሉም ነገር ረድኤት ነው ለማለት ይሄንን ስም ይሰጧታል፡፡

‹‹**ካጢሴ›› አረጋጊ ወይም አመቻች** ይህ ቤተሰብ በብዙ ሰላም ማጣት ውስጥ ያለፈ ከሆነ ስለጋብቻው ሲታሰብ ብዙ ነገር እየተረጋጋ ወደ ሰላም፣ የሀብት መናጋት ከነበረ እየተስተካከለ የሄድ ከሆነ እነዚህ ሁሉ ሙሽሪት ከመጣች ይስተካከላል ወደ ነበረበት ይመለሳል የሚል ተስፋ ሰንቀው የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**መናሜ››ባለ ብዙ ሰው** የልጅ እጥረት የነበረባቸው ሙሽሪት ከመጣች እንደሚበዛላቸው ፣ ሁለተኛ የሙሽሪት ቤተሰብ አጎት፣ አክስት፣ የአጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ወንድሞች ብዙ ካሏት የብዙ ዘመድ ባለቤት ነሽና ባንቺ ምክኒያት ከብዙ ዘመድ ጋር እንቀላቀላለን ባለ ብዙ ዘመዶች እንሆናለን ሊኗት ሲፈልጉ ይህን ስያሜ ይሰጧታል፡፡

‹‹**ማሳሜ››በረከት** አንዲት ሴት እራሷ በረከት ነች የሚል እምነት አለ፡፡ይሄውም አንድ ልጅ

ሚስት ሲያገባ ከሚስቱ ማግባት ጋር ተያይዞ ልጆች ይወለዳሉ፣ ቤቱ ሁል ጊዜ ይሞቃል፣ የሚመጣ ዘመድ ይጨመራል፡፡ ሀብት ንብረት በፊት የሌሉ ነገሮች ይጨመራሉ፡፡ ይህ የተሰማት የልጅ እናት በረከት ብላ ትጠራለች፡፡

‹‹**ቦየቴ**›› **ለጋ** በእድሜ በጣም ትንሽ እንደሆነች የታዘቡ እናት የሚያወጡት ስያሜ ነው፡፡

‹‹**አያኔ**››**ገድ ያለሽ** በእሷ መምጣት ምክኒያት የሆኑ የተለወጠ ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ሲሆኑ ሲከሰቱ የሚሰጥ ስያሜ ነው፡፡በሌላ በኩል ልጃቸው በቅድመ ጋብቻ በፊት የሚካሄደው የወፏን የገደ ጥሩ መልዕክት አዳምጠ ትክክለኛ መሆንዋን አረጋግጠ እንዳገባት ሲሰማቸው እናት የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ሂበሜ**›› **ሞገስ ያለሽ** ይህ ስም ሲወጣ በሁለት አይነት እይታ ነው፡፡አንደኛው የልጅቷ ዘር ስመጥር ከሆነ የንጉስ ቤተሰብ በዘር ደረጃ ከፍ ያለ ስፍራ የሚሰጠው ከሆነ የቤተሰባው ክብርና ሞገስ ለመግለጽ ያወጣሉ፡፡ ሁለተኛው የልጃቸው የኑሮና የዘር ጥሩነት ሲሰማቸው ወደ እዚህ ቤት ከገባሽ ጀምሮ ስምሽና ክብርሽ ይጨምራል ለማለት ሲሉ ይህንን ስም ያወጣሉ፡፡ በሶስተኛው ደረጃ የእሷ ሁለመናዋ የሚያምር ከሆነ መልኳ ቁመናዋ ጸባይዋ አሟልቶ እግዚአብሄር ያደለሽ ነሽ ለማለት ሲፈልጉ ይህንን ስም ይሰጣሉ፡፡

‹‹**ሎምባሜ**›› **ባለክብር** ክብሯን ጠብቃ፣ ስሟን ጠብቃ የሰርጉ የወጉ ሁሉ ነገር ባህል የሚጠይቀውን ስጦታ ሁሉ ተሟልቶ ተፈጽሞላት ካገባች ብቻ የሚሰጣት ስም ነው፡፡

‹‹**አሞሴ**›› **የእናቴ ልጅ** በጣም የውስጥ ሰው ከአንድ ማህጸን እንደወጣ፣ በደም እንደተሳሰሩ፣ሰዎች ያህል የእኔ አድርጌ እንደማኖርሽ አረጋግጥልሻለው፤እደግፍላሻለሁ፤ ትደግፊኛለሽ፤ ታዝኚልኛለሽ፤ አዝንልሻለሁ፤ ጎኔ ነሽ፡፡ ተረዳድተን፣ ተሳስበን፣ አብረን እንኖራለን የሚል ሀሳብና ስሜት ሲሰማቸው የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ሪባቴ**›› **ተተኪ** አንድ ሰው ከጎናቸው በሞት ወይም በሌላ የስራ ምክኒያት ሊሆን ይችላል የሚታመኑበት የሚደግፋቸው ሰው ከጎናቸው ያጡ አሁን ግን ሙሽሪት ስትመጣ ይህ ባዶ የመሰለኝ ነገር ትሸፍንልኛለች ትተካልኛለች ብለው እምነት ሲጥሉ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ጩፋሜ**›› **ባለ ምንጭ** ወደፊት እንዲሟላ የሚፈልጉት ነገር በአእምሯቸው ሲመጣ እስቲ ለዚህ ነገር መሟላት መነሻ ትሆኚ ይሆናል ብለው ሲያስቡ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ሂሊሴ**›› **ባለ ምቾት** ሁሉም ነገር በተሟላና በተደላደለ ነገር ላይ የመጣች መሆኗን ለመግለጽ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከሀብታም ቤት ተንደላቃ ኖራ የመጣች መሆኗን ለሰውም ለእሷም ለማስተጋባት ሲፈልጉ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ዘራሬ**›› **አበባዬ** ጌጤ ደም ግባቴ ወበቴ ባንቺ ያምርብኛል የመጀመሪያ ወጌን የማይብሽ ፍሬ የማይብሽ ነሽ ለማለት ይህንን ስም ያወጣሉ፡፡

‹‹**ቦልጠኔ**›› **ኩራቴ** ከዚህ በኋል ነቀፌታዬ ሄድዋል አንገቴን ቀና ብዬ እሄዳለሁ፤ እኮራለሁ፤ አልሸማቀቅም፤ ባህሪሽም፣ ቁመናሽም፣ መልክሽም አኩሪ ነው ሊሏት ሲፈልጉ የሚሰጧት ስም ነው፡፡

‹‹**ፊታሜ**›› **ባለ ፍካት** ፍሬ የማይበትና የምበላበት ጊዜ ደረሰ ለማለት ሲፈልጉ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ዘርፋሜ**›› **ዘርፌ** ከልጆቼ አንድ አካልነሽ፡፡ በልጆቼ እና በዘመዶቼ ውስጥ ተጨምረሽልኛል፡፡ ወበቴ፣ ጌጤ፣ ደምግባቴ ነሽ ለማለት ሲፈልጉ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

‹‹**ሲጊሴ**››**አቀዝቃዥ** በሀዘን የቆዩ ቤተሰቦች ክፉ ክፉ ነገር ብቻ ሲያጋጥማቸው የነበሩ ሙሽሪት ከመጣች ሀዘን ይወጣል ብለው ተስፋ ሲያደርጉ ሌላው ጥላቻ ነግሶ የነበረበት ቤተሰብ የእርስ በእርስ ጥላቻን ባንቺ መምጣት ምክኒያት ወደ ደስታ ወደ ፍቅር ይቀየር የሚል ምኞት ለመግለጽ የሚያወጡት ስም ነው፡፡

በዚህ የስም አወጣጥ ማህበረሰቡ ያለፈውን ታሪክ ይገልጽበታል፡፡ያወሳበታል፡፡ ታሪኩ መጥፎ ከሆነ በሙሽራዋ ስም ያንን መጠፎ ታሪክ በሕይወታቸው እንዳይቀጥል በእሷ የሰርግና ጋብቻ ምክንያት አንድ አዲስ ምዕራፍ ይፈጠርልኝ ብለው ምኞታቸውን ሲገልጹበት እናያለን፡፡ ለምሳሌ ‹‹ሪባቴ›› ተተኪ ከዚህ በፊት ያጡትን ነገር እንደሚያገኙ ተስፋ ሲሰንቁ ይታያል፡፡ ከዚህ በፊት የሚፈልጉትን ያህል ልጅ እንኳን ካልወለዱ አሁን እንደሚበዙ እንደሚዋለዱ እያሰቡ ያንን ሀሳብ በሙሽሪት የስም ስያሜ ላይ ሲገልጹት

ይስተዋላል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘን ማየት የምንችለው የከምባታ ብዙ መውለድ የመፈለግ ባህል ነው፡፡ ነቀፌታ እንዳይመጣባቸው ሲከላከሉና ለውስጣቸው መልስ ያገኙ መስለው እንዲሰማቸው ሲፈልጉ ‹‹መናሜ›› ባለ ብዙ ሰው ብለው ስያሜ ይሠጣሉ፡፡ፍቅር ለሰው ልጁ ሀሴትን ከመስጠቱም በላይ ሰብአዊ ፍጡርን የመቆጣጠር ሀይል አለው፡፡ ለፍቅር የማይሸነፍ ማንም ሰው የለም፡፡ በፍቅር የማይደሰት ልብ አይኖርም፡፡የሙሽሪት ቤተሰብም ይህ ያስደሰታቸው ይመስላሉ፡፡ ስለ ልጅቷ የሰሙት ዜና ሁሉ ፍቅርና ደስታ ሲሰጣቸው ‹‹ኢተሜ›› ፍቅር ብለው ሲሰይሚት ይታያሉ፡፡

በተለያየ ማህበረሰብ የበረከት ምንጭ ናቸው ተብለው የሚጠቀሱት የተለያዩ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ለከምባታ የበረከት የማግኛ ምንጭ ነው ብለው የሚያስቀምጡት እንዱ ጋብቻ መሆኑን የሚያሳየን አንድ ወንድ ልጃቸው ሚስት ማግባቱ የቤቱ የሁሉም ነገር የማግኛ መነሻ ነው ብለው ማሰባቸውን የሚያሳየው የስም አወጣጥ ‹‹ማሳሜ›› በረከት የሚለው መሆኑን የመረጃ አቀባዩች ገለጻ ይህንን የሚያሳይ ነው፡፡

በከምባታ ብሄረሰብ ገድ አይቶ ማግባት ትኩረት የሚሰጠው ነገር መሆኑን በጥናቱ መነሻ ላይ ተጠቁሟል፡፡ ሙሽሪት በምትመጣበት ጊዜ የሚታየው የትኛውም የስኬት መነሻ ሌላ ነገር ተደርጎ አይወሰድም፡፡ ይልቁንም የልጅቷ ገድ ጥሩ ስለሆነ ነው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ ገድ ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ ታዲያ ስኬታቸውን ያስተዋሉ የልጁ እናት ‹‹ኢያኔ›› ጥሩ ገድ ያለሽ ብለው ስም ማውጣታቸው ከማህበረሰቡ ባህል ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡

የሴት ልጅ ባለሙያ መሆን በቤት ውስጥ ከሚጣልባትና ከምትወስደው ሀላፊነት አንጻር ባለሙያ መሆኗ ተፈላጊነቷን ያጎላዋል፡፡ ባለሙያነት ከእጅ ስራና ጥቅስ ከመጥቀስ የዘለለ የአእምሮ አስተዋይትን የሚይዝ ነው፤ ከቤት አያያዝ፣ ልጆችን በአግባቡ ማሳደግ፣ ምግብ መስራት፣ ባልን መንከባከብ፣ ከብቶችን በአግባቡ ማስተናገድ ብሎም የእርሻ ስራ ማገዝ በሴት ጫንቃ ላይ የሚጣሉ ተግባራት ናቸው፡፡ ታዲያ ይህ ተግባር ሁሉ ስኬታማ መሆን የሚችለው ሙሽሪት ባለሙያ ሆና ስትገኝ ነው ፡፡ በዚህም የስም አሰያየም ላይ የምናየው

የልጁ እናት ስም ሲያወጡ በእናቷ ቤት በነበረችበት ጊዜ ጥሩ ዝና የሰሙ ይመስላልና ይህንን ስያሜ ሲያጎናጽፏት አንድም ሙያዋን ትታ እንዳትመጣ ባለሙያ መሆንዋን የሰሙ መሆናቸውንና በስሟ ሊያረጋግጡት ስለፈለጉ ‹‹ሉባሜ››ማለታቸው ይህንኑ የሚያመለክት ነው፡፡

ወንድ ልጅ መውለድ ኩራትና ክብር ነው፡፡ብዙ ወንድ ልጅ የወለደች ሚስትም ትወደዳለች፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ሴት ልጅ ብቻ የምትወልድ ሚስት ከሆነች ባልየው ወንድ የምትወልድ ሴት ታስፈልገኛለች በማለት ሌላ ማየት ሊጀምር ይችላል በማለት ሚስት ስጋት ውስጥ ትገባለች፡፡ ሴት ብቻ የምትወልድ ከሆነ ይከፋታል፡፡ ደስተኛ አትሆንም፡፡ ወልዳ እንኳን በተኛችበት ምን ወለድሽ ብለው ቢጠይቋት ሴት ከማለት ብላ ሰው ነው የወለድኩት ትላለች፡፡ በዚህ የሀሳብ አገላለጽ የምንረዳው ምንም ብወልድ እናንተን አይመለከታችሁም፡፡ ሴት ብቻ ነው የምትወልደው ብላችሁ ለሌላው ለመንገር እንጂ ለሌላ ለምንም አይደለም፡፡ አያገባችሁም ፤ አልነግራችሁም አይነት መልስ ትሰጣቸዋለች፡፡ ስሜቷ እንደተጎዳ መረዳት ይቻላል፡፡ ታዲያ ‹‹ኪበሜ››ከበቡሽ ብለው እናት ስም ሲያወጡ እንዱ ብዙ ልጅ መውለድ መቻላቸውን ኩራታቸውን ሲገልጹላት ሁለተኛው በወንዶች መሀል የተገኘሽ ነሽ አይነት ውስጣዊ ስሜታቸውን በስሟ አሳበው ሲያስረዱ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ሴት መውለድ እና ወንድ መውለድ ያለውን የአመለካከት ልዩነት መረዳት ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ በማግኘትና በማጣት፣ በደስታና በሀዘን ፣በከፍታና ዝቅታ ውስጥ ማለፍ ግዴታው ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሰው ሁሉ በእነዚህ የሕይወት ተቃራኒ ኡደት ውሰጥ ያልፋል፡፡ ይህ ቤተሰብ ለሙሽሪት ስም ሲያወጣ ከነበረበት የሰላም መደፍረስ ለኑሮ ደስታ ይናፍቀው የነበረው ቤተሰብ ከዚህ መውጣትና በሰላምና በጥሩ ኑሮ ሕይወት ውስጥ መግባት ይፈልጋል፡፡ ማንም ቢሆን መጥፎ ሕይወት ፈልጎ አይገፋም እንዲጋፈጥ ግን ይገደዳል፡፡ ነገር ግን ነገ ሌላ ቀን ነውና ከእነዚህ ኑሮ አንድ ቀን እወጣለሁ ብሎ ያሰበ ቤተሰብ በሙሽሪት መምጣት ምክኒያት ከማይመች ሕይወት ወጥቶ ወደ ሰላሙ እመለሳለሁ ብሎ ተስፋ መሰነቁን በሙሽሪት ስም ላይ ‹‹ካጢሴ››አረጋጊ ነሽ በማለት ስም ያወጡላታል፡፡

ማህበረሰቡ ለጎሳዎች የሰጠው ደረጃ በውስጡ ያመኑበት የራሳቸው የሆነ ፍልስፍና አለው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡የንጉስ ቤተሰብ ማግባት ክብር ዝና ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅና ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ጎሳ አለ፡፡በተቃራኔው ዝቅተኛ ጎሳ ነው የሚሉትም አላቸው ማለት ነው፡፡ይህንን ስያሜ የሚሰጡ ሰዎች ከዚህ የከፍተኛነት ደረጃ ከተሰጠው ቤተሰብ መሆኑን ለሰርጉ እድምተኛ ለማሳወቅ ወደፊትም ሁሌም የክብር ስማቸውን እየጠሩ የትልቅነት ስሜት እየተሰማቸው እንዲኖሩ ሲፈልጉ ‹‹ሂበሜ››ባለሞገስ በማለት ስም መስጠታቸው ያረጋግጥልናል፡፡

በከምባታ የቆርሲሻ ባህላዊ የጋብቻ ወቅት ለሙሽሪትና ለሙሽራው ቤተሰብ ለአባት ለዘመድ የሚደረጉ ወጎችና ስርኣቶች አሉ፡፡ እነዚህ ማህበረሰቡ ያስቀመጣቸው ወግ ሁሉ ሚስት ያገባ ወንድ በሙሽሪት ስም አማካኝነት ይወደሳል፣ ይመሰገናል፡፡ ሙሽሪትም ሁሉም ስርኣት ተሟልቶላት ያገባሽ ነሽ፡፡ ልትኮሪ ይገባሻል አይነት መልዕክት ለማስተላለፍ ሙሽሪት‹‹ ሎምባሜ››ባለ ወግ ይሏታል፡፡

የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ሁሉም ነገር ተመቻችቶለት ቢኖር ይመርጣል፡፡ይህ ምኞት ተስተካክሎ የሚኖሩ ሰዎችም አሉ፡፡ በሀብት፣ በንብረት፣ በዝና በክብር የተሳካለት ሰው አነስ ያለ የኑሮ ደረጃ ላይ ካለው ሰው በልበ ሙሉነትና በኩራት መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ በተንደላቀቀ ኑሮ ላይ ያሉ ማንነታቸውን መግለጽ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ የሙሽራ ስም ላይ የምንታዘበው ይሄንኑ ነው ‹‹ሂሊሴ››ተንደላቃቂ ብለው ስም ሲያወጡ ይሄው ስሜት ሲያንጸባርቁ ነው፡፡

ከላይ የቀረቡት ስሞች የአወጣጣቸውን ሁኔታ ጠቅለል ተደርጎ ሲቀመጥ ከስሞቹ መረዳት የሚቻለው ህብረተሰቡ በስም አማካኝነት ከችግሩ መላቀቅ እንደሚፈልግ፣ ደስተኛ መሆኑን የወቅቱን ልምላሜ፣ ስኬት፣ ሀብት ወይም በረከት የሀዘን መርሻ፣ ምኞቱን፣ ተስፋ መሰነቅ፣ ለገድ ያለውን እምነት፣ ለጸታ ያላቸውን እይታ፣ ወጉን፣ ባህሉን፣ ማህበራዊ ደረጃን ወዘተ የሚያሳዩ ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ በክልሉ ለረጅም ዓመት የተለያየ አገልግሎት እየሰጠ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ታሪክ እንሚያስረዳን የአማርኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ቋንቋ

እንደሆነ በወሰነ በአጼ ቴድሮስ ዘመን መንግሥት ጀምሮ በመላው ሀገራችን ከጫፍ ጫፍ እንደሚነገርና በትምህርት፣ በሥራ ቋንቋነት ወዘተ ሰፊ ተግባር ሲያከናውን እስከ አሁን ድረስ አለ፡፡ ከዚህ የተነሣ በከምባታ ውስጥ ገጠር አከባቢ ድረስ ይህንን ቋንቋ የሚናገር ወይም የሚያዳምጥ ሰው አይጠፋም፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የአማርኛ ቋንቋ በከምባትኛ ቋንቋ የሙሽራ ስም አወጣጥ ሥርዓት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው ስሞችን እናያለን፡፡

| አማርኛ | የከምባትኛ ስያሜ | ሥነ-ልሣን |
|---|---|---|
| 1. አማረች | አማረቼ | አምኣርአች-ኤ |
| 2. አየለች | አየለቼ | አይልአች-ኤ |
| 3. በቀለች | በቀለቼ | ብኣቅአልአች -ኤ |
| 4. ዘነበች | ዘነበቼ | ዝኣንኣብች--ኤ |
| 5. አበራሽ | አበራሼ | አብአርኣሼ-ኤ |
| 6. ተስፋነሽ | ተስፋነሼ | ትአስፍኣንአሽ-ኤ |
| 7. ታገሡች | ታገሡቼ | ትኣግኣስአች-ኤ |
| 8. ለምለም | ለምለሜ | ልኣምልም-ኤ |
| 9. ከበቡሽ | ከበቡሼ | ክኣብአብኡሽ-ኤ |
| 10.አበበች | አበበቼ | አብአብአች-ኤ |
| 11.አስቴር | አስቴሬ | አስትር-ኤ |
| 12.ትዕግስት | ትዕግስቴ | ትዕግእስት-ኤ |
| 13.በላይነሽ | በላይነሼ | ብአልኣይነሽ-ኤ |
| 14.ሙሉነሽ | ሙሉነሼ | ምኡልኡንአሽ-ኤ |
| 15.እምነት | እምነቴ | ኤምነአት-ኤ |
| 16.ታመነች | ታመነቼ | ትአምአንአ-ች |
| 17.ታደለች | ታደለቼ | ትአድአልአች-ኤ |
| 18.ደሳለች | ደሳለቼ | ድአስአልች-ኤ |
| 19.መለሰች | መለሰቼ | ምአልአስአች-ኤ |
| 20.መሠለች | መሠለቼ | ምአስአች-ኤ |

| | | |
|---|---|---|
| 21.ጸደቀች | ጸደቀቼ | ጽኣድኣቅአች-ኤ |
| 22.ተረፈች | ተረፈቼ | ትኣርአፍአች-ኤ |
| 23.ዝናሽ | ዝናሼ | ዝእንአሽ-ኤ |
| 24.ጸጋነሽ | ጸጋነሼ | ጽኣግአንአሽ-ኤ |
| 25.እቴነሽ | እቴነሼ | እትኤንአሽ-ኤ |
| 26.ወርቅነሽ | ወርቅነሼ | ውአርቅንአሽ-ኤ |
| 27.ብርትኳን | ብርቱካኔ | ብእርትክአን-ኤ |
| 28.ደገፉች | ደገፉቼ | ድአግኣፍአች-ኤ |
| 29.ደረበች | ደረበቼ | ድአርኣብች-ኤ |
| 30.ምህረት | ምህረቴ | ምእህርአት-ኤ |
| 31.ውብዓለም | ውብዓለሜ | ውእብኣልኣም-ኤ |
| 32.ብዙነሽ | ብዙነሼ | ብእዝኡንአሽ-ኤ |
| 33.ብርሃንነሽ | ብርሃንነሼ | ብእርሃአንኣሽ-ኤ |
| 34.ደመቀች | ደመቀቼ | ድአምአቅኣች-ኤ |
| 35.አሰለፈች | አሰለፈቼ | አስአልአፍች-ኤ |
| 36.ገነት | ገነቴ | ግኣንአት-ኤ |
| 37.ሙሉነሽ | ሙሉነሼ | ምኡልኡንአሽ-ኤ |
| 38.ማርነሽ | ማርነሼ | ምኣርንኣስ-ኤ |
| 39.መቅደስ | መቅደሴ | ምአቅድአስኤ |
| 40.መሰረት | መሰረቴ | ምአስአርአትኤ |
| 41.ታረቀች | ታረቀቼ | ትኣርኣክአች-ኤ |

ከላይ የተዘረዘሩት ስሞች ለሙሽራ የሚሰጥ ስያሜ ሲሆን አጠቃቀሙ ግን የአማርኛ ስም ላይ የመጨረሻውን እ- ወደ ኤ በመቀየር የሚጠቀሙት ስያሜ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ባህላዊ የስም ስያሜ መጨረሻ ላይ ያለው ኤ- በአማርኛው ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ ስሞች መጨረሻ ላይ የምናስተውለው ኤ- እዚህ ጋ ገብቶ እናያለን ፡፡ ነገር ግን በከምባተኛ ላይ የሚሠጠውን ትርጉም መስጠት አልቻለም፡፡ በከምባትኛ ኤ-ባለ የሚል ትርጉም እንዳለው አንስቻለሁ፡፡ እዚህ ጋ ግን ‹‹ኤ›› ትርጉም

አልባ ነች ለምሳሌ፡- አማረች “አምአርኧች ” የሚለውን ስም በአማርኛ አማርሽ ቆንጆ ሆነሽ የሚል ትርጉም ሲኖረው አማረቼ አምኣርኧች-ኤ ግን በአማርኛው ቢሆን በከምባትኛው ትርጉም የለውም፡፡ የማቆላመጫ ድምጽ ነው ብለን እንዳንወስድ መሆን የነበረበት አማረችዬ ነው፡፡ “ኤ” የማቆላመጫ ድምጽ ትሆናለች ፡፡ምክኒያቱም የአማርች ስያሜን በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለዚህ አማረቼ መጨረሻ ያለው ‹‹ኤ››በተጽኖ የገባ እንጂ ለማቆላመጥ የገባ አይደለም ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው በቅጥያ የገባ ድምጽ አይደለም፡፡ የመጨረሻውን ድምጽ ከ እ -ወደ ኤ የመቀየር ሂደት እንጂ፡፡ ይህ ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በሆነው በከምባትኛ ላይ እ ድምጽ ስለ ሌለ ወደ አቅራቢያ ወደሚገኘው ወደ-ኤ- የመቀየርና የመጠቀም ሂደት ነው፡፡የሂውም፡- ኧ-እና እ ድምጽ በከምባትኛ ቋንቋ አናባቢ ውስጥ ስለሌሉ እ- የምትለውን ድምጽ ትንሽ ቅርበት ያላት “ኤ” በመሆኗ ወደ እሷ ቀይሮ የመጠቀም ሂደትን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ የስያሜ አሰጣጥና አጠቃቀም ላይ የምናስተውለው ይህንኑ ነው፡፡ እዚህ ላይ መገንዘብ የምንችለው በስም አወጣጡ ላይ የማህበረሰቡን አመለካከት የምናይበትና በስሙ ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ ላይ ያሳረፈውን ተጽዕኖ ማየት እንችላልን፡፡

ሁለት ቋንቋዎች በአንድ ተናጋሪ በሚነገሩበት ወቅት የአንዱ ቋንቋ የአነጋገር ስርኣት ወይም ቅደም ተከተል ሳይታሰብ በሌላኛው ቋንቋ አጠቃቀም ወቅት ሊከሰት ይችላል፡፡ በአብዛኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርኣት በሁለተኛው ቋንቋ ስርኣት ውስጥ ሲገባ ይስተዋላል፡፡በዚህ ጊዜ የሁለተኛ ቋንቋ የአጠቃቀምና የአነጋገር ስርኣት ሲያስለውጠው ይታያል፡፡በዚህ ክስተት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስነ ልሳናዊ ቅንጣቶች በሁለት ቋንቋ ውስጥ ጣልቃ ሲገቡ ይታያል፡፡አብዛኛውን ጊዜ ጣልቃ ገብ የሚሆኑ ስነ ልሳናዊ ዘርፎች ድምጾች፣ ሰዋስዋዊ አጠቃቀሞችና ቃላት ናቸው፡፡ በዚህ የሙሽራ ስም አወጣጥ ላይ የሚስተዋለው ይሄው ነው፡፡

የቋንቋው ጣልቃ ገብነት ለሙሽራው በተሰጡ ስሞች ላይ በስሙ መጨረሻ ‹‹ኤ›› በማስገባት የአማርኛውን ፍቺ ትርጉም አልባ አድርጎታል፡፡ ትርጉም አልባ የሚሆነው በቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግ ስናይ ነው፡፡ ለማህበረሰቡ ግን በአማርኛው የሚሰጠውን ፍቺ የያዘ ትረጓሜ እንደሚጠቀሙበት ማስታዋል ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን የአፍ መፍቻ ቋንቋው

ጣልቃ ገብነት ቢኖርም ስም አውጪዎች የራሳቸውን ስሜት መግለጻቸውን አላገደውም በእነሱ አገላለጽ በስሞቹ ውስጥ ያለው አንድምታ ከላይ በከምባትኛ ስሞች ላይ ያስታዋልነው አመለካካት፣ እምነት፣ ጾታዊ እይታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ባህል እንደሚገልጹ በከምባትኛ ስሞች ላይ የተሰጠው ትንታኔ እዚህም ላይ የሚሰራ ነው፡፡

የስም አወጣጥ ስርአት ከተጠናቀቀ በኋላ የሠርጉ ማለቂያ ወቅት የሽማግሌዎች ምርቃት ይደረጋል ፡፡(ምልከታ ሚያዝያ 4/ 2010)

- ኢላን ቁልቱን            በልጅ ታሸንፍ
- ጎንድ ጎጌሳ ኢልቱን        የጉንዳንን አጀብ ያህል ልጅ ትውለድ
- ሁጄን ኡራጌን ቁሉ         በሥራ አሸናፊ ሁን

ከላይ የተገለፀውን የምርቃት አሰጣጥ ስናይ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መስመሮች አንድን ሀሳብ አጠናክረው የሚገለጹ ናቸው፡፡ ‹‹ኢላን ቁልቱን›› በልጅ ታሸንፍህ፣ ‹‹ጎንድ ጎጌሳ እልቱን›› የጉንዳን አጀብ ያህል ትውለድ፡፡ ይህ ሀሳብ ከፍተኛ የሆነ ልጅ የመውለድ ፍላጎትን የሚያንፀባርቅ ከመሆኑም በላይ በመጀመሪያ የጋብቻ እሳቤ በከምባታ ብሔረሰብ ምን እንደሚመስል በተነሳ ወቅት ጋብቻ ለከምባታ ዘር መጨመር፣ወገን ማብዛት ነው የሚሉትን የመረጃ ሰጪዎችን ሀሳብ የሚያረጋግጥና የሚያጠናክር ሀሳብ ነው፡፡ ይኸውም መወለድ ያለበት የልጅ መጠን ከፍተኛ እንዲሆን ለመመኘት ነው፡፡ የጉንዳን አጀብ ያህል ልጅ ትውለድ ማለት በጣም ብዙ ልጅ እንዲወለድ መፈለግ የማህበረሰቡ ፍላጎትና እምነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ‹‹በልጅታሸንፍህ›› የሚለው ሀሳብ የፍላጎትህን ያህል ልጅ ብቻ ሳይሆን ከፍላጎትህ አንተ ከመጠንከው ቁጥር በላይ ልጅ ትውለድልህ የሚል እንድምታ ያለው ምርቃት ነው፡፡ ‹‹ ሁጄኒ ኡራጊኒ ቁል›› በሥራ አሸናፊ ሁን የሚለው ምርቃት ቤትህን፣ ባለቤትህን፣ ልጆችህን የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ አሟልተህና አርክተህ ማኖር በምትችለው ልክ ሥራ፣ ጠንክር፣ በርታ፣ ባጠቃላይ ኑሮን አሸንፈህ መኖር ይገባሀል የሚል ሀሳብ የያዘ ሲሆን ጠንክሮ መስራት ኑሮን ለማሸነፍ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ ያሰረዳል፡፡

ከዚህ በኃላ ቤተሰብ የስጦታ ዕቃዋን ቆጥረዉ ሙሽራዋን ለሚዜዎቹና ለሽማግሌዎቹ ያስረክቧታል፡፡

**አጃቢዎች የሠርጉ ሥርዓት ሲጠናቀቅ የሚዘፍኑት ዘፈን፡-**

| | | |
|---|---|---|
| አና አና… አባት | - ኣቼ ኣቼ …. | እማማ እማማ እማማ |
| ኢሩ ሀዋሩታ | - ኢሩ ሀዋሩታ | ሰአቱ መሸቷል |
| ማጣናት ድኑታ | - ማጣናት ዲኑታ | ፈረሷ አንካሳ ናት |
| መኒት ቄረታ | - መኒት ቄራታ | ቦታው እሩቅ ነው |
| ሀማሙታ አሲዬኔ | - ሀማሙታ አሲዬኔ | ሙሽሪቱን ስጡን |

እናትና አባትን እየጠሩ አንሂድ ሸኙን የሚል ቅስቀሳ ሲሆን ለቅስቀሳቸው ማሳመኛ ሲያቀርቡ እናያለን ‹‹ እሩ ሀዋሩታ›. ሰዓት መሸቷል ‹‹ማጣነት ድኑተ›› ፈረስዋ አንካሳ ናት፡፡ የሚለው ሀሳብ ፈረስዋ እግሯን ማንከሷን ሳይሆን በፍጥነት ሙሽሪት እንድትሰጣቸው ያቀረቡት ምክንያት ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ለአንዲት ሙሽሪት መጓዣ አለ የተባለ ምርጥ ፈረስ ነው የሚዘጋጀው፡፡ ከዚህ የተነሳ ቶሎ ለመሄድ ያቀረቡት ምክንያት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ሙሽራዋ ከተሰጠቻቸው በኋላ መጀመሪያ በሴት ፈረስ/ባዝራ ቀጥሎ በበቅሎ ላይ ያስቀምጧታል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት 1ኛ/ ፈረስ የምትወልድ ስለሆነች ዉለጂ እንደማለት ሲሆን በበቅሎ የሚያስቀምጡበት በምትዳርበት ቀን ኮሶ "ጤሙ" ስለምትጠጣ ደጋፊ ሲለሚያስፈልጋት በቅሎ በአቅም ከፈረስ ይልቅ ጠንካራ ከመሆኗ የተነሳ የሙሽራዉ ሚዜ ስለሚፈናጠጥ ሁለት ሰዉ የመሸከም አቅም ስላለዉ ነዉ፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ በበቅሎ ቀድሞ የሚያስቀምጡት በቅሎ መሃን ስለሆነች ነዉ፡፡ ወደ ሙሽራዉ ቤት ሲደርሱ በቤት ደጅ ላይ ሣር ባለበት ኬሻ "ኤንዴቤሮ" ተነጥፎ ሙሽሪትን ያስቀምጡና ወንድና ሴት ህፃናትን በታፋዋ ላይ ወንድና ሴት ውለጂ እያሉ ያስቀምጣሉ፡፡ ሁለት የተቆላ ቡና ለሙሽራዉ ይቀርብና አኝኮት ተነጥሮ በቀረበዉ ቅቤ ተጎመጥምጦ በጡቶቿ መሃል እትፍ እትፍ ይላል፡፡ ይህም ከዛሬ ጀምሮ አንድ ነን አንለያይም የማለትና ቃለ-መሃላ መግቢያ ምልክት ነዉ፡፡ በእግሯ ጣት ላይም ትኩስ ወተት ይደፋሉ፡፡

### 4.2.1.11 ጎጨ አፉ ሴራ›› በር የመያዝ ሥርዓት

ሙሽረውና ሙሽሪት ቤት ሲገቡ የቤቱ በር የሙሽራዉ እህት እንዳይገቡ ትይዛለች፡፡ ይህን እንደምክንያት የሚነገረው  ወንድሟ ካገባ ቦኋላ ፍቅሩ እንደሚቀንስና ወደ ሚስቱ እንደሚያደላ ለማመልከት ነው የሚባል እንድምታም አለ፡፡

አጃቢዎች ሙሽራዋን ይዘው ወደ ቤት ለመግባት ሲመጡ ቤት አናስገባም እያሉ በሩን በሁለት እጃቸው ዘግተው የሚይዙ አሉ፡፡ በመጀመሪያው መግቢያ በር የሙሽራው እህት (ታላቅ ወይም ታናሽ እህት) በሩን ትይዛለች፡፡ አጃቢዎች እየጨፈሩ በላይዋ ላይ በሩን ሊያስለቅቋት ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን በምንም አይነት በሩን አትለቅም፡፡ በሩን የምትለቀው ከሚዜዎቹ መካከል የሚበቃትን ያህል ገንዘብ ከሰጧት ነው፡፡ ይህ የሚሰጣት ገንዘብ 100 ብርና ከዛም በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ ገንዘብ አገልግሎት ሙሽራዋ በጫጉላ ቤት በምትቆይበት ሰዓት ምግብ እያበሰለች ሙሽራዋን ለመንከባከብ የሚሆን ገንዘብ ነው፡፡ቤቱ ሁለት በር ይኑረው ሶስት በር ይኑረው በበሩ ልክ የሙሽራው እህቶች ከሌሉ ሙሽሪትን በቅርበት ሆና ልትንከባከብ የምትችል ሴት በሩን ትይዛለች፡፡ በበሩ ልክ የቆሙትን ሴቶች ገንዘብ እየሰጡ ማስለቀቅ የሙሽራው ሚዜዎች ግዴታ ይሆናል፡፡አንዳንዴ ሚዜዎች በርከት ያለ ገንዘብ መስጠት ካልቻሉ በጭፈራ መልክ እያደረጉ ጠጋ ብለው በሩን ለያዙ ሴቶች ሚስጥራቸውን እየነገሩ በሩን እንዲለቁላቸው ይለምኗቸዋል፡፡ የገንዘቡን መጠን ይቀንሱላቸው እንጂ ምንም ሳይሰጣቸው የመግቢያውን በር አይለቁላቸውም፡፡ እንደምንም ብለው በሩን ካስለቀቁ ነው ልጅቷን ወደ ጫጉላ ቤት የሚያስገቧት ፡፡

**በሩን የያዙት ሰቶች የሚጫወቱት ጫወታ**

| **መገኛ ቋንቋ** | **አቻ ፍቺ** |
|---|---|
| ገሪት ዮዬ ገሪት ዮዬ | እውነት አለን እውነት አለን |
| ጃል ዋሉን ጃል ዋሉን | ሚዜው ይምጣ ሚዜው ይምጣ |
| ገሪት አሱኒ ገሪት አሱኒ | እውነታችንን ይስጠን ይስጠን |

| | |
|---|---|
| ዮባ አሰንቃማባ አሰንቃማባ | በፍጹም በሩን አልሰጥም አልሰጥም |
| ዮባ ገፈራምባ ገፈራምባ | በፍጹም በሩን አልለቅም አልለቅም |
| ከኒን ገልታ ከኒን ገልታ | እዚሁ ያድራሉ አዚሁ ያድራል |
| ሽቱት ውሀበይንዶ | ሽቶ ውሀ ነው |
| ጃሉስ ቡጢማንዶ | ሚዜው ደሀ ነው |
| ወጉ ዮኔ ወጉ ዮኔ ሸለሜኖኔ | ወግ አለን የምንሸለመው |

ከላይ ያለውን ሃሳብ ስናይ … እውነት አለኝ …ሲሉ ባህሉ ወጉ የሚያስገድድ ስጦታ አለኝ ይህ ስጦታ ወንድሜ ከዚህ በኋላ ሚስቱን ነው የሚወደው ከዚህ የተነሳ ለሙሽሪት የጫጉላ ቤት እንክብካቤ ላድርግላት ብዬ ገንዘብ ብጠይቀው አይሰጠኝም፤ ባለመስጠቱ ምክንያት ሳትሞሸር ብትቀር እወቀሳለሁ፤ ሚዜዎቹ ይህን ወጉ ያስቀመጠልኝን ስጦታ ስጡኝና ስራዬን ልስራ ካልሆነ እዚሁ ቆማችሁ ማደራችሁ ነው፤ በፍጹም በሩን አለቅም ማለቷ ነው፡፡

ሚዜው ድሀ ነው… ይህ ቅኔ የሚወጣው ያሰበችው ስጦታ ሲዘገይባት ነው፡፡ እስካሁን ዝም ብላችሁ የምታስጮሁኝ ገንዘብ ሳይኖራችሁ እንዴት ከወንድሜ ጎን ሚዜ ነን ብላችሁ ለምን ቆማችሁት ወይስ የከምባታን ወግ አታውቁም አይነት መልዕክት እያስተላለፉ ያቀነቅናሉ፡፡ ገንዘቡን እስክትሰጡኝ በሩን መያዜን እቀጥላለሁ ማለታቸው ነው፡፡

#### 4.2.1.12 ‹‹ቆራ ሂሩ›› ወገብ የመፍታት ሥርዓት

ጫጉላ ቤት እንደገባች የመጀመሪያው ነገር ‹‹ቆራ ሂሩ›› ወገብ የመፍታት ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ የወገብ መፍታትን ሥርዓት የምታካሂደው የሙሽራው እናት(የባል እናት) ናት፡፡ ወገብ መፍታት ማለት ሙሽሪት ከዚህ በፊት ያልወለደች ስለሆነ ከዚህ በኋላ ውለጂ ተብሎ ማህፀኗን እንደመፍታት ይወሰዳል፡፡

#### 4.2.1.13. በልሸተ- የአክብሮት ጥሪ

‹‹በልሸት››የአክብሮት ጥሪ በጫጉላ ቤት ሙሽሪት የምትሰለጥነው ባህላዊ ሥርዓት ነው፡፡

ከሠርጓ ማግስት ጀምሮ ሙሽሪት መጥራት የሌለባትን ቃላት የልጁ አክስት (የአባት እህት) ‹‹አደት›› ታስተምራታለች፡፡ የልጁን አባት ስም ወንድም የባሏን አጎቶች ስማቸው እስከ አያታቸው ድረስ መጥራት በባህሉ አይፈቀድም፡፡ ስለዚህ የባሏን ዘመዶች እስከ አያታቸው ድረስ ያለው መነሻ ድምጽ መጥራት እንደሌለባት ይነገራታል፡፡ ይህ በከምባታ‹‹ በልሸት›› ይባላል፡፡

በልሸተ ማለት አንድን ሰው መከበሩን ለመግለጽ ሲባል ስሙንና በስሙ የሚጀምሩ ማንኛውንም ነገር በሌላ ጥሪ ቀይሮ መጥራት ማለት ነው፡፡ ሙሽሪት የባሏን ዘመዶች ከሠርጓ ማግስት ጀምሮ ማክበር ይጠበቅባታል፡፡ ስለ በልሸት የአክብሮት ጥሪ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው አመለካከት ስንመለከት የባልን ዘመድ ማክበር የሚጀመረው ስሙን በቀጥታ ባለመጥራት ነው፡፡ በቀጥታ ስሙን ወይም በስሙ የሚጀምሩ ማንኛውንም ቃላት መጥራት አለማክበር ወይም አቅልሎ ማየት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የትኛውንም በአማርኛ ለአክብሮት የምንጠቀማቸው ከስም ቀድመው የሚመጡ ጋሼ ደበበ ፣ ጋሼ አበበ አባት ኤኬሌ ብለው ከስሙ በፊት መጠቀም ለከምባታ ማህበረሰብ ለባል ቤተሰቦች እንዲሁም ዘመዶች ፈጽሞ ነውርና የማይፈቀድ ባህል ነው፡፡ ይልቁንም ከስም ቀድሞ የአክብሮት ቃላትን ተጠቅሞ ስምን መጥራት ይቅርና ስሙ በመነሻ  ድምጽ የሚጀምር ቃል  የትኛውንም ቃላት መጥራት በባህሉ አይፈቀድም፡፡ ይህም እንደነውር ይወሰዳል፡፡ የባሏን ዘመዶች የማታከብር ናት ተብላ ትወገዛለች፡፡ ስለዚህ ይህንን የባሏ አክስት /የባል የአባት እህት/ የአማቾቿን ስም ጥሪ ቀይሮ ማክበር ግዴታዋ ይሆናል፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚገባ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት እያለች የባሏ እህት እንዴት እንደምታስተምራት ወ/ሮ ኑራሜ አራሮ ሚያዚያ 28 2010 ዓ/ም በዚህ መልክ ይገልጻሉ ፡፡ የባል አባት ስም ‹‹ወብሎ›› ፣ የባል አያት ስም ‹‹አናጎ›› ፣ የባል ቅድመ-አያት ስም ‹‹ሳኬ››  እነዚህ ስሞች እንዴት እንደሚቀየሩ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ ‹‹ወብሎ›› የሚለው ስም  የሚጀምረው በ ‹‹ወ›› ነው፡፡በ‹‹ወ›› ድምጽ የሚጀምሩ ቃላት እንዴት ይቀየራሉ?

አቀያየሩን ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ‹‹ወብሎ›› ስም አቀያየር ስርኣት

| የማይጠሩ ቃላት | አማርኛ አቻ ፍቺ | የተቀየሩ ቃላት | አማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1. ወዘና | ልብ | ፉሊኢኖ | መተንፈሻ |
| 2. ወአ | ውሃ | ዳዳሞ | መጠጥ |
| 3. ወዕቼ | ጥጃ | ኤምባ | የጥጃ ስም |
| 4. ወማ | ንጉስ | ዳና | ዳኛ |
| 5. ወጋ | ዓመት | ኑር | አምና |
| 6. ወቃ | መንገድ | መረሜኖ | መራመጃ |
| 7. ወሽቼ | ውሻ | ቲተሜ | የውሻስም |
| 8. ወዱ | ድሮ | ኤጂ | ጥንት |
| 9. ወጁ | ነጭ | አዙትአጉደኖ | ወተት የሚመስል |
| 10.ወሉት | ቁጠር | ቁጥራ | ቁጥር |
| 11.ወና | በፊት | ከኒችብሬ | ከዚህ በፊት |
| 12.ወሮዶ | ወደታች | ሙጌና | ቁልቁለት |
| 13.ወጠምቤት | አርጩሜ | ኦላንቼ | መግረፊያ |
| 14.ወሪቼ | እባብ | ከረኖ | ነዳፊ |

ከላይ የተቀየሩ ስሞችን የአቀያየሩን ስርዓት ስናይ ስሙ ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር የተቀየረ አለ፡፡ ለምሳሌ፡-

ወቃ መንገድ መረሜኖ መራመጃ

ወሪቼ እባብ ከራንቼ ነዳፊ

ወማ ንጉስ ዳና ዳኛ

ወጠምቤቼተ አርጩሜ ኦሌኖ መግረፊያ

የመጀመሪያው መንገድ ለመራመጃነት ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ ያገለግላል፡፡ ስለዚህ መንገድን የተከለከለ ቃል ስለሆነ መራመጃ ተብሎ ከሚሰጠው ግልጋሎት አንጻር ተቀይሯል፡፡ ሁለተኛው የንጉስ ተግባር አንዱ መዳኘት ነው፡፡ ንጉስ ወደ ዳኛ ተቀይሯል፡፡

ሶስተኛው ምሳሌም ተመሳሳይ ነው፡፡ የአርጩሜ ተግባር መግረፍ ነው፡፡ስለዚህ ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር የተቀየሩ ይመስላል፡፡

**ስሙ ካለው ተጨማሪ ስም አንጻር የተቀየረ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወሽቼ | ውሻ | ቲተሜ | የውሻ ስም |
| ወኣ | ውሃ | ዳዳሙ | ውሃ |
| ወና | በፊት | ከኒች ቢሬ | በፊት |
| ዋሉ | መምጣት | አሜቱ | መምጣት |

ውሻ የወል ስም ሲሆን ቲተሜ የአንድ ውሻ የግል ስም ነው፡፡ የውሃ ሌላ ተጨማሪ ስሙ በከምባትኛ ዳዳሞ ነው፡፡ ወኣ ውሃ ነው ዳዳሙ ውሃ ነው፡፡ ሶስተኛውም ምሳሌ እንዲሁ ተመሳሳይ ነው፡፡

**መልኩን በመግለጽ የተቀየረ ቃል**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወጁ | ነጭ | አዙት አጉደኖ | ወተት የሚመስል |

የወተትን ከለር በመግለጽ ነጭ ወተት የሚመስል በሚል ተቀይሯል፡፡

**‹‹አናጎ›› የሚለውን ስም አቀያየር**

| የማይጠሩ ቃላት | ትርጉም | የተቀየሩ ቃላት | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| 1. አጉ | መጠጣት | ኮሻሁ | ግጥም ማድረግ |
| 2. አንገተ | እጅ | ኤጀተ | መያዝ |
| 3. አዕሉ | መታጠብ | ጣጦጬ | መለቅለቅ |
| 4. አፉ | መያዝ | ኡሉ | መንካት |
| 5. አፉዕሉ | መቀመጥ | ገፍዩ | አረፍማለት |
| 6. አለሱ | ስንዴ | ዊጠተ | እህል |
| 7. አስዕሙ | መቃኘት | ጡዱ | መመልከት |
| 8. አረብተ | ምላስ | ጠዋሙ | ነገረኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9. አና | አባት | መንቹ | ሰውዬ |
| 10. አፉ | መያዝ | ተፍአኡ | መንካት |
| 11.አወኑ | መከተል | ዘክሱ | መከተል |
| 12. አሉዱ | ወደላይ | ብዜና | ሰሜን |
| 13. አባስማ | መጥረጊያ | ፊሊስተ | መጥረጊያ |
| 14. አንጀነት | የሚሸት | ፎሸ | ሽታ |
| 15. አባ | ትልቅ | ጌዴላ | ትልቅ |

‹ሳኬ ››የሚለውን ስም ላለመጥራት በቅየራ የምትጠቀማቸው ቃላት

| <u>የማይጠሩ ቃላት</u> | <u>ትርጉም</u> | <u>የተቀየሩ</u> | <u>ትርጉም</u> |
|---|---|---|---|
| 1. ሰኑተ | አፍንጫ | እንፌኖተ | መናፈጫ |
| 2. ሱሉሙተ | ግደር | ደጄተ | የጊደር ስም |
| 3. ስጋ | ቀዝቃዘ | ጫላ | ያልሞቀ |
| 4. ሴሬኬቱ | መመርመር | ቆርሙ | መመርመር |
| 5. ስነተ | ሲኒ | ፈንጀነት | መጠጫ |
| 6. ሶሮ | እርቦ | ኬናንቹ | መስፈሪያ |
| 7. ሰዊታ | ሀሳብ | መላ | መላ |
| 8. ሰዳ | የሳር ዓይነት | ቆርጡ | ሰርዶ |
| 9. ሰጠራ | አውራዶሮ እናት | ኩኪኔ | የአዉራዶሮ እናት |
| 10.ሰና | ወቅት | ጃተ | ጊዜ |
| 11.ሰንፉ | ማበጠሪያ | ደጉድተ | ሰፌድ |
| 12.ሳማ | ዕጣ | ቆዳ | ድርሻ |
| 13.ሱሳ | ቡቱቶ | ጎፎኦድሻተ | ያለቀልብስ |
| 14.ሱጡ | ማስቀመጥ | ማጠቁ | መደበቅ |
| 15.ሱሉ | ማነቅ | ለንጉ | ማነቅ |
| 16.ሶዝማ | ጠዋት | ገሲማ | ማለዳ |

ከቃላቱ መረዳት የሚቻለው ስሙን ላለመጥራት በምታደርገው ሽሽት የተለያየ የአቀያየር ስርኣት እንጂ ወደ አንድ ድምዳሜ ሊያደርሰን የሚችል የአቀያየር ስርዓት አይታይም ፡፡

ከአቀያየሩ ስርዓት የምንገነዘበው ዋናው ቃላቱ ወይም ድምጽ ከምን ወደ ምን ተቀየረ የሚለው ሳይሆን በድምጽና በቃላት መቀየር ምክንያት አክብሮት በህበረሰቡ ውስጥ እንዴት እንደሚካሄድ ማየት ይቻላል፡፡ ሌላው ከድምጽ ጀምሮ እስከ ንግግር ድረስ ቋንቋ ዲስኮርስ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ቤሂረሰብ ላይ የምናየው ይሄንኑ ነው፡፡ ሙሽሪት የማይገቡ ድምጾችን እየቀያየረች ስትጠራ ድምጽ መቀየር ፈልጋ ሳይሆን በድምጹ መቀየር ምክንያት የሚከሰተው የአክብሮት ተግባር ነው፡፡ አድማጩም የስሙ ድምጽ የተቀየረው የአክብሮቱን መልክት አጣጥሞ ይቀበለዋል፡፡

#### 4.2.1.14 ኢርፉት - ስጦታ

የልጁ አባት፣ እናት፣ አጎት፣ አክስት እና ሌሎች ዘመዶች ድግስ ደግሰው ስጦታ የሚሠጡበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት የሚፈጸመው ሙሽራዋ ከጫጉላ ቤት ወጥታ ከሌላ ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅላ መኖር እንድትጀምር ለማድረግ የሚካሄድ ነው፡፡ የጫጉላ ቤት ቆይታ ከሠርጓ ቀን ከአንድ እስከ ሁለት ወር ልትቆይ እንደምትችል አቶ ስምየን አያኖ 02/09/2010 ዓ.ም ያስረዳሉ፡፡ ቀጥለውም በጫጉላ ቤት ስትኖር ከባሏ ውጪ ማንም ሰው አያያትም ምግብ እንኳን ዘመዶቹ እጃቸውን ብቻ እያሾለኩ ይሰጧታል እንጂ አያዩአትም፡፡ ከጫጉላ ቤት የቆይታዋ ጊዜ ሲያበቃ ከቤተሰብ ጋር እንድትቀላቀል ለማድረግ ዝግጅት ተደርጎ ሥጦታ ይሰጣታል፡፡ ይህ በከምባታ ‹‹ኢሪፉታ›› ይባላል፡፡

ምግብ ከተበላ  ከተጠጣ በኋላ የስጦታ አሰጣጥ ሥርዓቱን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡- የልጁ ቤተሰቦች እንደየአቅማቸውና ፍላጎታቸው ስጦታውን ይሰጣሉ፡፡

> “ቴሱ ኢርምፋምተ ጄቹ ወና አኑ ዮስሪች ቅጠንሴ ኢሪፉታ አሰኖ ”
>
> “አሁን ስጦታ የሚሰጥበት ጊዜ ነው አባት ካላው ሀብት ለመስጣት የወደደዉን ስጦታ ይሰጣል”

“አና›› አባት ላሉታ አሴንኬ ዓመታ አቢሱ አሴንኬ፣ አና አቢስ፣ አሴንኬ ኢልቱ፣ ስርቱ ከኒች ዘኪን ቦዮ ዎእቹ አሴንኬ፣ “ፍሬን ሰጠሁሽ፣ እናትን ማክበር  ሰጠውሽ፣ አባትን ማክበር ሰጠውሽ፣ ጎረቤት ማክበር ቤተሰብ ዘርን ማክበር ሰጠውሽ  ውለጂ ተዋለጂ በመጨረሻ የቦዮ የሚበል ላም ጥጃ ሰጠጥቼሻለው፡፡

‹‹እሽማ››አጎት የሙሽራይቱ እናት ወንድም ላሉ፣ ሀራሩ ፣ ለንካና፣ እሽማ አብሱ  ኣሴንኬ ከን አሌን በርግ ለሙንኩዕኔ ሳዕልቴናንተ ፋሹ አሴንክዕኔ" ትርጉም ፡- ፍሬሽ እንዲበዛ ሰጠውሽ አጎት፣ አክስትን ማክበር ሰጠውሽ በሚል ምርቃት በተጨማሪ ሁለታችሁም ለጉዞ እንድትተቀሙበት አንድ ፈረስ ሰጥቼሻለው ፡ ይላል ፡፡

"አዳዬ›› የአባት እህት አኒ አሳንኬ ሌኡ አሴንኬ እለሙ ሆረንካ አብሱ አሴንኬ ከን አሌን በርግ መትተ ሆልቼተ አሴንኬ"  እኔም ሰጠውሽ ማደግን ሰጠውሽ ዘመድ የተባለውን ሁሉ ማክበርን ሰጠሁሽ በዚህ ላይ ጨምሬ አንድ በግ ሰጥቼሻለው ፡፡ ትላለች

"አማይ" የእናት እህት ለሉ ዜኡ ኣሴንኬ ከን አሌን ሆረንከ መና አብሱ አሴንኬ ሆልቾ በከኒ በርጌንኬ" ትላለች ከብት ማርባትና መውደድን ሰጠውሽ ሰውን ሁሉ ማክበር ሰጠውሽ በዚህ ላይ ጨምሬ የበግ ግማሽ  ሰጥቼሻለሁ፡፡

ይህንን የስጦታ አሰጣጥ ስርዓት ስናይ በአካል እጇ የሚገባ ነገር ከመስጠት ይልቅ ትኩረቱ ለልጅቷ መልዕክት ማስተላለፍ ነው፡፡ በዋናነት ሥጦታቸው ምክር ወደፊት ሙሽራዋ ከቤተሰብ ጋር ተቀላቅላ ስትኖር እንዴት መኖር እንዳለባት እያንዳንዱ ሥጦታ ሰጪ በሥጦታ መልክ ምኞትና ፍላጎት ከእሷ ምን እንደሚጠበቅ ሲገልጽ ይሰተዋላል፡፡ እንዲያውም አካላዊው ሥጦታ በተጨማሪነት እንደሚሰጧት ማሳየታቸው ዋና ጉዳይ ወይም ትኩረት እንድታደረግ የፈለጉት ምክራቸውን መለገሳቸው መሆኑን የእያንዳንዱ የሥጦታ አሰጣጥ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ፡-  የአባት ሥጦታ ስናይ፡- ፍሬ ሰጠውሽ ሲሉ የትኛው በጋብቻው ዓለም ኑሮዋ ስኬታማ እንዲሆን እየተመኙ ከእሷ የልጁን (የባሏን) እናት አባት፣ ጎረቤት፣ ዘርን ወይም ዘመዶችን ሁሉ ማክበር ከእሷ እንደሚጠበቅ ከገለጹላት በኋላ በተጨማሪነት ወይም ከዚህ ጋር ጨምሬ አንድ ጥጃ ሰጠውሽ ይሏታል፡፡ ሙሽራዋ ካስታዋለች ከእሷ የሚጠበቁትን ተረድታ መተግበር ይጠበቅበታል፡፡ እናትም ፤- እንዲሁ ከሙሽሪት የሚፈልጉትን የሚጠበቅባትን ነገር ካስተላለፉ በኋላ አንድ ጥጃ ሲሰጧት ይታያል፡፡ ምን አልባት አባትም እናትም ጥጃ የሰጡበት ምክንያት ጥጃዋ እንዴት ተንከባክባ አሳድጋ ለቤተሰቧ የወተት ባለቤት ማድረግ እንዳለባት የኑሮ ዘይቤዋ ከብት በማርባት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ለመግለጽ ነው፡፡ ይህንን የሚያረጋግጠው በመጨረሻ የአማዬ ምርቃት ከብት ማርባት መውደድን ሰጠውሽ ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ይህ

ማህበረሰቡ ከብት ማርባት ያለውን ጥቅምና ከበሬታ ያሳያል ፡፡ባጠቃላይ የስጦታ አሰጣጥ ስርዓቱ የምክር የግሳጼ እና የአኗኗ ዘይቤ ማሳያ መድረክ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

### 4.3. ‹‹ሔረቱተ›› አግባብቶ ማግባት

ሁለተኛው የከምባታ ባህላዊ የጋብቻ አይነት ሲሆን አቶ ካሳ ጆሪ 24/8/2010 ዓ/ም እንዲህ ይላሉ፡- ከቤተሰብ ፈቃድና ዕዉቅና ዉጪ የሆነ ጋብቻ ነዉ፡፡ በሁለቱም ተጋቢዎች ፍቃደኝነት ተስማምተዉ ከቤተሰብ አውቅና ውጪ የሚፈፀም ነዉ፡፡ አንድህ ዓይነቱ ጋብቻ እብዘኛዉ የሚከሰተዉ የቤተሰብ ተቃዉሞ ሲገጥም፣ ለሠርግ ድግስ ዓቅም ሲያጥርና ለጥሎሽ የሚሆን ገንዘብ ሲታጣ ነዉ፡፡ አጀማመሩም ሁለቱን ታጋቢ ጥንዶች የሚያውቅ ዘመድ ከወንዱ ወይም ከሴቷ ጋር አግባብ ያላቸው (በአብዛኛው ጊዜ ለዚህ ተግባር የሚታጩት ሴቶች ሲሆኑ አክስትና የወንድም የአጎት ሚስት) የምትሆንህ የምትሆንሽ በማለት ማግባባት ይጀምራሉ፡፡ በተለይ ወንዱ በሰማውና ባየው ልቡ ከታሰበና ፍቃደኛ ከሆነ አግባቢዎቹ ሴቷን ለማሳመን በርትተው ይሰሩና የእሷን መስማማት ካገኙ በኋላ ልጅቱ በሚስጥር ከቤቷ እንድትወጣና በወንዱ ዘመድ ቤት በማትደፈርበት ሁኔታ እንድትቀመጥ ተደርጎ ሁለቱ ‹‹ስለተስማሙ ፍቃዳችሁን›› ተብሎ ሽማግሌ ይላካል፡፡የሚላከውም ሽማግሌ በተራው ወላጆቹን ለማግባባትና ለማሸነፍ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከተሳካለቸውና ስምምነት ላይ ከደረሱ ማጫ የሚወስድበት ቀን ተወስኖ በስምምነቱ ጎዳና ጋብቻው የሚፈጸምበትን እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በመጀመሪያ ቢያንገራግሩና ተደፈርን ለማለት ቢሞክሩም የስጦታውን ዋጋ ለማብዛት ካልሆነ በቀር ብዙም ፋይዳ የለውም፡፡‹‹በሔረቱት››አግባብቶ ከቤት እንድትወጣ ካደረገ ቦኋላ የአግቢው ቤተሰብ ከ3 ቀን ቦኃላ ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ይህ በከምባትኛ‹‹ **መገኒተ›› ሙጡኝ** ይባላል ፡፡

#### 4.2.1.‹‹ መገኒተ›› ሙጥኝ

መገንተ ሙጡኝ የሚለው ቃል የተወሰደው ‹‹መገኖ›› (እግዚአብሔር) ከሚለው ቃል ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የቃሉ ውስጣዊ ይዘት እርቅን በእግዚአብሔር ስም ይዞ ወደተቀያየሙ ሰዎች ፊት መቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ መገኒት ወጉን ባህሉን አሟልተው የሚመጡትን ሰዎች

ማንም ረግጦ አያልፍም ወይም አልቀበልም፣ አልታረቅም የሚል ሰው አይኖርም፡፡ ለዚህ ነው ነፍስ ያጠፋ ሰው እንኳን በመገኒት (ሙጡኝ) ጉዳዩን በእርቅ መጨረስ የሚችለው፡፡ይላሉ የጎሳዎች መሪ ወይም የኮካታ ሰብሳቢ አባት ጴጥሮስ ኦርዶፋ (14/9/2010) ‹‹ሔረቱት›› አግባብቶ የማግባት ጋብቻ ሥርዓት ወቅት ልጅቷን በዘመዶቹ ቤት እንዳስቀመጠ በሦስተኛው ቀን ሽማግሌዎች ለሙጥኝ ይላካሉ ይህን በከምባታ ባህል መገኒት ይባላል፡፡ ‹‹ለመገኒት›› ለሙጥኝ ስርዓት የሚሄዱ ሽማግሌዎች ‹‹ቢቴ›› እና‹‹ ቢኬ መገኒተ›› የሚባል የሽምግልና አላላክ ስርኣት አለ፡፡ ‹‹ቢቴ መገኒተ›› ተቀባይነት የሌላው ባህሉን ያልጠበቀ ሲሆን ‹‹ቢኬ መገኒት›› የሚባው የከምባታን ባህልና ወግ የጠበቀ ተቀባይነት ያለው የሽምግልና አላላክ ስርዓት ነው፡፡

ቢቴ መገንተ ወግና ሥርዓቱን ያልጠበቀ ወይም ተቀባይነት የሌለው እንዲሆን ያደረገው ምንድ ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው አባት ጴጥሮስ ሲያብራሩ ቢኬ መገንት ከምባታ በባህሉ ለሙጥኝ ወይም የትኛውንም ችግር ሊፋታ ይችላሉ ብሎ የመረጣቸው ጎሳዎች አሉ፡- እነዚህም፡-

1. ላሂ መገኒተ -ኦየታ
2. አሺን መገኒተ- ጉልባ
3. ሰሬች መገንተ - ዎማሎ
4. ገዲ መገንተ - የሚባሉ 163 ጎሳዎች አሉ፡ የእነዚህ ጎሳዎች ስም ዝርዝር ለዳኝነት የሚጠቀሙብትን መዝገባቸውን እያገላበጡ በማንበብ አጳፉኝ እንዲህ ሲሉ ሰጋ፣ ኤርገና፣ ኤቤጄና፣ ካርማ፣ አጋዋ፣ ሂኒራ፣ አዋዶ፣ ዘኬታ፣ ዲቦሶ፣ ዱቂጬ፣ አዳሙኝታ፣ አመኔያ፣ ጉና፣ አቡሬ፣ አዋዶ፣ ነዴና፣ ዛቶ፣ አውሳ፣ በኔሽመና፣ ዱማ፣ ሂዝያ፣ ፋርዛኖ፣ እንደጋኝ፣ ኡልበራጋ፣ ጤልመና፣ እንተካና፣ ፍጤመና፣ ጆራ፣ ጋዳ፣ እንደና፣ ዱርቤ፣ ቦዴመና፣ ጎንጋ፣ ቁንጣኖ፣ መልጌሰንታራ፣ ኡቀዛ፣ ኑርቶ፣ እነዋ፣ ሞጬ፣ ጎጂና፣ ገበራ፣ ጎትመና፣ ጋላ፣ ሀበሎ፣ የቡ፣ ሆንቃዕላ ፣ ሀንበራሶ፣ ሂምባዕስመና፣ ሻሾጎ፣ ሁርዛ፣ መስቃን፣ መስዋ፣ ደሞታ፣ ጦምባራ፣ ቤቂታ፣ ሰርቀሞ፣ ዌሬዛ፣ ቦሮጅመላ፣ ዶለጋ፣ አውዳ፣ ወማሎ፣ ኦሞሾጎራ፣ ጅጋ፣ ሂሴሴ፣ ባዶጎ፣ ቁዕና፣ እንንችችላ፣ ህዝባቃ፣ ኮሊምና፣ አዳሙና/አዳማኜ/አነሽቶ፣ ዘባም፣ ኦቶሮስ፣ አርጋማ፣ ዲሞራ፣ መልግባ፣ ባዶጎ፣

ኢነጋራ፣ ወረራ፤ አነገበራ፣ ዲዲ፣ ዳዊ፣ ቀርሱ፣ ደጋግመና፣ ጎንዶሮማ፣ ለጥብኦሶ፣ ሂሪታ፣ መገራ፣ ጉኡታ፣ ደሙታ፣ እንጀትኦሶ፣ አሰረኦሶ፣ አለቅራ፣ ሆጄ፣ትግራ፣ ጣምበሮ፣ ላውካ፣ ዱበሞ፣ መስመሳ፣ ገንዛ፣ ጠዞ፣ ሰንጋ፣ ሆገኦሶ፣ ዶርቤ፣ ዛሚኔ፣ በርጋጌ፣ ያንጋሮ፣ ደረጃ፣ ሳቦላ፣ ደዋር/ኦሳ፣ ወላይታ/መላ፣ ታረች/መና- ታሬችመና/፣ አንቺያማ፣ አዘራ፣ ቡቡላ፣ ወርምኔ፣ ሃይባ፣ ሃንቃላ፣ አልክመና፣ ምንጊራ፣ ዳሞ፣ አገጂ፣ ለጥብኦሶ፣ ሂሪታ፣ መገራ፣ ጉኡታ፣ ደሙታ፣ እንጀትኦሶ፣ አሰርኦሶ፣ አለቅራ፣ አባኦሶ/አባይ፣ መና፣ ደምበላቻ፣ ዘምቦችቶ፣ ዘፄታ፣ መሽቶ፣ ስንታየኖ፣ ዱቦ፣ አጀክቾ/ኤፍታ/፣ ድልድሌ አማራ፣ ቆራንዳ አማራ፣ ቤተ አልባ አመራ፣ ገራዶ አማራ፣ ገፋት አማራ፣ ባርሙጃ፣ ዎሎ፣ አብርሃም አማራ፣ ቡሌ አማራ፣ ቀነኒ አማ፣ እናገፍ አመራ፣ ጋሞ አማራ፣ ዋና አማራ፣ ሳታገጅ አማራ፣ አንገት አማራ፣ ሐጤ/አጼ አማራ፣ ሐግበ አማራ፣ ባሶ አማራ፣ አንጥሮ አማራ፣ ዳሮ አማራ፣ ኢታሎ አማራ፣ ሞገስ አማራ፣ ሎኪ አማራ፣ አርቶ አማራ

ከላይ በአራት ደረጃ የተገለጹ ጎሳዎች ልጁ ልጅቷን ከቤት አባብሎ ከቤት እንድትወጣ አድርጎ ሽማግሌዎችን ሲልክ ከገዲ መገኒታ ጎሳዎች የተመረጡ ሰዎች፣ ላሂ መገኒት (አየታ)፣ ከአሺን መገኒት (ጉልባ) እና ከሰሬች መገኒት (ወማሎ) ጎሳ የግድ አንድ ሰው በሽምግልና ውስጥ መግባት አለበት፡፡ ከተጠቀሱት ጎሳዎች ውስጥ አንድም ሰው ካልገባ ይህ የሽምግልና አላላክ ‹‹ቤቴ መገኒታ አቅናምባ›› የውሸት ሙጥኝ ነው አንቀበልም ‹‹መገኒት አንፋምባ››ሙጡኙን አንይዝም ተባብለው ሽማግሌዎቹን ይመልሷቸዋል፡፡ ይህ ማለት በትክክል ወጉንና ሥርዓቱን የተከለ የሽምግልና አላላክ ሥርዓት አይደለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ውሸታሞች ናቸው ፤ይቀልዱብናል፤ ያሾፉብናል፤ በትንሽ ዓይን አይተውናል፤ ልጃችንን አንሰጥም ይመልስልን ይላሉ፡፡ የልጅቷ ቤተሰቦች ከሽማግሌዎችጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

<u>**ቤኬ መገኒት**</u> (እውነተኛ ወግና ባህሉን የጠበቀ ተቀባይነት ያለው የሙጥኝ አላላክ ሥርዓት ይባላል፡፡ ይህም ከላይ ከ1-3 ከተጠቀሱት ጎሳዎች ውስጥ አንድ ወይም ሁለት አሊያም ሦስቱም ጎሳዎች የተካተቱበት ከገዲ መገኒት የፈለጉትን ቁጥር ያህል ጎሳዎችን በማካተት የሚላክ የመገኒት/የሙጥኝ/ የሽምግልና አካሄድ ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ተዋቅሮ የተላኩ ሽማግሌዎች ተቀባይነት ስላላቸው የልጅቷ ቤተሰብ የልጁን ጉዳይ በመጨረሻ

ፍቃደኛነታቸውን ይገልጻሉ ወይም ጉዳያቸውን ጨርሰው መምጣት ይችላሉ፡፡ “ያኔ‹‹መገኒት አንፌም›› ይላሉ ሙጡኙን ተቀብለናል፤ አሁን በመጣችሁበት ጉዳይ መነጋገር ትችላላችሁ በማለት ለመስማት ፈቃደኛነተቸውን ይገልጻሉ፡፡መገኒት የሙጥኝ አካሄድ ሥርዓት ሌሎች በከምባታ ብሔረሰብ ጎሳዎች ጋር የሚኖሩ ነገር ግን በጋብቻ ወቅት በሙጥኝ (በመገኔ) ሥርዓት ውስጥ የማይካተቱ ጎሳዎች አሉ፡፡ እነዚህም አጊዛተ ፣ አዋዱተ እና ሰጋ ይባላሉ ፡፡ከነዚህ ጎሳዎች ጋብቻ ስፈጽሙ እርስ በራሳቸው አጊዘት አጊዘተ ፣ አዋዱት አዋዱተ፣ ሰጎ ሰጋን ነው ማግባት የሚችለው ፤ ከሌላው የከምባታ ጎሳዎች ጋር እንዲጋቡ ማህበረሰብ አይፈቅድላቸውም፡፡ ከዚህ የተነሣ የመገኒ (ሙጥኝ) ሥርዓቱ እርስ በእርስ ነው የሚላላኩት እንጂ ሌላ ጎሳ አይልኩም፡፡ ይህ ማህበረሰብ በራሱ መመዘኛ የሰጣቸው ደረጃ መሆኑን ይናገራሉ፡፡‹‹ገድ መገኒት›› ከሚባሉት ውስጥ አንድ መቶ ስልሳ ሦስት ጎሳዎች እንዳሉ የከምባታ የጎሳዎች መሪ የሆኑ ወይም የኮካታ ሰብሳቢ አባት ጴጥሮስ አርዶሎ በተደረገላቸው ምልልስ መዝግበው ካስቀመጡት እያነበቡ ጭምር የገለጹት ሲሆን ከአንድ መቶ ስልሳ ስድስት ውስጥ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ጎሳዎችን ገዲ መገኒት የሚባሉት አራተኛ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ ከነዚህ ጎሳዎች ውስጥ ብቻ የተወጣጡ ሽማግሌ ተመርጦ ለጋብቻ ጉዳይ ለሙጥኝ ቢላክ ቤተሰቡ ለእነዚህ ሽማግሌዎች የሚሠጠው ምላሽ ‹‹ቤቴ መገንተ ሃሳዊናምባአ›› በውሸት የመጣ ሙጥኝ ስለሆነ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ውይይት ወይም ሀሳብ ለመለዋወጥ ፈቃደኞች አይደለንም ብለው ይገልጹላቸዋል፡፡

ትክክለኛ ለጋብቻ የሙጥኝ አላላክ የጎሳው አደረጃጀት የጠበቀ ሆኖ ከመጣ የልጅቷ ቤተሰቦች አመጣጣቸው ተቀብለው ውይይት ግን ለመጀመር በዕለቱ መጀመር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ልጅቷ የተቀመጠችበት ቤት ድረስ ሰው ልከዉ ያለችበትን ሁኔታ ማጣራት አለብን፡፡ አስገድደው ደብድበው፣ በጫና ከቤት እንድትወጣ አድርጓት ነው ወይስ ተስማምተው የፈለገችውን ነገር ገዝቶ አሟልቶላት ነው፡፡ ይህንን ቀድመን ማጣራት አለብን ብለው ሽማግሌዎችን ቀጠሮ ሰጥተው ይሸኟዋቸዋል፡፡ የቀጠሮው ቀን እስከ ምደርስ የልጅቷ ቤተሰብ ወንድሟን ወይም አጎቷን አሊያም የቅርብ ዘመድ ልጅቷ ወደ ተቀመጠችበት ቤት እንሂድና ልጅቷን በአካል አግኝቶ እንዲጠይቃት ይላል፡፡ የተላከውም ሰው ሂዶ ይጠይቃታል፡፡ ልጅቷ ከልጁ ጋር ተግባብታ ስለምትወጣ ባያደርግላትም

ሁሉንም ነገር አሟልቶልኝ ነው ከቤት የወጣሁት ምንም ነገር አላደረገልኝም የሚል መልስ ትሰጣለች፡፡ ምክንያቱም ተስማምታ የምትወጣበት የጋብቻ አካሄድ ስለሆነ ቤተሰቧም ቢሆን ይህን ልቡ እያወቀ ከእርሷ አንዳበት ለመስማት ፈልገው እንጂ ሁሉንም ነገር ይታወቃል፡፡የዚህን የማጣራት ሁኔታ አውቀው የቀጠሮ ቀን ወላጆቿ ሽማግሌዎችን ይጠብቃሉ፡፡

ከላይ የተገጸውን ‹‹የሂረቱት›› አግባብቶ ማግባት ስርኣት ከቤተሰብ አውቅና ውጪ ሊሆን የቻለበት ምክኒያት የቤተሰብ ተቃውሞ ሲገጥም ነው፡፡የቤተሰብ ተቃውሞ የሚነሳው ለባህላዊ ጋብቻ መመዘኛ ሳያሟላ ሲቀር ፣ ለጋብቻ የማይፈለግ ባህሪ፣ የደም ንክኪ ወይም የሀብት አለመመጣጠን፣ የእሱ ቤተሰብ ሀብታም ሆኖ የእሷ ቤተሰብ ደሀ ከሆነ ወይም የእሱ ቤተሰብ ደሀ ሆኖ የእርሷ ቤተሰብ ሀብታም ከሆነ አሊያም በሁለቱ ቤተሰብ መካከል ጠብ (ጥላቻ) ካለ ባጠቃላይ ወላጆች ፍቃደኛ አለመሆናቸው ሲረጋገጥ በድብቅ ጋብቻ ለመመስረት የሚከሄድ ድብብቆሽ ነው፡፡

ሁለተኛው በምክንያት ያነሱት ለሰርግ ድግስ አቅም ሲያንሳት ለጥሎ የሚሆን ገንዘብ ሲጠፉ በወላጆች ፍቃድ የተመሰረተ ጋብቻ ከሆነ ባህል የሚጠይቀውን ማሟላት ይገባዋል፡፡ይህንን ባህላዊ ስርኣትለመፈጸም የሀብትና የገንዘብ አቅም ማነስ ሲያጋጥም የፈለኳትን ልጅ ድህነቴ ሊያሳጣኝ አይገባም ያለ ልጅቷን አባብሎ ከቤት እንድትወጣ ያደርጋታል፡፡

ሌላ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው ማህበራዊ ደረጃን ነው፡፡ አንደኛው የጎሳ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው የሀብት ደረጃን ማየት እንችላለን፡፡ ወጉን ባህሉን መጨረስ ያቃለው ከሆነ የሀብት ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ ላይ ማኅበረሰቡ የተሰጠውን ማኅበራዊ ደረጃን ማየት እንችላለን፡፡ ኅብረተሰቡ በራሱ መመዘኛ ለጎሳዎች ከ1 እስከ 4 ካሉት አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ጎሳዎች ከአንድ እስከ አራት ደረጃ ሰጥተዋል ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት አንድ አንዳንድ ጎሳ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሌሎቹ አንድ መቶ ስልሳ ሦስቱ አንድ ላይ አራተኛ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ የደረጃ ሰጣጥ የራሱ የሆነ ሰፊ ታሪክ ያለው እና እራሱን አስችሉ በጥናት መልክ ማንሳት የሚቻል ነውና ለዚህ ጥናት ግን የቤቴ መገኒትና የቤኬ መገኒት የቋንቋ አገላለጽ ይህንን ሁሉ

ዝርዝር በውስጡ አምቆ የያዘ መሆኑን ለማሳየትነው፡፡በዚህ ዓይነት ሽምግልና ተካሄዶ እርቅ ከወረደ በኋላ የወንዱ ቤተሰብ ኮርማ ማር "ወርጃሙሃ" መለቡሃ/ ይዘዉ ለጥፋታቸዉ ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተጋቡ ቦኃላ የወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ጥሎሽ ያመጣሉ፡፡ በዚህ አኳሃን ጋብቻ በቤተሰብ ዘመድ ሁሉ እዉቅና ያገኛል፡፡

### 4.4 "ምዱ" የጠለፋ ጋብቻ

ጠለፋ ህገ ወጥ ጋብቻ ሲሆን ከሴቷም ሆነ ከቤተሰቧ እዉቅናና ፍላጎት ዉጪ በወንዱ አስገዳጅነት በጉልበት የሚፈፀም ነዉ፡፡ ወንዱ ሴቷን ለጋብቻ ፍላጎት የማጥናት ሙከራ ወይም ጥያቄ አቅርቦ በሴቷ በኩል ፈቃደኝነት ሲታጣ ወንዱ ግን የግድ የልጅቱን ማግባት አለብኝ በሚል ደረቅ እልህ ከያዘዉ በአሳቻ ቦታ ወንድ ጓኞቹን አስተባብሮ በመጠበቅ ከገበያ፣ ከወንዝ ወይም ከተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሲትሄድ ወይም ተመልሳ ስትመጣ በትክሻ ተሸክመዋት ይወስዷታል፡፡ ጠላፊዎቹ ልጅቷን የሚሸከሟት አግቢዉ አስቀድሞ እጇን ሲነካት ነዉ፡፡ ጠለፋ በተጨማሪ ከጥሎሽና ከሠርግ ዉጪ ለመዳን ሲባል በኀይል የሚፈፀም ጋብቻ ነዉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሴቷ ቤተሰብ ልጅቷ የወደደችዉን ሰዉ እንዳታገባ ከተቃወሟት ወይም ወንዱን የሴቷ ቤተሰብ ወዶአት ስለ ልጅቱ ፈቃኛ ሳትሆን ከቀረች ወንዱ እንዲጠልፉት ይፈልጋል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የስምምነት ጠለፋም እንዳለም ይታወቃል፡፡

በ"ቆርሲሻ" በጠለፋም ሆነ በሄረንቻ ካገበች ቦኋላ ሙሽሪት ለሙሽራዉ ቤተሰብ ክቡር እንግዳ ነች፡፡ የልጅ ወላጆች፣ ወንድሞቹና እህቶቹ ሌላ ስም እያወጡላት ያቀማጥሏታል፡፡ ወደ ሙሽራዉ ቤት የሚመጣ እንግዳ ሁሉ ሙሽሪትን ሠላም ከማቱ በፊት ስጦታ/እሪፎ/ የመስጠት ባህላዊ ግዴታ አለበት፡፡ የሙሽራዉ ጓደኞች በተለይም ሴቶች ለሙሽሪት ከረሜላ፣ ብርቱኳንና የመሳሰሉ ስጦታዎችን ይዘዉ መጥተዉ ይጠይቋታል፡፡ የልጁ አባት ሙሽሪትን በስሟ አይጠራትም፡፡ በከምባተኛ "እዜቾ" ይሏታል፡፡ ሙሽሪት ማለት ነዉ፡፡ አንቺም አይሏትም አንቱ ነዉ የሚሏት፡፡ የልጅ እናት ደግሞ ሙሽሪት ሥራ እስክትጀምር እንሰት ፍቃ ትሰጣለች፡፡ ከገበያም ቁሳቁስና ማጣፈጫ ትሸምታለች፡፡ ምክንያቱም

በከምባታ ባህል አንዲት እንስት ሴት ካገባች ቢያንስ ቢያንስ አንድ ዓመት ድረስ ከቤት ሳትወጣ በማንኛዉም ማህበራዊ ጉዳይ ሳትሳተፍ የቤት ዉስጥ ሥራም ሳትሰራ ጫጉላ ቤት ተቀምጣ መቀለብ አለባት፡፡

እንደየ ቤተሰቡ ባተሌነት አኳያ ከ3 ወር እስከ አንድ ዓመት ባለዉ ጊዜ አማቷ የጎረቤት ሴቶች ሙሽሪትን ወደ ገበያ ያወጧታል፡፡ ይህ ሙሽሪትን ወደ ገበያ የማዉጣት ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት በራሱ አግርሞት ያለዉ የከምባታ ባህላዊ እሴት ነዉ፡፡ ሙሽሪቷን ወደ ገበያ ዳር አድርሶአት ሁሉም ተሰብስበዉ በአንድነት ቦርዴ ይጠጣሉ፡፡ ከዚያም ገበያ የእያንዳንዱን ዕቃ ተራ እያሳዩአት ባህላዊ አሸማመት ዘይቤ ያለማምዷል፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሙሽሪት በራሷ ገበያ ወጥታ መሸመት ሥራ መሥራትና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ትጀምራለች፡፡(ቡድን ወይይት ግንቦት 6/2010)

### 4.5. ‹‹ረግተ›› የዉርስ ጋብቻ

አንዳንድ ጊዜ ሚስት እያለች ባል በወጣትነቱ ይሞታል፡፡ እንድህ ዓይነቱ አደጋ ሲከሰት የሟች የቅርብ ዘመድ ወይም ወንድሙ ሚስቱን እንዲወርሳት ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነዉ የሟቹ ሚስት ሌላ ባዳ አግብታ የቀድሞ ባሏ ንብረት እንዳይባክን፣ ልጆቹ እንዳይጎሳቆሉ በአባታዊ ስሜት እንዲያሳድጋቸዉ ለማድረግ ታስቦ ነዉ፡፡ ለዉርስ ሌላ ምክንያት የሆነዉ ባህላዊ እምነት አንዷ የአንድ ጎሳ አባል ካገበች የዚያ ጎሳ አካል ሆና ስለምትቆጠር፣

የመጀመሪያ ባሏ ከሞተባት የሌላ ጎሳ አባል የሆነ ባል እንድታገባ አይፈለግም፡፡ የዉርስ

ጋብቻ ሁለት ገጽታ ያለዉ ነዉ፡፡ ይሄውም ባሏ የሞተባትን ሴት በቤተዘመድ ሽማግሌ ዉሳኔ በዉዴታም ሆነ በግዴታ የሚፈፀም ጋብቻ ዓይነት ነዉ፡፡

የጋብቻ ዕድሜን በተመለከተ በከምባታ ብሔረሰብ የአብዘኛዉ የጋብቻ ዕድሜ ከ20 ዓመት በላይ ነዉ፡፡ የወንዱ ዕድሜ ብቻ አይወስንም፡፡ አቅሙም ወሳኝ ነዉ፡፡ መተዳደሪያም እንዳለዉም ይታያል፡፡ ሴት ግን ዕድሜዋ እየገፋ በሄደ ቁጥር ለጋብቻ የመፈለጓ መጠን

ይቀንሳል፡፡ በከምባታ ብሔረሰብ ድርብ ጋብቻ የተለመደ ነዉ፡፡ ከምባታዎች ድርብ ጋብቻ የሚፈጽሙበት የራሳቸዉ የሆነ ባህላዊ ምክንያት አላቸዉ፡፡ በቀድሞ ጊዜ በጦርነትና በጉልበት መሬት ይያዛል፡፡ በተያዘበት መሬት ላይ በእያንዳንዱ አቅጣቻ/ግምት፣ ጋሻ.. ያለዉን ንብረት የሚትጠብቅለትንና የሚትንከባከብለትን ሴት ማግባት የተለመደ ነበር፡፡ በሌላ አንፃር ደግሞ ድርብ ጋብቻ የሚፈፀመዉ የመጀመሪያ ሴት መካን ከሆነች ወይንም ወንድ ልጅ ካልወለደችለት ባሏ ወንድ ልጅ ስለሚፈልግ የግድ ሌላ ሴት ያገባል፡፡ ምክንያቱ በባህሉ ወንድ ወራሽ ዘር የሚተካ ተብሎ ስለሚታመን ነዉ፡፡ አልፎ አልፎ በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠረዉ የከረረ ጥላቻ ወይም በሴቷ የሙያና በስነ-ምግባር ጉድለት ባሏ ካልረካባት ልቡ ካላረፈባት ሌላ ሚስት ማግባት ይፈልጋል፡፡ አሁን አሁን ግን የብሔረሰቡ የጋብቻ ባህል በአብዘኛዉ ከአንድ በላይ ማግባትን እያወገዘ ነዉ፡፡ ስለሆነ እየቀረ ያለበትም ሁኔታ ነዉ ያለዉ፡፡ በድርብ ጋብቻ የተፈጠረ ቤተሰብ በአብዘኛዉ እየተጣለና እየተጋጨ ያስቸግራል በተለይም አባት በሚሞትበት ጊዜ በንብረት አከፋፈል ጊዜ የሚፈጠረዉ ግጭትና ጥል በቀላሉ የሚበርድ አይሆንም (ቡድን ውይይት ግንቦት 6/2010)፡፡

### 4.5.1 የውርስ ጋብቻ አፈጻጸም

የልጅቷ ቤተሰቦች ባሏ ከሞተ 2 ዓመት ተኩል እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ከጠበቁ በኋላ ወደ ልጅቷ ቤት ለመሄድ ይመካከራሉ፡፡ የልጅቷ ወላጆችና ቤተሰቦች ለዘመዶቻቸው ነግረው ለመሄድ ከተነጋገሩና ቀን ከወሰኑ በኋላ የልጃቸው የባል ቤተሰቦች ተሰብስበው እንዲጠብቋቸው መልዕክት ይልካሉ፡፡ በመልዕክቱ መሠረት የሟች ቤተሰብ ተሰብስበው ይጠብቋቸዋል፡፡ ሂደው እቤት እንደደረሱ ቀድመው ሀሳብ የሚያነሱት የልጅቷ ወላጅ ቤተዘመዶች ናቸው (ምልከታ ሚያዝያ 9/2010)፡፡

#### መገኛ ቋንቋ.

ሚሲሌ አኑ- ከቀጠ እኮች ረገንቹ አስዬ፣ ምን መንቹ አስዬ

- ኒ ቤቱት ከቀጠ ጥጅቴ ቴሱ ስግንሶሴ ክቹቾሴ ሀብሲንሶሴ
- አቀኖ ምን መንቹ ቅጠንስቴኑምቦደ ፣ መሰኤን ወሎ ዘሪ ገፊሬ
- ከንከ በር ጥጅቴኡ ቡሩ ቡዕርቱን፣ ስግሱን

ሀንቡን አጉርቱን፣

ሀከንተኔ ምን አና እሀኖ መንቹ ረገአኖ መንቹ አስዬ

**የአማርኛ አቻ ፋቺ**

የልጅቷ አባት፦ ልጃችን ይህን ያህል ጊዜ ከቆየች የቦታውን ሰው ስጡን

- ልጃችን ይህን ያህል ጊዜ ሀዘን ላይ ከቆየች እናንተም ሀዘን ላይ ከቆያችሁ አሁን ሁለቱም ወገን እናቀዝቅዘውና ለቦታው የሚሆን ወይንም ሟቹን መተካት የሚችል ሰው ስጡን፡፡ እሱን ሊተካ የሚችል ሰው ከሌላችሁ ልጃችንን መርቃችሁ ልቀቋት ከሌላ ቤተሰብ ታግባና ኑሯን እንድትቀጥል አድርጉልን፡፡
- እስከዚህ ቀን ድረስ አዝናለች ቅቤም ትቀባ፣ ትቀዝቅዝ፣ ትርሳ፣ ትተው

**መገኛ ቋንቋ**

የሟች ቤተሰብ- ልካ ረገአኖ መነ አስኑን

-አት አደቤ ሀዞሁ አት ሂአንያን ወሎ መኒ አስናምበአ

-አቴት ረገኡ ሀስሰኖሂሁ፣ ሜጡራ ሰዊተ አስቱዕናን ግድንሴንኬ

-አት ሂኦንትገ ለንካን ምኒ አስናምበአ

**የማርኛ አቻ ፍቺ**

የሟች ቤተሰብ- ያቀረቡልን ሀሳብ ትክክል ነው፤ ባሏን የሚተካ ሰው መስጠት አለብን፡፡

አንተ ወንድም እንደባህላችን መውረስ ያለብህ አንተ ነህ፤ አንተ እያለህ

ወደ አጎት ቤት ሰው ፍለጋ አንሄድም አንተ ምንም

ሀሳብ ሳትሰጥ እናስገድድሃለን ይሉታል ፤

ይህ የሀሳብ ምልልስ እንደተደረገ እንዲያገባት ወይም የወንድሙን ሚስት እንዲወርስ

የተጠየቀው ወንድም የማይፈልጋት እንኳን ቢሆን ሽማግሌዎቹ ይረግሙኛል በሚል ፍራቻ የእምቢታ ቃል አያወጣም፡፡ በዚህ ይስማሙና ልጁ ከእርሷ ጋር ኑሮ የሚጀምርበትን ቀን ወይም የሚያገባትን ቀጠሮ ይዘው ቤተሰቡ ያዘጋጀውን ቡና ይሁን ምግብ በልተው ጠጥተው ይለያያሉ፡፡

ከላይ የቀረበውን የምልልስ ሀሳብ ስንመለከት ፡ የልጅቷ ቤተሰቦች ሀዘን ማጠናቀቂያ ጊዜ ጠብቀው ልጃቸው ብቸኛ ሆና እንዳትቀር ለባሏ ቤተሰቦች ይዘው የቀረቡት ሀሳብ የመጀመሪያው ‹‹መዕኔ መንቹ አስዬ›› የቦታውን ሰው ስጡን? የሚለው ሀሳባቸው ባሏን የሚተካ፣ ባሏ መውለድ ጀምሮ ያቆመውን የሚያስቀጥል ፣ አቁሞ የሄደውን የእርሻ ሥራ የሚያስቀጥል፣ እንደባሏ ሆኖ ልጆቿን የሚያሳድግ ኃላፊነትን የእርሷንም ጭምር የሚወስድ ባጠቃለይ ባሏ ሲያደርግ የነበረውን ነገር ሁሉ በማድረግ የሚተካውን ሰው ስጡን የሚል ሀሳብ ያዘለ ጥያቄ ይዘው ቀርበዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ልጃችን ይህን ያህል ጊዜ ካዘነች ሀዘኗን ማብቃት አለባት ‹‹ከንከ በር ጥጅቴኡ ቡሩ ቡዕርቱን ስግሱን›› ይህን ያህል ጊዜ አዝናለች አሁን ቅቤ ትቀባ ታቀዝቅዝ ሲሉ በሀዘኑ ምክንያት ያቋረጠቻቸውን ነገሮች እንድትቀጥል ይደረግ ሀዘኗን የሚያስረሳ በሀዘኗ ምክንያት የተጎዳችበት ጊዜ ይብቃ አሁን ወደቀድሞ ኑሮዋ እንድትመለስ ይደረግ ለማለት ፈልገው ነው፡፡

በመጨረሻም ‹‹ መዕኔ መንቹ ቅጠንስቴኑምቡች ማሰኤን ገፈሬሴ››፤ የሟቹን ቦታ ሊተካ የሚችል ሰው ልትሰጡን ካልቻላችሁ መርቃችሁ ልቀቋት፡፡ ይህ ማለት በራሷ ፈቃድ ይህን ቤተሰብ አልፈልግም ብላ ሌላ ዘር ማግባት አትችልም፡፡ እነርሱ ሳያውቁ እንኳን ከሌላ ዘር ጋር ተስማምታ ብታገባ ይረግሟታል፡፡ ስለዚህ ወደ እርግማኑም እንዳትገባ የፍራቻ እና የማስፈራራት ሀሳብ የተቀላቀለበት ነው፡፡ ምክንያቱም ፍራቻው እርግማን ነው፤ ከረገሟት እርግማኑ ይደርሳል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ማስፈረራቱ ደግሞ እናንተ የውርስ ሰው ማዘጋጀት ካልቻላችሁ ልጃችንን የሚወስዳት ሰው አይጠፋም ብቻዋን አትቀርም የሚል ውስጣዊ መልዕክት ያለውን ሀሳብ አስተላልፈዋል፡፡

የሟች ቤተሰብ የመለሰውን ሀሳብ ስመለከት ‹‹ይዛችሁ የቀረባችሁት ሀሳብ ትክክል ነው››፤ ባህላችንን እናከብራለን፤ በባህላችን መሠረት የሟች ወንድም ትወርሳለህ‹‹ አት ሂኦንትገ

ለንካንምኒ አስናምበአ፤ ኬሳ አስኔንኬ›› አንተ ወንድሙ እያለህ ሌላ አጎት ቤት ፍለጋ አንሄድም፣ ለአንተ ሰጥተንሃል›› ሲሉ ይስማሉ፡፡

ይህንን ሀሳብ ስንመለከት ወንድም ላይ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እንጂ አስተያየት እንዲሰጥበት ዕድል የሚሰጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንተ በባህላችን መሠረት ይመለከተኃል ስለዚህ ሰጠንህ ውሰዳት ነው የተባለው፡፡ ከዚህ ሀሳብ ማፈንገጥ እንደማያዋጣው ያውቃል ፡፡ ከባህሉ ቢያፈነግጥ የሚከተለው እርግማን ነው፤ ከእርግማን በኋላ ደግሞ ምን ዓይነት ኑሮ ሊኖር እንደሚችል ስለሚያውቀው ሀሳቡን መቀበል አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡ ስለዚህ ያለው ዕድል መቼና እንዴት እንደሚያገባት ማሰብ ብቻ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የሽማግሌዎች ሀሳብ አቀራረብ ከባህሉ ማንም እንደማይወጣ እምነት እንዳላቸው የሀሳብ አቀራረባቸው ያሳያል፡፡ የሚጋቡበት ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ቀን እኚሁ የልጅቷ ዘመዶችና የልጁ ቤተሰቦች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ቀን አግቢው ለእሷ የሚያስፈልጋትን ስጦታ ሁሉ(ልብስ፣ ጫማ፣ ዣንጥላ ወዘተ) እንደአቅሙ ይገዛላታል፡፡ ቤተሰቡም በሚጋቡበት ቀን በግ ወይም በሬ አርደው በሁለቱ ግምባር ላይ ደም እንዲቀቡ ይደረጋል፡፡ ይህ ቃለ መሃላ እንደማስገባት ነው፡፡የታረደው በግ/በሬ ሥጋ ተሠርቶ የሁለቱም ቤተሰቦች ከተጋበዙና ለሴትዮዋ የተዘጋጀው ስጦታ በሰዎቹ ፊት እንድትወስድ ከተደረገ በኋላ የምርቃት ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ ሥርዓቱ የሚካሄደው ከሚች ቤተሰብ በመጡ ሽማግሌዎች ይሆናል፡፡ ‹‹አባ ዶግሶ ማሰእዬ›› የዶግሶ አባት ይመርቁ፡-

**ምርቃት**

| የመገኛ ቋንቋ | የአማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ለሙንኩ ቦኩ አንሽንሶ | - ሁለቱም ቤተሰብ እንተው |
| አቼ ቴሱ ሆኑንኩ ስግንሶ | - እንግዲህ ሁላችን እናቀዝቅዝ |
| ሙጣአንፌም | - እርጥብ ይዘናል |
| ቡበት እኩንከ | - ማማረር አይሁን |
| ህልቅሰኖሩ ጎፉን | - የሚያስደነግጥ ነገር ይለቅ |

| | |
|---|---|
| አትን ለንኪ ሀልቆት | - አንቺም ካሁን በኃላ አትደንግጪ |
| - አትን አንሽስ | - አንቺም አቀዝቅዥ፣ ላንቺም ማቀዝቀዝ ይሁንልሽ |
| - ሂላሪን ደቀንቶት | - ከክፉ ነገር  አያግኝሽ |
| - ሆሩንኩሩ ከኒን ሀጉን | - ሁሉም ነገር በዚሁ ይለፍ |
| - ለንኪ ሀልቅሰኖሪን ደቀንቶት | -ከዚህ በኃላ ከሚያስደነግጥ ነገር አትገናኚ |
| -በጅጉት ዋልቱን | - ደስታ ይምጣ |
| -ሬሆን ለንኪ ደቀንቶት | - ከሞት ጋር ከዚህ በኃላ አትገናኚ |
| -ሬሁት ቡላ ቀሉ እኮሂ | - ሞት የበቅሎ መውለድ ይሁንልሽ |
| እልቱን ስርቱን | - ውለጂ፣ ክበጂ |

የምርቃቱን ሀሳብ ስንመለከት፦ ሁለቱም ቤተሰብ ሀዘኑን እንተው፣ እንርሳ፣ ወደ ደስታ ሕይወት እንግባ የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡ ይህ ሀዘንን ማክረር ጥሩ አይደለም፤ ሀዘን ሀዘንን ይዞ ይመጣል፤ መተው ግን ወደ ደስታ ያመራል፡፡ ስለዚህ ነው ‹‹ለሙንኩ ምኑ አንሽንሶ፣ ስግንሶ›› ሁለቱም ቤተሰብ ሀዘንን እናቀዝቅዝ፣ እንተው ያሉት፡፡ ‹‹ሙጣ አንፌም›› እርጥብ ይዘናል፣ አናከርም፣ የሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ አውቀናል፤ እርጥብ ነገር ይዘናል፣ ሁሉን ትተናል ብለው ለልባቸው ለአምላካቸው የማሳወቅ ዓይነት ያስረዳሉ፡፡

‹‹ሀልቅሰኖሩ ጎፉን›› የሚያስደነግጥ ነገር ከእንግዲህ አይኑር ሞትም ሆነ በሽታ አደጋ እንቅፋት መሰናክል ከቤቱ ደስታን የሚወስድ ነገር ከዚህ በኃላ በዚህ ቤት ላይ አይከሰት፤ይህ ቤተሰብ ከእንግዲህ አይደንግጥ ከዚህ በኃላ በደስታ ብቻ ይኖላ ይታሰብ ማለታቸው ነው፡፡

‹‹ሬሆን ለንኪ ደቀንቶት፣ ሬሁት ቡል ቀሉ እኩ›› ከሞት ጋር ከዚህ በኋላ አትገናኚ ፤ ሞት የበቅሎ መውለድ ይሁን ማለት ፍጹም የሞትን ጥላቻ የሚያሳይ ሲሆን በቅሎ አትወልድም

ስለበቅሎ መውለድ አሁን የሚያስብ ሰው የለም፡ የበቅሎ ስም ከተነሳ አብሮት የሚነሳው አለመውለዷ ነው፡፡ ልክ እንደበቅሎ መውለድ ( የበቅሎ መውለድ እንደተረሳ ሁሉ በዚህ ቤተሰብም ሞት የተረሳ ይሁን) ለማለት ፈልገው ነው፡፡

በመጨረሻም‹‹እልቱን ስርቱን›› ትውለድ፣ ትክበድ ማለታቸው እንድትወልድ ዘር እንድትተካ፣ እንድትበዛ መልካም ሀሳባቸውን አስቀምጠው የምርቃታቸው መቋጫ አድርገዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና ላይ ነው፡፡ ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የከምባታ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስነ ስርዓትና በስርዓቱ ወቅት የሚደረጉ የቋንቋ አጠቃቀሞች መተንተን ነው፡፡

ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቱ በአሁን ሰአት በዘመናዊ የጋብቻ ስርዓትና በመንፈሳዊ የጋብቻ ስርዓት የተተካ በመሆኑ በምልከታ ወቅት ባህሉን ያለቀቁ እስካሁን በዘመናዊም ሆነ በመንፈሳዊ ስርዓት ውስጥ እየተካተቱ የቀጠሉ እንደ ምርቃትና ጥሎሽ አሰጣጥ የመሳሰሉትን በአካል በመገኘት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ለዚህ ጥናት አብዛኛው መረጃ የተገኘው በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ነው፡፡

እነዚህ መረጃዎች በገላጭ ተንታኝ ስልት (discriptive analisis) እና ጥልቅ የዲስኩር ትንተና (CDA) አተናተን ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ከትንተናው የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

‹‹በቆርሲሻ›› በመተጫጨት መጋባት የጋብቻ ስርዓት በቅድመ ጋብቻ ወቅት መጥፎ ገድ ጥሩ ገድ በሚል ህብረተሰቡ ባወጣው መመዘኛ መሰፈርት ለጋብቻ የሚፈቅድና የሚከለክል መሆኑ በገድ ላይ ከፍተኛ እምነት እንዳላቸው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

የቃል ኪዳን ስርዓት በንግግር ቃል ከማስገባት ይልቅ ተግባራዊ ስርዓት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በስርዓቱ ክወና የተካተቱ ተግባራት ሲጠቃለሉ የአንገትና የእጅ አምባር ማጥለቅ ፣ በግምባር ደም የመቀባት፣ ከሙሉ እንስራ መጠጥ ከአናቱ የማፍሰስ ፣ ጥቁር የመንከስ ፣ ደም ረግጦ ወደ ቤት የመግባት ስርዓት እና ቡና አኝኮ በጡቶቿ መካከል የመትፋት ስርዓት ቃለ መሀላ ማስገቢያ ስርዓቶች መሆናቸውን ክወናው ያዘለው የቋንቋ መልዕክት ተተንትኗል፡፡

የሽማግሌዎች የሙጡኝ ‹‹መገኒተ›› አላላክ ስርዓት ጋብቻው ባህላዊ መሰረት እንዲይዝ

የሚላኩ ሽማግሌዎች ማህበረሰቡ ባስቀመጠው ማህበራዊ ደረጃ አማካኝነት የሚላኩና የሚያስፈጹሙ ናቸው፡፡ የብሄረሰቡ ጎሳዎች በአራት ደረጃ የተከፈሉ ናቸው ፡፡ ከአረቱ ቤተሰብ የተውጣጣ ጥምር ቡድን ተዋቅሮ የሙጥኝ ስርዓት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በደረጃ ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ ጎሳዎች በሙጥኝ ስርዓቱ የማይካተቱ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሁሉም ጎሳ እኩል አይደለም የበላይና የበታች አለው የሚል ፍልስፍና እንዳለቸው በትንተና የተገኘ ውጤት ያሳያል፡፡

‹‹በልሸተ›› በጋብቻ ማግስት ሙሽሪት የምትማረው የአማቾቿ የአክብሮት ጥሪ ነው፡፡ ይህ የባሏን አባትና ዘመዶቿን ስም እንዳትጠራ እንዴት በሌላ ቃላት ተክታ እንደምትጠቀም ይነገራታል፡፡ በተጨማሪም በስማቸው የመጀመሪያ ፊደል የሚጀምሩ ማንኛውም ድምጽ በሌላ ቀይራ በመጥራት አክብሮቷን እንደምትገልጽ ተተንትኗል ይህ ለባል ቤተሰብ መከበር ከፍተኛ ግምትና አስተሳሰብ እንዳላቸው በትንተናው ተረጋግጧል፡፡

‹‹ረግተ›› የውርስ ጋብቻ ይህ ስርዓት በሞት ምክኒያት የጋብቻ ሕይወት እንዳይቋረጥ በባህሉ መሰረት ተተኪ ይዘጋጃል፡፡ ተተኪው ባዳ ሆኖ ወይም የስጋ ዝምድና የሌለው ከሆነ የተወለዱ ልጆች ሊበደሉ፣ ሊጎዱ፣ ሊጎሳቆሉ፣ ላያድጉ ይችላሉ የሚል አስተሳሰብ ስላላቸው የሟች ወንድም ወይም የሟች የቅርብ ዘመድ የሟችን ሚስት እንዲያገባ በማድረግ እናትና ልጆች ሜዳ ላይ አይበተኑ በሚል፣ ኑሮና ህይወት የማስተካከል አስተሳሰብ እንዳላቸው በትንተናው የተገኘ ውጤት ያሳያል፡፡

‹‹ምዱ››ጠለፋ የሚባለዉ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት አብዛኛው ማህበረስብ የማይቀበለውና የሚያወግዘው ነው፡፡ ይህ ባህል በጥቂት ግለሰቦች በስሜትና ባለመግባባት የሚከሰት ከመሆኑም በላይ ከተፈጸመ በኋላ በሁለቱ ተጋቢ ቤተሰቦች መካከል እርቅ ለማካሄድ ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ማህበረሰቡ የዚህ ባህል ትክክለኛነት እምነት እንደሌላው የተደረገው ጥናት ያሳያል፡፡

ባጠቃላይ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የቋንቋ አጠቃቀም ለጋብቻ ያላቸውን ጥንቃቄ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ለጾታ ያላቸውን አመለካከት፣ እምነታቸውን ባህላቸው በቋንቋ አማካኝነት እንዴት እንደሚገልጹና ጋብቻ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መተሳሰር መሆኑን የሚያስገነዝቡ በሁለት

ተጋቢዎች መካከል አንድነት እንዲኖር በበርካታ የተግባርና የቃል ማሰሪያዎች እንደቀረበ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በድህረ ጋብቻ ወቅት ሚስት ለባል ቤተሰቦች የምታደርገው ከፍተኛ አክብሮት በቀጥታ ስሙን ካለመጥራት ባሻገር ባህሉ በየትኛውም ነገር ሚስት ለባሏ ዘመዶች ክብር መስጠት እንዳለባት ያሳያል፡፡ በመከባበር ውስጥ ብዙ መልካም ነገር ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይህ ባህል በአሁን ሰዓት እየከሰመ እየጠፋ ነው፡፡ ስለዚህ የቋንቋና የባህል ምሁራን አጥንተው ለቀጣይ ትውልድ ቢያስተላልፉት መልካም ነዉ ፡፡

የቋንቋ አጠቃቀሙን እያንዳንዱ ሀሳብ በነጠላና በግላጭ የሚገልጹ ሳይሆኑ በውስጣቸው ብዙ ትርጉም ማውጣት የሚያስችል እምቅና ክብደት ያላቸው ቃላት በመጠቀም ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡ መገሰጽ፣ መምከር፣ ማሞገስ፣ ማስተካከል፣ እምነት፣ ባህል ጾታና ማህበራዊ ደረጃን የሚገልጹባቸው መንገዶች ነጠላ መልዕክት አስተላላፊዎች አይሉም፡፡ ይህ አገላለጽ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉትና በዚሁ ቢቀጥል ጥሩ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት ሲጠና ሌሎች ጥናት የሚያስፈልጋቸው ነገሮችን ጠቁሟል፡፡ አንደኛ በብሂረሰቡ ውስጥ ያሉ አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ጎሳዎች በአራት ደረጃዎች ተከፍለዋል፡፡ ይህ ጥናት የጎሳዎቹን ስምና ደረጃ ብቻ ያነሳ ነው፡፡ ጎሳዎቹ በምን መመዘኛ ደረጃ ተሰጣቸው? ደረጃውን የሰጠው ማን ነው? ደረጃ ሰጪው እንዴት ተመረጠ? ደረጃ ውስጥ እንደይገቡ የተደረጉ ጉሳዎች አሉ? ልምን? የሚሉና ሌሎች ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ስለዚህ አራሱን አስችሎ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛ በአክብሮት ጥሪ (በልሽተ) ላይ ለዚህ ጥናት የሚሆን ጥቂት ነገር ተነሳ እንጂ እራሱን አስችሎ የስም ቅየራዉ እስከ ስንት ቤተሰብ ድረስ ነው? ምን አይነት ስሞች ወዴት ይቀየራሉ? በስም አቀያየሩ ላይ ለቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት ማውጣት ይቻላል ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳ ነው  እና ቀጣይ ጥናት የሚፈልጉ ነገሮች እንዳሉ ጥናቱ ጥቆማ አሳይቷል፡፡

## ዋቢ መጽሀፍ


ብርሀኑ ማቴዎስ ፣1986 የከምባታ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትንተና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ኤም ኤ ዲ ማ ጽ ያልታተመ ፡፡

ፈለቀ ብርሀኔ፤ 2009 ከምባታነት፣ እሴቶቹ፣ ትምህርትና ልማት አዲስ አበባ

ፍቃደ አዘዘ፤ 1993 የስነ ቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መጽሀፍ ማዕከል ሁለተኛ እትም

ደስታ ጸደቀ 1981 የከምባትኛ ስሞች በከምባታ ማህበረሰብ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ትምህርትና ዲ ማ ጽ ያልታተመ

ደስታ ገ/ሚካኤል 1963 የከምባትኛ ተረትና ምሳሌዎች ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዮኒቨርስቲ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ሰነ ጽሁፍ ትምህርት ዲ ማ ጽ ያልታተመ

ደስታ ሎረንሶ 1987 የከምባታ ህብረተሰብ ባለ እጆችና ስነቃላቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሰተ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍክ ትምህርት ፤ዲ ማ ጽ ያልታተመ

ተስፋዬ ሀቢሶ 1986፤ የከምባታና ሀድያ አስተዳደር የብሄረሰቦች ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች አዲስ አበባ ተጠርዞ የተሰናዳ

ፍሬሕይወት አድነው 1997 ከምባቶመት›› የከምባታ ፎክሎር ይዞታና ለውጥ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ትምህርት፣ኤም ኤ ዲ ማ ጽ ያልታተመ

ገዛሓኝ አሰፋ 1999 ዓ/ም የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በኢትዩጲያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት አዲስ አበባ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ፡፡ ያልታተመ

ግርማ ዘውዴ 2010 ‹‹የታሪክ የባህልና የእምነት ዳሰሳ ›› የመጀመሪያ እትም

አርቲንድ ደጉ 1995 የከምባታ ብሄረሰብ የሰርግ ስነስርአትና ግጥሞች አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዩጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ዲማጽ፤ ያልታተመ ፡፡

የማስታወቂያ ባህል ሚኒስቴር 1990 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ የባህል ፖሊሲ አዲስ አበባ 1990

የኢትዮጲያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍታብሄር ህግ (1952) ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር አንድ

የከምባታ ጠምባሮ ዞን ማስታወቂያና ባህል መምሪያ 1996 ፤አምበርቾ ቅጽ 1፣ቁጥር 1፣ግምቦት 1996 ዓ/ም አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

ፀደኒያ ዳመነ 2001 ‹‹የከምባታ ብሄረሰብ የባህላዊ ምግብና መጠጥ አዘገጃጀት አቀራረብና አመጋገብ ስርዓት በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት አዲስ አበባ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ  ያልታተመ

Braukamper;utrich.1983.Die kambate;Geschichete und Gesenschafteasies,silda thiopischem Bauern volkes,Wies baden;Frang steiner verlag.

Bauman, Ricahrd and chales L.Briggsn.1990 poetics and performance as criticall perspectives on languge,and social Life, Annual Review of Ant,

Berhanu Mathewos,1986.An Analysis of kembata proverbs,MA;Thesis school of Graduate studies.Addis Ababa university.

Bell.catherine, Ritual theore Ritual pratics,newyork oxfored unle press

Ben-Amos-1993 oan,context in context,western Folkore, Theorizing Foklore:Tow and New perspectives on the politics of culture vol.52.No 214,pp 209-226

Chouliaraki, L..& Fairclough, N. (1999). Rethinking Critical Discourse Analysis .Edinburgh; university press.

Dorson Richard M(ed) 1972 Folklore Folklife An introduction Chicago and London:Theunversity of Chicago press

Fairclough N.1995 Critical Discourse Analysis, London: Longman

Fairclough N. 2003 Discourse Analysis Textual Analysis: for Social Research. London, Routledge,

Finnegan Ruth, 1992 oral Traditions and verbal Arts London and New York Routlege. on and New York:Routledge,

Fishchertichte,Erika 2005 Theatre,sacrifice, Ritual Lond and New York Routledge

Fowler, R. and B. Hdge.1979 Critical Linguistics, In R. Fowler etal (Eds.) Language and Control. London: Routledge and Keegan Paul,

Goldstein,Kenneth.1964 AGuide for Field Workers in folklore.penny/vain Gale Research company American folklore,association inc

Halliday, M.A.K 1985. Introduction to Fnctional Grammar. London: Edward Arnold,

Liukun 2013 The cultur study in forign languge education.

Milk and cook, 2007 Doing ethnographic. London SAGE publishing:

Pentikainen,juha (2011) Ritual Folklore and Encyclopedia of Beliefs,customs.Tales Music,and Art,charlies,T,Mccormick and Kim kennedy Whiteceds,USA,ABC-cLlo LLc,2011,pp.1104-1110

sims,Martha C and Stephens,Martine.2005 Living.Folklores An Introduction to the study of people and their Tradition Longan:Utah state university press.

Singer,Norman.j (1977) .some notes on southern shoa London:school of oriental and African studies,university of London 28-29 june

Titshar, s. Meyer, m., Wodak, R, and Vetter, E.2000 Methods of Text and Discourse Analysis. London: Sage Publication,

Van Disk,(1998) News as Discourse Hilliside, NJ: Eribaum,

Widdowson, H.G (1998) The Theory and Practice of Critical Discourse Analysis, Applied Lingustics,

Zoltan Dornyei (2007):: Research methods in AppliedLingustic:quantitative, qualitative and Mixed Methodologies oxfor duniversity press

# መረጃ አቀባዮች

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አባት ጴጥሮስ ኦርዶሎ | ወ | 85 | ገረምባ |
| 2 | አቶ ወልዴ ሀሚዮ | ወ | 82 | ሀማንቾ |
| 3 | አቶ ሎጂሶ ኡዊቶ | ወ | 78 | ሂጎ |
| 4 | አቶ አሰፋ አለሙ | ወ | 75 | ቦንጋ |
| 5 | አቶ አቦ ሂገና | ወ | 89 | ደ/ 02 |
| 6 | አባት ወልደአብ ጆሬ | ወ | 98 | ደ/01 |
| 7 | አባት ባንዳ ዴቦ | ወ | 90 | ደ/02 |
| 8 | አቶ ጴጥሮስ ዋሼ | ወ | 86 | ጌዮጣ ገርባ |
| 9 | አቶ ካሳ ጆሬ | ወ | 72 | የቡ |
| 10 | አቶ አብቼ ሂራሞ | ወ | 92 | ደ01 |
| 11 | ወ/ሮ ኬሾ ኡሳሞ | ወ | 95 | ጌዮጣ ገርባ |
| 12 | ወ/ሮ ኑራሜ አራሮ | ሴ | 77 | ጌዮጣ ገርባ |
| 13 | አቶ ተክሌ ሙጉሮ | ወ | 72 | ደ/02 |
| 14 | አቶ ኤልያስ አያሴ | ወ | 87 | ገረምባ |
| 15 | ኤቶ ስምኦን አያኖ | ወ | 91 | ገርባ |
| 16 | አቶ ዩሴፋ ኮብሮ | ወ | 79 | ቃዛላ |
| 17 | ወጣት አክሊሉ | ወ | 22 | ባ/ቱ ባለሙያ |
| 18 | ወጣት አትጠገብ ሀ/ ማሪያም | ሴ | 25 | ባ/ቱ ባለሙያ |
| 19 | ወጣት ሙሉነሽ ብርሃኑ | ሴ | 81 | ባ/ቱ ባለሙያ |
| 20 | አቶ ዘውዴ ሙጉሮ | ወ | 38 | ባ/ቱ ባለሙያ |

## አባሪ አንድ

### የበልሻ ስሞች የተለመዱ አቀያየሮች ( የአክብሮት ጥሪ)

| | | |
|---|---|---|
| ሰኑታ | አፍንጫ | እንፌንቾት |
| ባሬቲተ | ፖፖ | ሾተት |
| መፅነተ | አል,ጋ | ኤንሸራ |
| ጊረተ | እሳት | ማሾራ |
| ባጨስተ | ማጭድ | ዘዘረተ |
| ከልተ | መቆፈሪያ | ሂደተ |
| አዙተ | ወተት | ሺሸት |
| ሴሉ | ጠላ | ሺደራ |
| ውኣ | ውሃ | ዳዳሙ |
| በበሩ | በርበሬ | ደውሸረ |
| በርጬመ | ወንበር | ጥቄሻ |
| ቡሩ | ቅቤ | ሀንዳሙ |
| ኤሬደ | ጺም | ገፉጨ |
| ጎደባ | ሆድ | ጨነ |
| ሀቱተ | ቆሎ | እንቀሉት |
| ሀጉ | በ,ጋ | ውጣሰነ |
| ሀሚሉ | ጎመን | ቀበረተ |
| ሀንዳርቹት | ርግብ | ክምርቾ |
| እልተ | | እምብርተ |
| ደጉድተ | ሰፊድ | ሳንፈተ |

| | | |
|---|---|---|
| ኤሎ | ገደል | ለግዱተ |
| ጋማንሱ | | መደንሱ |
| ግሰነተ | እንቅልፍ | ሂምብረታ |
| ኮራንቼ | | ኢልቲሩ |
| አገና | ወር | ቶከነ |
| አለሱ | ስንዴ | ሱነሱ |
| አንገተ | እጅ | ኤጀተ |
| አንተቤኡ | ዶሮ | ለዳሙ |
| አርቼተ | ፀሀይ | ኢዴ |

## አባሪ ሁለት

### ‹‹ማሳተ›› ምርቃት

| የመገኛ ቋንቋ | አማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ባዱኔ ጡማ ኢሁ | ሐገራችን ሠላም ይሁን |
| ኢያኑሴ መኩን | የልጅቷ ገድ ለእኛ የተመቸ ይሁን |
| ኢያኑሴ ኢለሚ መኩ | ገዱ ለዘመዶች ይመች |
| ኢያኑሴ ሆሪንካ መኩ - | ገዱ ለሁሉም ይመች |
| አደቤ ኢያኑሁ ኔሳ መኩ | የልጁ ገድም ለእኛ የተመቸ ይሁን |
| ኢተት ደደንቱን | የሁለቱም ቤተሰብ ፍቅር የተገመደ ይሁን |
| ለሙንኩስ ማሳአንቱን | ሁለቱም ይባረኩ |
| ላሙንኩሳ ኢለሙ አቢሱን | ሁለቱም ዘመድ ያክብሩ |

ኢልቱን ሥርቱን -                ይውለዱ ይክበዱ( ይብዙ)

ሆለመራ ኤቤ መገኑ ማሳኡሳ - ብዙ ነገር አምጠተዋል እግ/ር ይባርካቸው

ኢለሚን ደቀሚ ዋልቴ ዳቀንቹ

ዶሊ ሆሪ ኢሁን                ዛሬ ከእኛ ጋር ለመገናኘት መጥተዋል ይህ

ግንኙነት ለዘላለም ይደግ፣ ይቀጥል

- አኒሀ አማሃ ኢያኑ ኦሶ መኩ - የእናትና የአባት ገድ ለእናንተ የተመቸ ይሁን

- ቲ ኢለንሰት ጎንድ ጎጌሳ ኢሁን -- ይህ ዝምድና እንደ ጉንዳን ክምር ይብዛ
- ኤሳች ፋኦ መገኑ ዊንሹ -- ከእኔ የቀረውን ምርቃት እግ/ር ይሙላው
- ቲ ኢለንሰት አንቀጸንቴቲ ኢሁን --ዝምድናችን የተፈቀረ ይሁን የተሳሰረ ይሁን
- ኤሳች ፋኦ መገኑ ዊንሹ -- ከእኔ የቀረውን ምርቃት እግ/ር ይሙላው
-

## አባሪ ሶስት

### የልጅቷ አጃቢዎች ሙሽራውን ሲነቅፉ

| መገኛ ቋንቋ | የአማርኛ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ሜሴሌ ቦኩ | የልጅቷ ቤተሰቦች |
| አት መርቿኒ | አንተ ምንድነህ? |
| ሀበንካን | ምን ያህል ነህ? |
| ኒ ቤቱት ወርቀተቤ | የእኛ ልጅ ወርቅ ናት |
| ኒ አመ ቤቱት አንጋት ዮኖታ ቤቱ ልጅ ናት | የእኛ ልጅ እኮ የከበረ ቤተሰብ ልጅ ናት |
| እቸስ ሀቂንን ቁጨእዬቤ | አንተ ምግቡን ከነእንጨቱ እየዋጥከው ነው |
| ምኔንተስ ዱብ መበቤ | በቤትህ ጠግበህ እንዳልበላህ ታስታውቃለህ |

- እሴ አን ቦኩ ዱበላሻቤ የአባቷ ቤተሰብ ሀብታም ነው
- መ ቡቸ ቆቼቤ ደግሞ የሰጠህው ምን ጥሎሹ ነው
- ከላይ የተገለፀውን ስድብ ቢጤ ቀልድ ስናይ፡ የሁለቱም ወገኖች እራሳቸውን ሲክቡ አንዱ አንዱን የማጥላላትና ሌላውን ዝቅ አድርጎ የእኛ ቤተሰብ ይበልጣል አይነት ስነ ልቦንን ሲነኩ እናያለን እናስታውላለን፡፡

## ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1/ ጋብቻ ላንተ/ላንቺ/ ምንድ ነው እንዴት ትገልጸዋለህ/ሽ/?

2/ ስንት አይነት ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች አሉ?

3/ ተጫጭቶ የመጋባት ስርኣት አለ?

4/ ስለ ጋብቻ ሲታሰብ የተጋቢዎችና የቤተሰብ ሚና ምንድ ነው?

5/ ከጋብቻ በፊት ገድ ማየት ለምን ይጠቅማል?

6/ ጥሩ እና መጥፎ ገድ የሚባሉ የትኞቹ ናቸው?

7 ከጋብቻ በፊት የሚደረጉ ስርኣቶች ምን ምንድ ናቸው? በጋብቻ ወቅትስ?

ከጋብቻ በኋላስ?

8 በአያንዳንዱ ስርኣት ላይ የሚደረጉ የሀሳብ ልውውጦች ምን ምንድ ናቸው?

9/ የጥሎሽ ስርኣት አስፈጻሚዎች ምን ይላሉ? በዚህ ወቅው አይመረቅም? ምን ተብሎ?

10/ ከጋብቻ በኋላስ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት እያለች ምን ይደረጋል?

11/ የድንግልና ገበያ ምንድ ነው?

12/ የሰርግ ጥሪ አደራረግ እንዴት ነው?

13/ ለሙሽሪት ስም ይወጣላት መቼ እንዴት?

13 ለሙሽሪት ከሚወጡ ስሞች መካካል የምታወቁትን ንገሩኝ?

14 ለሙሽሪት የሚሰጡ ስሞች ትረጉሙ ምንድ ነው?

15/ ለሙሽሪት የሚሰጡ ስጦታዎች ምን ምንድናው?

16 የሙሽሪት ሰርጓ ሲደርስ ከሚዜሙ ግጥሞች መካካል የምታውቁት?


17 የውርስ ጋብቻ የአፈጻጸም ስርኣት እንዴት ነው?

18/ በማግባባት የማግባት ስርኣት እንዴት ይፈጸማል?

19/ የጠለፋ ጋብቻ መንስሂና አፈጻጸሙ  እንዴት ነው?

20/ እነዚህ ባህላዊ ጋብቻዎች ቀጠይነት የሚኖራቸው ይመስላችኋል?


# የደቡብ ክልል ካርታ




ምንጭ:- የምስራቅ ባዳዋቾ ጤና ቢሮ

# አ ሸ ም! ኮ ካ ታ

## *ከምባታ ጠምባሮ ዞን*




በኢትዮጵያ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የብሔረሰቦች ጥምረት ተምሳሌት የአንድነት መሠረት

ከአሳት እንደ ወጣ ትንታግ ጠንካራውን ዐለት ሰንጥቃ የወጣች የብዙ ፍሬ ዛፍ ዕድገት

*ከምባታ*

### የታሪክ የባሕልና የእምነት ዳሰሳ

ከመጋቢ ግርማ ዘውዴ አንጁሎ